
# ሐመር

## ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

የመጀመሪያ ዓመት ቁጥር 3 ሚያዝያ 1985 ዓ.ም.



እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሳችሁ!

- ሆሳዕና
- ሰሙነ ሕማማት
- ልሳን
- የጥያቄ መልስ
- የድኅነት ምስክር
- የቦረዳው ድንቅ ዋሻ

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሳችሁ!





የመጽሔታችን ማኅበርተኛ መሆን ለምትፈልጉ ሁሉ።

ለክ/ሀገር የዓመቱን ብር 38.40 ለአዲስ አበባ ብር 37.80 ወይም

ለክ/ሀገር የመንፈቁን ብር 19.20 ለአዲስ አበባ ብር 18.90 በአድራሻችን በአቶ ዮሐንስ አፈወርቅ ስም ብትልኩ እያንዳንዱን እትም በአድራሻችሁ የምታገኙ መሆኑን ስንገልጽ በመንፈሳዊ አክብሮት ነው።

አቶ ዮሐንስ አፈወርቅ
ሐመር መጽሔት ዝግጅት
የመ.ሣ.ቁ. 80078
አዲስ አበባ

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ሐመር

የመጀመሪያ ዓመት ቁጥር 3

ሚያዝያ 1985 ዓ.ም.


## ይዘት


1. ከአዘጋጁ ........................ 1
2. የማኅበሩ መልእክት ........... 2
3. ደብዳቤዎቻችሁ
   - ✣ የጥያቄ መልስ................ 4
4. ትምህርተ ሃይማኖት
   - ✣ ሰው የመሆን ምሥጢር..... 8
   - ✣ እርሱ ነው እሱ!! (ግጥም).... 10
   - ✣ ልሳን........................... 11
   - ✣ እመአምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ .... 13
   - ✣ ሰሙነ ሕማማት ............. 15
   - ✣ ሆሳዕና በአርያም (ስብከት).... 20
5. ኪነጥበብ
   - ✣ የድኅነት ምስክር ............26
6. እናስተዋውቃችሁ
   - ✣ የበረዳው ድንቅ ዋሻ.........29



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማስተባበሪያ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የሥነ–ጽሑፍ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ።


# ከአዘጋጁ

## እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሳችሁ!

በዚህ በትንሣኤ ወራት አብዝተን ስለክርስቶስ ትንሣኤና ከትንሣኤው በፊት በመስቀል ላይ የተቀበለውን መከራ፤ ያሳየውን አትሕቶ ርእስ ሁሉ እያሰብን ማስታወሳችን አይቀርም። ለሰው ልጆች ያለው ፍቅር የቱን ያህል ጥልቅ መሆኑንና የባሕርይ አምላክ የሆነው እርሱ ክርስቶስ ሰው ከመሆኑ አንስቶ ለቤዛነት በመስቀል ላይ እስከፈጸመው መሥዋዕትነት ድረስ የሆነውን በአንክሮ ስንመረምርና ዓለም ያለችበትን የሕይወት አዝማሚያ ደግሞ ስናጤን አንድ የሚያስገርምና የሚያሳዝን ነገር በህሊናችን መከሰቱ የማይቀር ነው።

እግዚአብሔር የወደቀውን ሰው ለማንሣት ሰው ሆነ፤ የሥጋን ባሕርያት ገንዘብ አድርጎ በሥጋ ተመላልሶ አብነት የሆነውን ነገር ሁሉ ፈጸመ። በሞት እንኳ ሕይወት መኖሩን አስተማረ፤ ሞቶም ለሞቱት ሕይወትን ሰጠ። ይህ ነው እጅግ የሚያስገርመው ነገር። ምንኛ የጸና ፍቅር ነው? የቱን ያህል የፈጠረውን ፍጥረት ቢወደው ነው? ያሰኛል። በጠሊቅ ለመረመረው በዘመናት ሁሉ ውስጥ ቢታሰብ ምንጊዜም ድንቅ ነው፤ እንዲህ ሆኖም አያውቅምና።

ይህን በመሰለ ፍጹምና ድንቅ ፍቅር ቤዛነት የተከፈለለት እግዚአብሔርን መስሎ የተፈጠረው የሰው ልጅ ደግሞ ማን መሆኑን ዘንግቶ፥ ከየት መምጣቱን ረስቶ ከአፈር ያበጃጀውንና ሰው ያደረገውን አምላኩን ክዶ በመስቀል ላይ የሰቀለው መሆኑን ማሰብና ዛሬም ቢሆን ወደኋላ ዘወር ብሎ ያለፈውን ታሪክና ክስተት በማስተዋል የሕይወቱን ሚዛን ለመጠበቅ ራሱን የማይመለከትና የማይመረምር፥ ይልቁንም እጅግ በሆነ ፍጥነት ወደሞት – ወደዘለዓለማዊው ሞት ሲከንፍ መመልከት በጣም የሚያሳዝን ነገር ነው።

ይሁን እንጂ ከክርስቶስ ትንሣኤ የተማርነው አንድ ነገር አለ። ሞትን ድል አድርጎ መነሣት ጌታችን በእውነት እምነት በፊቱ ለሚመላለሱ ሁሉ ለክርስቲያኖች አብነት ይሆን ዘንድ የፈጸመው፤ ሞትን ድል አድርጎ ለእኛም ተስፋ ትንሣኤን የሰበከበት አማናዊ ትንሣኤ። ስለዚህ የክርስቶስ ከሆንን ከክርስቶስ ጋር ደግሞ እንነሣለን የእርሱን ትንሣኤ ምሳሌ አድርገን። ለዓለማችን ሰው ለእኛም ቢሆን ያልገባን አንድ ምሥጢር ያለ ይመስለናል። በሥጋ የሚኖር ሞትን የማያውቅ ይመስለናል። ለመቃብር የሚያበቃው የምናየው ግዙፍ ሞት ብቻ ይመስለናል። ሌላም ሞት አለ፤ በሥጋ ቆሞ በነፍስ መሞት። ለዓለማችን ግልጥ ያልሆነው ይህ ሞት ነው። ዛሬም የምንሰብከው ልንሰብክ የሚያስፈልገውም ትንሣኤ በፍጻሜው ዘመን በግድ የሚሆነውንና የክርስቲያኖችን ተስፋ ብቻ ሳይሆን ይህን በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር የሚለይ የልቡና ሞት የምናሸንፍበትን ትንሣኤ ልቡናን ነው። ሰው ሁሉ ከኃጢአቱ የተነሣ በዓለም መቃብር ተቀብሮ በዲያብሎስ ግዛት ውስጥ ተይዞ ነው ያለው። ስለዚህ ትንሣኤ ያስፈልጋል፤ የልብ ትንሣኤ። የራስን ፈቃድ ሥጋዊውን ምኞት አሸንፎ ራስን ከኃጢአት ባርነት ነፃ አድርጎ በእውነት የእግዚአብሔር ሰው ለመሆን በሚያበቃ የልቡና ለውጥ ትንሣኤ ነው። የእግዚአብሔር ማደሪያ የዘለዓለም ሕይወት ባለቤት ያደርጋልና።

ስለዚህ ሐመር የክርስቶስን ትንሣኤ አብነት አድርጎ በመጨረሻው ዘመን እንነሣለን፤ ሞት ተሸነፈልን ማለት ብቻውን በቂ አይደለምና ሁላችን የልቡና ትንሣኤ ይኑረንና ሕይወታችንን በሥጋውና በደሙ ማኅተም ለዘለዓለማዊ ተስፋ እናብቃ ትላለች።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።


ዋና አዘጋጅ – ብርሃኑ ጎበና ካሣ

ም/ዋና አዘጋጅ – ዲ.እሸቱ ታደሰ ወንድም አገኘሁ

✉ 80078/1283

☎ 12–34–25

አዲስ አበባ



የማኅበረ ቅዱሳን ቤተ መጻሕፍት
MAHIBERE KIDUSAN LIBRARY

# የማኅበሩ መልእክት

## ሐመር

ሐመር ቃሉ የግዕዝ ሲሆን ትርጉሙም መርከብ ማለት ነው። መርከብ ደግሞ የሰው ልጅ ከእንጨት፥ ከብረት፥ ከፓሊስተርና ከመሳሰሉት ነገሮች ሠርቶ በባሕርና በውቅያኖስ ላይ ለተለያየ አገልግሎት የሚጠቀምበት ነው። በተለይ በአሁኑ ወቅት መርከብ ለሰው ልጅ ትራንስፖርትና በጦርነት ረገድ የሚሰጠው አገልግሎት እጅግ የጎላ ነው።

የመጀመሪያዋ ሐመር (መርከብ) የተሠራችው ግን የአዳም ልጆች በዝተው በምልዓተ ኃጢአት ተጥለቅልቀው እግዚአብሔርን አሳዝነው እርሱም እነዚህ ኃጢአተኞች በንፍር ውኃ እንዲጠፉ ባደረገበት ወቅት ነበር። አካሄዱን በእግዚአብሔር ፊት ያደረገው አንድ ጻድቅ ኖህ ብቻ በመገኘቱ ዘርን ያስቀር ዘንድ መርከብ እንዲሠራ በእግዚአብሔር የታዘዘ መሆኑን እንመለከታለን። ዘፍ.7፥1–12።

ዛሬ ግን መርከብ–ሐመር በክርስቶስ ደም የተሠራችው ቅድስት ቤተክርስቲያን ናት። ይህችውም ለምእመናን ወንጌልን በማስተማር፥ የእግዚአብሔር ልጅነትን በማሰጠት፥ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን እንዲቀበሉ በማድረግ በአጠቃላይ ጸጋ መንፈስ ቅዱስን በማሰጠት ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት–መንግሥተ ሰማያት የምታደርስ መንፈሳዊት ሐመር ወይም ሕያዊት መርከብ ናት።

ማኅበረ ቅዱሳንም ዛሬ በክርስቶስ ደም የተመሠረተችው ቤተክርስቲያን (ሐመር) መሠረቱ ናትና፥ «ሐመር» በሚል ስያሜ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በየጊዜው በሚያሳትማት መንፈሳዊ መጽሔት ትምህርተ ወንጌልን ለምእመናን ያቀርባል። ለመጽሔቱ ዓርማ አድርጎ ያቀረበውም የኖኅ መርከብ (ቅድስት ቤተክርስቲያን) መስቀሉን ተሸክማ፥ ቅዱስ መጽሐፉን ይዛ በመንፈስ ቅዱስ እየመረመረች በአማናዊው (እውነተኛው) ካፒቴን (የመርከቡ መሪ) እግዚአብሔር እየተመራች በውቅያኖስ (በዓለም ላይ ስትጓዝ) ነው። ከላይም «ንዑ ኀቤየ (ወደኔ ኑ) በማለት ድምፅዋን ከፍ አድርጋ የአዳም ልጆች ሁሉ በመርከቧ እንዲሳፈሩ የምትጣራ፥ ደውሏንም ሳታቋርጥ የምታሰማ መሆኑን ለማመልከት ነው።

በኖኅ ዘመን የነበሩ ሰዎች ለእግዚአብሔር ባለመታዘዛቸው ምክንያትና በክፉ ሥራቸው እግዚአብሔርን አሳዘኑት፤ አስቆጡትም። እርሱ ግን ሁሉን ቻይ አምላክ በመሆኑ ኖኅን መርከብ እንዲሠራና ከጥፋቱ ውኃ ከቤተሰቦቹ ጋር እንዲድን መመሪያ በሰጠበት ጊዜና መርከቢቱም በምትሠራበት ዘመን ሁሉ በኃጢአት የተመረዘው ሕዝብ ሊገነዘብና ሊያስተውል አልቻለም። አብዝቶ በመብላትና በመጠጣት፥ በመስከር፥ ሕገወጥ በሆነ ጋብቻ ያገቡና ይጋቡ ነበር። ይዘፍኑና ይጨፍሩ ኃጢአትን ያደርጉ ነበር። የኖኅን የእውነት ምስክርነትም አልተቀበሉም። ከኃጢአታቸው እንዲመለሱ ያስተማራቸውን ትምህርትና ማስጠንቀቂያ ወይም ማስገንዘቢያ ፈቃደኞች ሆነው አልተቀበሉም፥ ፈጣሪያቸውን ረስተው ከእነርሱ በላይ ምንም ዓይነት ኃይል እንደሌለ አድርገው ወሰዱ፤ እምቢተኞችም ሆኑ፥ 1ጴጥ.3፥20። 2ጴጥ.2፥5። የአምላካቸውን ትዕግሥት ስላልተገነዘቡት ቸርነቱን ስላላስተዋሉና በቃሉም ስላልታዘዙ ባልታሰበ ሰዓት በንፍር ውኃ ከምድር ላይ አጠፋቸው።

ዛሬም ዓለም በምልዓተ ኃጢአት ተጥለቅልቃለች፤ ሰዎቿም በኖኅ ዘመን የነበሩትን ይመስላሉ፥ የሰው ልጅ እግዚአብሔርን በክፉ ሥራው እያሳዘነው ነው። ስለሆነም ማኅበሩ ሐመርን መሠረት አድርጎ ያን ዘመን መለስ ብላችሁ ቃኙት በማለት ያስገነዝባል። እንደ ኖኅ ያሉ ጻድቃንና ቅዱሳን በአሁኑ ወቅት መኖራቸውን ባለቤቱ እግዚአብሔር ብቻ ቢያውቅም ትንቢቱ ይፈጸም ዘንድ፥ (ማቴ. 24፥14።) ቃሉ ለመፈራረጃ ይሆን ዘንድ በዓለም ወንጌል ይሰበካል። አባቶች መምህራን ሁሉ በየአጥቢያው ቤተክርስቲያን ያስተምራሉ፥ የሚሰማና ወደ ሐመሯ (ቤተክርስቲያን) የሚገባ ግን የለም። ማኅበሩ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሐመሪቷ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሆኖ «ሸክማችሁ የከበደ ወደ እኔ ኑ። እኔም አሳርፋችኋለሁ» ማቴ.11፥28–30። በማለት ባወጀው ቃል በተለይ ፈጣሪውን ክዶ የሚቅበዘበዘውን፥ በክፋትና በኃጢአት ተመልቶ የሚራወጠውን ሁሉ ወደ ሐመሯ እንዲገባና ሸክሙን እንዲያራግፍ ደግሞ ደጋግሞ ይጣራል።

ኖኅ በእግዚአብሔር ትእዛዝ መርከብ ሠርቶ ቤተሰቦቹንና ከአራዊት፥ ከእንስሳት፥ ከአእዋፍ እንዲሁም ከሁሉም ዘር ሁለት ሁለት ወደ መርከቧ አስገብቶ ነፍሳቱ ከጥፋት ውኃ እንዲድኑ አድርጓል። ማኅበሩ ሐመር–ቤተክርስቲያንም ደሀ–ሐብታም፥ ቀይ–ጥቁር፥ የተማረ–ያልተማረ፥ ሴት–ወንድ፥...ወዘተ. ብላ ሳትለይ በቤተ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ክርስቲያን ውስጥ ተገኝተው የጽድቅን ሥራ እንዲሠሩ የምታደርግ መሆኑን በየጊዜው ያስገነዝባል።

መንፈሳዊት ሐመር (ቤተክርስቲያን) በብዙ መልኩ ከኖኅ መርከብ ትበልጣለች፥ በክርስቶስ ደም የተመሠረተች ናትና። የኖኅ መርከብ ነፍሳትን ከጥፋት ውኃ ያዳነችው በዚህ ምድር ላይ ከሆነ ሥጋዊ ሞት ብቻ ነበር። ሐመር-ቤተክርስቲያን ግን ከምድራዊው መልዓተ ኃጢአት (ጥፋት) ከልላ ጠብቃ ለሰማያዊው ዘለዓለማዊ ሕይወት ታደርሳለች፥ በኖኅ መርከብ (ሐመር) ነፍሳቱ እንዳሉ ምንም ሳይለወጡ ወጡ፤ በሐመር-ቤተክርስቲያን የገባ ግን ኃጥኡ ጻድቅ፥ ርኩሱ ቅዱስ ሆኖ ተለውጦ በምድርም ተደስቶ በሰማይም በዘለዓለማዊ ደስታ እንዲኖር ታደርጋለች። ማኅበሩም ማንንም ሳይለይ ዘለዓለማዊ ሕይወትን የምታሰጠውን ከሁሉም የምትበልጠውን እውነተኛይቱን ሐመር-ቤተክርስቲያን የአዳም ልጅ ሁሉ ቶሎ ዐውቆ በውስጧ እንዲገባና የገባውም ወጥቶ በውቅያኖስ-የኃጢአት ዓለም ውስጥ እንዳይሰጥም ያሳስባል።

ኖኅ እነዚያን ሁሉ ነፍሳት ያዳነው በአንዲት መርከብ (ሐመር) ነበር። ዛሬም አንድ እግዚአብሔር ሕይወትን የሚያድነው በአንዲት ሐመር-ቤተክርስቲያን ነው። ይህችውም የቀደመችውና እውነተኛይቱ (ኤፌ.6፥16።) ለመሆኗ ክርስቶስ በውስጧ በመኖሩ ይታወቃል። የሰው ልጅም ይህች አንዲት ሐመር-ቤተክርስቲያን የትኛዋ እንደሆነች በመንፈስ ቅዱስ መርምሮ ማወቅና በውስጧ መግባት ግዴታው ሲሆን፥ በየጊዜው በሰው በሚፈበረከው (በሚመረተው) ሰው ሰራሽ ቤተክርስቲያን መሰል ቤት እንደጠፍ ከብት ተነድቶ መግባቱ ግን ከእግዚአብሔር ቁጣ ወይም ከጥፋት ውኃ አያድነውም።

ይህች በክርስቶስ ደም የተሠራችው ሐመር-ቤተክርስቲያን አንዲት መሆኗን እናምናለን። በሥጋ ዘመናቸው ሁሉ እግዚአብሔርን ደስ አሰኝተው ላለፉት ጻድቃን ሰማዕታት፥ የስማቸው መታሰቢያ ይሆን ዘንድ-በኢሳ.56፥4-6። እንደተጠቀሰው ቤ/ክ ይታነፅላቸዋል። አብያተ ክርስቲያናቱ በመረጣቸው ቅዱሳን ቢጠሩም አንድ እግዚአብሔርን ለማምለክ የታነፁ ስለሆኑ በየትም ቦታ በቅዱሳኑ ስም ተሰይማ የምናገኛት ቤተክርስቲያን አሐቲ (አንዲት) መሆኗን መገንዘብ ይኖርብናል። ይልቁንም እግዚአብሔር በማይመረመረው ከሃሊነቱ የዓለም ጉዳና ረኸም በመሆኑ የሰው ልጅ ከሐመሯ ሳይገባ ከመንገድ እንዳይቀር በየአጥቢያው ወደ አንድ ሰማያዊ መንግሥት የምታደርስ ሐመር-ቤተክርስቲያን ስለአዘጋጀልን የሥጋን ፈቃድ አሸንፈን በመርከቧ ውስጥ ተገኝተን እግዚአብሔርን እያመሰገንን የተዘጋጀውን ዘለዓለማዊ ድግሥ (ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን) መመገብ እንደሚኖርብን ማኅበሩ አጥብቆ ያሳስባል።

በሐመር-ቤተክርስቲያን ውስጥ እስከአለን ድረስ መድኃኒተ ዓለም ክርስቶስ ስለማይለየን ፲ፈለገው ማዕበል፥ ነፋስ፥ ሞገድ ቢነሣ ሁሉንም ስለሚገስጻቸው በሰላም ወደ ዓለምንበት ዘለዓለማዊ ቤታችን መድረስ ይቻላል። በሐመሯ ውስጥ ከጌታ ጋር እያለን ማዕበል እንኳ ቢነሣ ድርሻችን ጌታ መድኃኔ ዓለምን ከእንቅልፉ መቀስቀስ ነው። ማቴ.8፥23-27። ይኸውም የሁሉ ፈጣሪ እግዚአብሔር የሚያንቀላፋ አምላክ ሆኖ ሳይሆን፥ በሐመር-ቤተክርስቲያን ውስጥ ሳናቋርጥ መጸለይና ማመስገን እንደሚገባን ለማስተማር ነው። ይህም የአዳም ልጆች ሁሉ ተግባር መሆኑን ሐመር በማኅበሩ አንደበት ታሳስባለች።

ሌላው፥ የኖኅ መርከብ የሰው ልጆች መመኪያ፥ የኃጥአን ተስፋ፥ የኃጥአን አማላጅ፥ የደካሞች ምርኩዝ፥ የአዳም ተስፋ፥ ለሆነችው ቤዛዊተ ኩሉ ዓለም ወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ናት። የእግዚአብሔር እናት ሆና የተገኘች፥ በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል የተመሰገነች፥ ኃጢያተኛው የሰው ልጅ በእርሷ አማላጅነት ተማፅኖ ይድናልና፤ ከዚህ አንፃር በመንፈስ ቅዱስ የተቃኙ አባቶቻችን በኖኅ መርከብ-ሐመር መስለዋታል።

ማንኛውም የአዳም ልጅ የእግዚአብሔር እናት መሆኗን፥ የምሕረት ቃልኪዳን መቀበሏን አምኖ ከልጅሽ ከወዳጅሽ ምሕረትን ለምኝልን ቢል በምልጃዋ ከሞት፥ ከጥፋት፥ የሚድንባት አማናዊት ሐመር እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት። ማኅበሩ በተለይ ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያምን ምርኩዝ አድርጎ፥ እያንዳንዱ ሰውም ከተዘፈቀበት ኃጢአት በርኅራኄ እናቱ በድንግል ማርያም ምልጃ ተማፅኖ ይድን ዘንድ አጥብቆ ያስገነዝባል።

እንግዲህ ማኅበረ ቅዱሳን መጽሔቱን «ሐመር» በማለት የሰየመበት ምክንያት ከፍ ብሎ በሰፊው የተሰጠውን ትምህርትና ምሥጢር ለማስተላለፍ ነው። በሐመር አማካኝነት የጥፋት ውኃ ከሆነ ኃጢአት እንድንድን፥ ከፊታችን ከተደቀነ ፈተና እንዲሁም ከክህደት ማዕበል እንድናመልጥ በሐመር-ቤተክርስቲያን ውስጥ ተገኝተን በሥጋ ወደሙ ታትመን በሐመር-ወላዲተ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት ለሰማያዊ መንግሥት እንድንታደም እግዚአብሔር ይርዳን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

አሜን።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ደብዳቤዎች

በዚህ ዓምድ ከአንባብያን የተላኩ አስተያየቶችን፥ መንፈሳዊ ምክሮችንና የተለያዩ ጥያቄዎችን ከነመልሳቸው እናቀርባለን።

## የጥያቄ መልስ

ታቦትን አስመልክቶ ዲ/ዘመንፈስ ከአርሲ ለጠየቁን ጥያቄ የተሰጠ መልስ።

ትምህርተ ሃይማኖት (የሃይማኖት ትምህርት) በሁለት ይከፈላል ። ይኸውም

1ኛ. ዶግማ ፤ 2ኛ. ቀኖና በሚል ነው።

ዶግማ ቃሉ የግሪክ ሲሆን ፍቹም እምነት ማለት ነው።

ቀኖና ደግሞ ቃሉ የግሪክ ሲሆን ሥርዓት ማለት ነው። ከነዚህ ከሁለቱ ዶግማ ወይም እምነት አይጨመርበትም፣ አይቀነስለትም፣ አይሻሻልም፣ ችግርና ፈተናም ቢመጣ እስከሞት ድረስ አጥብቀን የምንይዘው ነው። ለምሳሌ ያህል ይህን ዓለም ከአለመኖር ወደመኖር አምጥቶ የፈጠረ ቢመረምር እንጂ የማይመረመር ሁሉን ቻይ አምላክ የሚሳነው ነገር የሌለ ፈጣሪ፥ የሰማይና የምድር ባለቤት የሠራዊት ጌታ ሕያው እግዚአብሔር ነው።

እግዚአብሔር (ፈጣሪ) የአካል ሦስትነት አለው። በመለኮትና በመፍጠር በሥልጣን በፈቃድ ግን አንድ ነው።

በሦስትነቱ አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ ሲባል በአንድነቱ አንድ መለኮት አንድ እግዚአብሔር ይባላል። በአዳም ምክንያት ከመጣው የዘለዓለም ሞትና ከዲያብሎስ ባርነት ነፃ የወጣነው ከሦስቱ አካላት በአንደኛው አካል ማለትም በውልድ በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህ ዶግማ ወይም እምነት ይባላል።

ቀኖና ግን በአምላካችን በኢየሱስ ክርስ ቶስ አምነው ያደጉ ክርስቲያኖች የሚመሩበት ሥርዓት ስለሆነ፤ በሃይማኖት አባቶች ወይም በቅዱስ ሲኖዶስ አማካኝነት እንደጊዜው ሁኔታ የሚሻሻል በመሆኑ የሚጨመርበት የሚቀነስለት ነው። ለምሳሌ ያህል እኛ ኦርቶዶክሳውያን ስንጠመቅ ሴት በሰማንያ ወንድ በአርባ ቀናችን ነው። የተወለዱት ሕፃናት ሴቷ ሰማንያ ወንዱም አርባ ቀን ሳይሞላቸው ቢታመሙና በሽታው አስጊ ከሆነ በ10፥ በ20፥ በ30...ቀናቸው መጠመቅ ይችላሉ ቀኖና ነውና። በቤተ ክርስቲያናችን የቀዳስያን ብዛት መነሻው አምስት ነው። ምናልባት ከአምስቱ አንዱ፥ ሁለቱ፥ ሦስቱ ቢታጡና ሌላም ተፈልጎ እስከ መጨረሻ የማይ ገኝ ከሆነ ከአቅም በላይም የሆነ ችግር ከገጠመ ሁለቱ ወይም አንዱ ብቻ ቀድሶ ማቁረብ ይች ላል። ቀኖና ነውና። በቤተ ክርስቲያናችን ታቦት ሲወጣ ቤተ ክርስቲያኑን የሚዞረው ሦስት ጊዜ ነው ችግር ካለ አንድ ጊዜ ብቻ ዞሮ መግባት ይችላል። ቀኖና ነውና በአጠ ቃላይ ሥርዓትን በተመለከተ ቀኖና ይባላል።

እምነትና ሥርዓትን ቅዱስ ጳውሎስ ለይቶ አስተምሮናል ለምሳሌ ያህል በቆላስይስ ሰዎች 2.ቁ.5 ላይ እንዲህ ይላል። «በሥጋ ምንም እንኳ ብርቅ በመንፈስ ከእናንተ ጋር ነኝና ሥርዓታችሁንም በክርስቶስም ያለውን የእምነታችሁን ጽናት እያየሁ ደስ ይለኛል» በዚህ ምንባብ ውስጥ በክርስቶስ የሆነው እምነት ዶግማ ሲባል ሥርዓት ብሎ የጠራው ቀኖናን ነው። ስለቀኖና (ስለሥርዓት) ቅዱስ ጳውሎስ ደጋግሞ ጽፏል። ከጻፈውም ውስጥ፤

1. «ነገር ግን ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን።» 1ቆሮ.14፥40።

2. «ወንድሞች ሆይ ከእኛ እንደተቀ በለው ወግ ሳይሆን ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን። እኛን ልትመስሉ እንዴት እንደሚገባችሁ ራሳችሁ ታውቃላ ችሁና» 2ተሰ.3፥6–7። ቀኖና (ሥርዓት) የሚወሰነው በሃይማኖት አባቶች እንደሆነና ወንጌልን የሚያስተምር ሰው ለሚያስተምራ ቸው ክርስቲያኖች በሃይማኖት አባቶች የተወሰነውን ቀኖና ማስተማርና መስጠት እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ሲል ያስረዳል።

በከተማዎችም ሲዞሩ በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያትና ሽማግሌዎች የቆረጡትን (የወሰኑትን) ሥርዓት ይጠብቁ ዘንድ ሰጧ ቸው። አብያተ ክርስቲያናትም በሃይማኖት ይበረቱ ነበር፥ በቁጥርም ዕለት ዕለት ይበዙ ነበር።» ይላል። የሐዋ.16፥4–5። በዚህ የእግዚአብሔር ቃል መሠረት ቅዱስ ጳውሎስ ደርቤንና ልስጥራን በተባሉ ቦታዎች ለነበሩ ክርስቲያኖች ወንጌልን ከሰበከ በኋላ ሐዋርያት የወሰኑትን ቀኖና (ሥርዓት) እንደሰጣቸውና እናያለን። ይህም ሥርዓት በቁጥር አምስት ላይ እንደምናየው አብያተ ክርስቲያናት በሃይ ማኖት (በዶግማ) እንዲበረቱ፥ በቁጥርም ዕለት ዕለት እንዲበዙ እንዳደረገ እንረዳለን። ስለዚህ ቀኖና ወይም ሥርዓት ቤተክርስቲያንን ይጠቅ ማል እንጂ አይጎዳም። በመሆኑም ዶግማንና ቀኖናን ወይም እምነትንና ሥርዓትን ጎን ለጎን ይዞ መጓዝ ሐዋርያትን መከተል እንጂ ወደ ኋላ ተመልሶ አይሁድን መከተል አይደለም። እንግዲህ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን የሚቃ ወሙ ሰዎች ሁሉ፥ የሚቃወሙት በቀኖና (በሥርዓት) የሚመሩትን ክርስቲያኖች ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል የሆነ መጽሐፍ ቅዱስን በመሆኑ እንዳይሳሳቱ አደራ እንላለን።

አሁን እንግዲህ የዶግማንና የቀኖናን ልዩነት ከተረዳን በቀጥታ ወደ ታቦቱ ጥያቄ እንሄዳለን።

ጥያቄ– 1.ዛሬ በኛ ቤተ ክርስቲያን ያለው ታቦት ነው? ወይስ ጽላት በታቦትና በጽላት መካከል ልዩነት አለና።

መልስ – ታቦት የጽላት ማስቀመጫ ነው። ዘጸ.40፥20። ጽላት ደግሞ ቅዱስ ቃሉ የተጻፈበት ቅዱስ ሰሌዳ ማለት ነው። ዘጸ.34፥27–28። ስለዚህ እነዚህ ሁለት ነገሮች ዛሬም በሐዲስ ኪዳን አሉ። ሆኖም ግን አሠራሩ ሙሉ በሙሉ በዘጸ.25፥10–18።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ያለውን የሙሴን ሕግ የተከተለ አይደለም። ምክንያቱም፥

1ኛ. ታቦት እንደሙሴ ሕግ የሚዘጋጀው ከግራር እንጨት ሆኖ ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል፤ ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል ቁመቱም አንድ ክንድ ተኩል ይሁን ይልና በውስጥና በውጭም በጥሩ ወርቅ ለብጠው፤ በዙሪያውም የወርቅ አክሊል አድርግለት ይላል። ደግሞም ታቦቱን የሚሸከሙት ከወርቅ በተሠሩ መሎጊያዎች አራት ሰዎች እንደሆኑ እንረዳለን። በአጠቃላይ የብሉይ ኪዳን የታቦት አሠራር እጅግ ከባድ ነው። አይቻልም። ምናልባት አንዳንድ የቤተክርስቲያን ፍቅር የነበራቸው ያለፉት ነገሥታትና ዛሬም ፍቅረ ቤተክርስቲያን ያላቸው አንዳንድ ምእመናን ይችሉት እንደሆን ነው እንጂ።

2ኛ. ጽላት፥ ጽላትም እንደሙሴ ሕግ ከሆነ መዘጋጀትና መጠረብ ያለበት ከድንጋይ ነው። በአንድ ታቦት ውስጥም መቀመጥ ያለባቸው ሁለት ጽላቶች ናቸው። ዘዳ.34፥1። በአጠቃላይ እንደብሉይ ኪዳኑ ሕግና ሥርዓት ከባድ ነው። የብሉይ ኪዳኑ ሥርዓትም ለሐዲስ ኪዳኑ ሥርዓት ጥላ ሆኖ አልፏል። 2ቆሮ.3፥7–11። ቆላ.2፥17። ዕብ.10፥1።

እንግዲህ እዚህ ላይ የሐዲስ ኪዳኑ ታቦትና ጽላት የብሉይ ኪዳኑን የታቦት አሠራርና ሥርዓት ጠንቅቆና ተከትሎ የማይሄድ ከሆነ፤ ይህ የብሉይ ኪዳኑን የታቦትና የጽላት አሠራር ሥርዓት ጠንቅቆ ያልሄደ የሐዲስ ኪዳን ታቦትና ጽላት ከየት መጣ? የሚል ጥያቄም ሳይነሳ አይቀርም።

አንባብያን ሆይ በቀጥታ ወደ ጥያቄው ከመግባታችን በፊት በዚህ ጽሑፍ መግቢያ ላይ ስለዶግማና ቀኖና ማብራሪያ የሰጠነው ይህን ለመሰለው ጥያቄ እንዲጠቅም ነው። አሁን ወደ ሐዲስ ኪዳን ታቦትና ጽላት ስንሄድ ቁም ነገሩ እንደሚከተለው ነው።

የሐዲስ ኪዳን ታቦትና ጽላት አሠራርም ሆነ አጠቃቀሙ የተወሰነውና የሚወሰነው በቀኖና ነው። ቀኖና ደግሞ እንደሁኔታው የሚሻሻል ነው። ሲቻል ይጨመርበታል ሳይቻል ደግሞ ይቀነስለታል። እንግዲህ በቤተክርስቲያናችን ቀኖና ካበረከተን ነገሮች አንዱ የሐዲስ ኪዳን የታቦትና የጽላት አሠራርንና አጠቃቀምን ነው።

ስለዚህ በሐዲስ ኪዳን ታቦትን ለመሥራት የግራር እንጨት ባይገኝ በዘፍ.1፥31 ላይ «እግዚአብሔር የፈጠረውን (ያደረገውን) ሁሉ ተመለከተ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ» ስለሚልና እግዚአብሔር የፈጠረውን ስለማይንቅ ከግራር ሌላ ከማይነቅዝ እንጨት መሥራት እንችላለን። ቁመቱ ወርዱና ዙሪያውም እንደችሎታችን ይሆናል። በውስጥና በውጭ ስለሚሆነው የወርቅ ክብርም እንደችሎታችን ይሆናል። ከሌለንም ወርቁ ይቀራል ቀኖና ነውና።

ስለጽላቱም እንደዚሁ ነው ከቻልን ከከበረ ድንጋይ፥ ከዕብነ በረድ መቅረጽ እንችላለን፤ ካልቻልን ጽላቱን ከማይነቅዝ እንጨት መቅረጽ እንችላለን። በሌላ በኩልም ከቻልን እንደ ብሉይ ኪዳኑ በአንድ ታቦት ሁለት ጽላት ማስቀመጥ እንችላለን፤ ካልቻልን በአንድ ታቦት አንድ ጽላት ብቻ ይሆናል። በተጨማሪም የጽላቱን ማስቀመጫ ታቦት ባይኖረን ጽላቱን ታቦት ብለን በመጥራት በጽላቱ ብቻ መጠቀም እንችላለን። ቀኖና ነውና።

በዚህ ጊዜ ደግሞ በኤር.31፥31። 2ቆሮ.3፥1–3። በዕብ.8፥8–13። የኛ ሥጋ የእኛ ልቡና የእርሱ ታቦትና ጽላት አልሆነም ወይ? በሐዲስ ኪዳን ለምን ታቦትና ጽላት አስፈለገ? ለምንስ ይህ ሁሉ ችግር ተፈጠረ የሚሉ አሉ። ለዚህም በቁጥር አንድ መጽሔት ላይ እንደተገለጠው አዎ የኛ የክርስቲያኖች ልቡና በክርስቶስ ደም ታቦት፥ ጽላት፥ ቤተ መቅደስ መሆኑን እናምናለን። ቢሆንም በሐዲስ ኪዳን ታቦትና ጽላት ያስፈለገው ስለአምላካችን ስለኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ሲባል ነው። ምክንያቱም በብሉይ ኪዳን ክብሩን የገለጠበት፥ ድምፁን ያሰማበት ሙሴን እንደባልጀራ ለማነጋገር የክብሩ ዙፋን ያደረገው ጽላቱ በውስጡ ያለበት ታቦቱ በመሆኑ፥ በሐዲስ ኪዳንም የሥጋውና የደሙ የክብር ዙፋን እንዲሆን ዞሮ ዞሮ ስለኛ በዓለም የተዋረደውን መድኀኒዓለም ክርስቶስን ለማክበር ሲባል ነው።

ጥያቄ – 2. በዘጸ.31፥18፤32፥15–19።34፥1–5። 2ዜና.5፥10 ያሉትን ጥቅሶች በመጥቀስ እግዚአብሔር ለሙሴ የሰጠው ሁለት ጽላቶችን ብቻ ነው። ነገር ግን የኢ.ት/ኦ/ተ/ቤተክርስቲያን እነዚህን እልፍ አእላፋት ጽላቶች ከየት አመጣቻቸው? አራብታችሁ ቅረጹ የሚል አለ ወይ?

መልስ – በዘዳ. 32፥19። ስንመለከት እግዚአብሔር ራሱ አዘጋጅቶ ለሙሴ የሰጠውን ሁለቱን ጽላቶች እሥራኤል ጣዖትን ሲያመልኩ ስላገኛቸው ሙሴ ተበሳጭቶ ሰበራቸው። ቸርነቱ ለዘለዓለም የሆነ አምላክ ሕያው እግዚአብሔርም ለሙሴ የመጀመሪያዎቹን አስመስሎ እንዲሠራ ነገረው። ሙሴም አስመስሎ ሠራ። ዘዳ.34፥1–5። መሥራት ብቻ ሳይሆን አሥሩን የቃል ኪዳን ቃላትም በጽላቶቹ ላይ እንዲጽፍ ሙሉ ሥልጣን ከእግዚአብሔር ተሰጠው። ሙሴም ተፈቅዶለታልና አሥሩን ቃላት በጽላቶቹ ላይ ጻፈ። ዘጸ.34፥27–28። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ጽላትንም ሆነ ታቦትን እያስመሰሉ ለመሥራት ሙሉ ሥልጣንን አግኝተናል። ይህን በተመለከተ አንዳንድ አባቶች እንዲህ ይላሉ።

«አዳም እንኳን በደለ፤ አዳም ባይበድል ኖሮ አምላክ ሰው ሆኖ በቀራንዮ ስለእኛ የመሰቀሉን፥ ስለኛ የመሞቱን የፍቅር ምሥጢር አናውቀውም ነበር።

እሥራኤልም የጥጃ ምስል በሆነው በጣዖቱ እንኳን በደሉ እሥራኤል ባይበድሉ ሙሴ አይናደድም፤ በእግዚአብሔር የተዘጋጁት ሁለቱ ጽላት አይሠበሩም፤ የሰው ልጅም እግዚአብሔር የሠራቸውን የፊተኞቹን አስመስሎ ለመሥራት ሥልጣን ባልኖረውም፤ ቢሠራም ለምን ሠራህ ለሚለው መረጃ ባላቀረበም ነበር» ይላሉ። ያም ሆነ ይህ ጽላትን አስመስለን፥ አባዝተን፥ አራብተን ለመሥራት መሠረታችን ሥልጣኑ ለኛ ለልጆቹ የተላለፈልን ከአባታችን ሙሴ ነው።

ሙሴ የተሰበሩትን አስመስለህ ሁለት ጽላቶች ቅረጽ ከሚል በቀር ጽላቶችን አብዝታችሁ አራብታችሁ ተጠቀሙ የሚል ቀጥተኛ ቃል አምጡ ለሚለው ግን ነገሩ እንዲህ ነው። በብሉይ ኪዳን የጽላትም ሆነ የቤተመቅደስ ሥርዓት፤ የመስዋዕቱ የዕጣኑ አገልግሎት፤ በኢየሩሳሌም ብቻ ስለነበረና፤ የሌላውም አገር ሕዝብ የሚከተለው የጣዖትን



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ሥርዓት እንጂ የሙሴን ሥርዓት ባለመሆኑ ጽላቱ ተባዝቶና ተራብቶ ለሌላው አገር ሕዝብ አልተሰጠም። እግዚአብሔርም ከኢየሩሳሌም ውጭ አልፈቀደም የተቀደሰውን ጣዖታውያኑ አሕዛብ ያረክሱታልና ስለዚህ ስግደቱም የቤተመቅደስ ሥርዓቱም በኢየሩሳሌም ብቻ ነበር። ዮሐ.4፥18–24።

በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦችም ሰሎሞን ያሠራው ታላቁ ቤተ መቅደስና ሁለቱ ጽላቶች አንሰውናል፤ በርቀት የምንገኝ እኛ የመንገድ ድካም በዝቶብናል። ስለዚህ በያለ ንበት ቤተ መቅደስ ሠርተን ጽላትን አስገብተን መጠቀም እንፈልጋለንና ይፈቀድልን ብለው ሙሴን ጠይቀው ሙሴም ከሁለቱ ጽላቶች በቀር ሌላ አልተፈቀደም ብሎ መልስ የሰጠበት ቦታ የለም።

ያም ሆነ ይህ በሐዲስ ኪዳን በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው በአብ፥ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠምቀው፤ ሁለተኛ ተወልደው የእግዚአብሔር ልጆች እንዲሆኑ ሥልጣን የተሰጣቸው ክርስቲያኖች ከፀሐይ መውጫ እስከ መግቢያዋ ድረስ እንደሚበዙና በአዲስ ኪዳን በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ንጹሑን ዕጣን፥ ንጹሑን ቁርባን ከኢየሩ ሳሌም ውጭ በየስፍራው ለእግዚአብሔር ማቅረብ እንደሚችሉ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል።

1. «ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያዋ ድረስ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ይሆናልና፥ በየሥፍራውም ለስሜ ዕጣን ያጥናሉ፤ ንጹሕም ቁርባን ያቀርባሉ፤ ስሜ በአሕዛብ ዘንድ ታላቅ ይሆናልና ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር» ሚል.1፥11።

2. «አስተማራቸውም ቤቴ ለአሕዛብ ሁሉ የጸሎት ቤት ትባላለች ተብሎ የተጻፈ አይደለምን? እናንተ ግን የወንበዶች ዋሻ አደረጋችኋት አላቸው» ማር.11፥17። ኢሳ.56፥7። ኤር.7፥11።

ይህ ትንቢት በቀጥታ ለሐዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች መሆኑ ግልጥ ነው። ምክንያቱም በብሉይ ኪዳን ቤተ መቅደስም ሆነ የዕጣን፥ የቁርባን አገልግሎት እንኳን ከፀሐይ መውጫ እስከ መግቢያዋ ድረስ ላሉ አሕዛብ በኢየሩሳሌም ከሚኖሩ የእግዚአብሔር ሕዝብ በቀር ለእሥራኤል ጐረቤት አገሮች እንኳ አልተፈቀደምና። ነቢዩ ሚልክያስ ንጹሕ ዕጣን ያለው በማቴ.2፥11። ወንጌሉ እንደሚለው ከአሕዛብ ወገን የሆኑ ሰብአ ሰገል በቤተ ልሔም ዋሻ ለክርስቶስ ካቀረቡት ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ በዓለም ያለን ክርስቲያኖች በክርስቶስ ስም ለክርስቶስ የምናቀርበው ቅዱስ ዕጣን ነው።

ንጹሕ ቁርባን የሚለውም በማቴ. 26፥26። ጌታ እንደነገረን ኅብስቱን አንሥቶ ሥጋዬ ነው፤ ወይኑንም አንሥቶ ደሜ ነው ያለው የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው። ንጹሕ የተባለው እሱ በባሕርዩ ንጹሕ ሆኖ የእኛን የኃጢአት እድፍ ስለሚያነጻ ነው።

አሁን እንግዲህ በብሉይ ኪዳን በኢየ ሩሳሌም ብቻ መሆን የሚገባቸው ቤተ መቅደሱ፥ ዕጣኑ ቁርባኑ በክርስቶስ ደም በሆነ በአዲስ ሕይወት በአዲስ ተፈጥሮ፥ በአዲስ ሥርዓት ክርስቲያኖች ለሆንን ለዓለም ሕዝብ በየሥፍራው (በያለንበት) እንድንጠቀምባቸው ከተፈቀዱልን በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩት ሁለቱ ጽላቶች ከፀሐይ መውጫ እስከ መግቢያዋ ተባዝተው በዓለም ያለን ክርስቲያኖች በያለንበት በየቤተ መቅደሳችን ለሥጋውና ለደሙ የክብር ዙፋንነት ብንጠቀምባቸውና የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ብናከብርባቸው ምን የሚጐዳ ነገር ተገኘ? የሚያስደነግጠውስ ምኑ ነው? ስህተቱስ የት ላይ ነው?

ደግሞስ አሠርቱ ትእዛዛት የተጻፉባቸው ሁለቱ ጽላቶች መባዛት መራባት የለባቸውም ከተባለ በጽላቶቹ ላይ የተጻፉት አሠርቱ ትእዛዛት መባዛት የለባቸውም። ከኢየሩሳሌ ምም መውጣት የለባቸውም ማለት አይደ ለም? ትእዛዛቱም ተከለከሉ ማለት ነውና።

በጽላቶች ላይ የተጻፉት ትእዛዛት በእግዚ አብሔር ፈቃድ በፀሐይ መውጫ እስከመግ ቢያዋ ድረስ በሚገኙ ክርስቲያኖች እጅ ገብተ ዋል። ይህም ያስደስታል እንጂ አያሳዝንም። ይህ ከሆነ ለሥጋውና ለደሙ (ለክርስቶስ) ክብር ሲባል በኦርቶ/ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ጽላቶች ምን በደል አስከተሉ? ክርስቶስ ከሚከብርና እግዚአብሔር ለቀደሙ አባቶቻችን በታቦቱ አድሮ የሠራላቸውን ድንቅ ሥራ እያስታወስን እግዚአብሔርን ከምናመሰግን በቀር ደግሞም ጌታ ስለ ጸሎት ሲያስተምረን «አባታችን ሆይ በሚለው ጸሎት ውስጥ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን» በሉ ብሏል። በዚህ መሠረት በራእየ ዮሐንስ 11፥19። ላይ ታቦቱን በሰማይ አሳይቶናል። ስለዚህ የሙሴ የቃል ኪዳን ታቦት በሰማይ እንዲገኝ፥ በሰማይ እንዲሆን በሰማይ እንዲታይ ፈቃዱ ከሆነ፤ በምድርም እንዲሆን ፈቃድህ ይሁን ብለን ብንጠቀምበት ስህተቱ ምን ይሆን?

ጥያቄ – 3. የሰሎሞን ቤተ መቅደስ እስኪሠራ ድረስ በእርግጥ ታቦቱ ከቦታ ወደ ቦታ ይዘዋወር ነበር፤ ቤተ መቅደሱ ተሠርቶ ታቦቱ ወደ ቤተ መቅደሱ ከገባ በኋላ ግን ካህናቱ ታቦቱን ተሸክመው ስለመውጣታቸው መጽሐፍ ቅዱስ አይናገርም። ታዲያ ዛሬ ክርስቶስ ደሙን ካፈሰሰ በኋላ፤ በብሉይም ሆነ በሐዲስ መመሪያ ሳይኖር፤ ከየት አምጥታችሁ ነው ታቦትን በየጊዜው በማውጣት የክርስ ቲያኖች ሕሊና ሁሉ ወደተሰቀለው ክርስቶስ መሆኑ ቀርቶ ወደ ታቦቱ የሆነው?

መልስ – በብሉይ ኪዳን እንኳን አይወ ጣም ነበር ማለት አንችልም ምክንያቱም በችግ ራቸው ጊዜ ለችግራቸው መፍትሔ ያገኙ ዘንድ ከነበረበት ከድንኳኑም ቢሆን ያወጡት ነበርና ለምሳሌ:-

1. በሙሴ የተተካ ኢያሱ ሕዝበ እሥራኤልን እየመራ ወደ ምድረ ርስት ሲሄድ ድንገት የዮርዳኖስ ወንዝ ሞልቶ ባገኘው ጊዜ ወንዙን ከፍሎ ሕዝቡን ለማሻገር ከእግዚ አብሔር በተነገረው መሠረት ካህናቱ ታቦቱን ከነበረበት ቦታ ተሸክመው ወደ ወንዙ በመሄድ ታቦቱን የተሸከሙት ካህናት እግር ወንዙን ሲረግጥ ወንዙ ተከፍሎ ሕዝቡ በሰላም ሲሻገሩ እናነባለን። ኢያሱ.3፥1–17።

2. እሥራኤል ምድረ ርስት በደረሱ ጊዜ ምድረ ርስት (ኢያሪኮ) በጠላት እጅ በጽኑዕ ግንብ ታጥራ አገኟት። በዚህም ጊዜ ይህን የጠ ላት የግንብ አጥር ለማፍረስና ርስታቸውን በእጃቸው ለማድረግ እግዚአብሔር



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

የገለጠላቸው ጥበብ ካህናቱ ታቦቱን ተሸክመው ሕዝቡም እየተከተሉ ሰባት ጊዜ ግንቡን እንዲዞሩት ነው። የታዘዙትን አደረጉ ግንቡም ፈረሰላቸው። ኢያሱ.6፥1–17።

3. እሥራኤል ጠላት በበረታባቸው ጊዜ ጠላትን ለማሸነፍ ካህናቱ ታቦቱን ተሸክመው ይወጡ ነበር። 1ሳሙ.5፥1–ፍ። ስለዚህ በብሉይ ኪዳን ካህናቱ ታቦቱን ከቦታ ወደቦታ ሲንቀሳቀሱ ካልሆነ በቀር ለሚፈልጉት አላማ ታቦቱን ካለበት ቦታ ተሸክመው አያወጡትም ነበር ማለት አንችልም። ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን ሠርቶ ካስገባውም በኋላ ቢሆን ካህናቱ ታቦቱን ተሸክመው እንዳያወጡ የሚል ሕግም የለም። ቤተ መቅደሱ እስኪፈርስ ድረስም ካህናቱ ታቦቱን ተሸክመው አላወጡም የሚልም ደግሞ የለም።

ካህናቱ ታቦቱን ተሸክመው ከቤተ መቅደስ እንደወጡ ምንባብ አለማግኘት ደግሞ በዚያ ቤተ መቅደስ ዘመን ሁሉ ታቦቱ አልወጣም ማለት አይደለም። እግዚአብሔር የሠራው ሥራ በብሉይ ኪዳን የተፈጸመው አገልግሎት ሁሉ ሙሉ በሙሉ በመጽሐፍ ቅዱስ አልተጻፈም። በመጽሐፍ ቅዱስም ያልተጻፈ ብዙ ነገር እንዳለ እናምናለንና በዚያም ሆነ በዚህ እኛ በሐዲስ ኪዳን ታቦትን ተሸክመን የምናወጣው፥

1ኛ. በብሉይ ኪዳን በእግዚአብሔር ቸርነት (ትእዛዝ) ካህናቱ ታቦታቱን ተሸክመው እንዲወጡ ተደርጎ ካህናቱም ታቦቱን ተሸክመው በመውጣት በታቦቱ ያደረ ኃይለ እግዚአብሔር ለሕዝበ እሥራኤል ያደረገውን ድንቅ ሥራ ለማሰብና እግዚአብሔርን ለማመስገን ነው። ዛሬም ለሥጋና ለደሙ የክብር ዙፋን የሆነውን ቅዱስ ስሙም የተጻፈበትን ቅዱስ ታቦት በምናወጣበት ጊዜ በደሙ የባረከን መድኅነ ዓለም ክርስቶስ አሁንም የሥጋውና የደሙ ዙፋን በሆነው በታቦቱ ረቂቅ ኃይሉን በማስተላለፍ በረከቱን ያበዛልናል ብለን በማመን ነው።

የተሰቀለው አምላክ መክበሩና መንገሡ ቀርቶ በየጊዜው ታቦት ወጣ እየተባለ ታቦቱ ብቻ ነገሠ ከበረ ሕዝቡም ወደ አምልኮ ባዕድ ኮበለለ ስለሚለው ግን አንድ ሕዝብ የንጉሡን ዙፋን ሲያከብርና ሲፈራ ንጉሡን ማክበሩና መፍራቱ እንደሆነ መዘንጋት የለበትም።

እኛ የምናምነው ቅዱስ ስሙ የተጻፈበትን የክርስቶስ ሥጋና ደም የክብር ዙፋን የሆነውን ታቦት ማክበራችን በኪሩቤል ዙፋን የሚቀመጥ መድኅን ክርስቶስን ማክበራችን መሆኑን ነው። በታቦቱ ፊት መስገዳችንም በታቦቱ ለተጻፈው ለቅዱስ ስሙ ነው። በታቦት ፊት ለእግዚአብሔር ስም ይሰግዱ የነበሩ ኢያሱና የእሥራኤል ሽማግሌዎች በረከት አገኙበት እንጂ አልተጎዱም ኢያ.7፥6። ዘዳ.33፥10።

በሐዲስ ኪዳንም «ድል ለነሣው ከተሰወረ መና እሰጠዋለሁ፥ ነጭ ድንጋይንም እሰጠዋለሁ፥ በድንጋይም ላይ ከተቀበለው በቀር አንድ ስንኳ የሚያውቀው የሌለ አዲስ ስም ተጽፏል» ራእ.2፥17። ለዚህ ስም ደግሞ ጉልበት ሁሉ መንበርከክ እንደሚገባ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል።

«በሰማይና በምድርም ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ ለኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው» ፊልጵ.2፥10–11። በዚህ መሠረት ቅዱስ ስሙ በተጻፈበት ከነጭ ድንጋይ (ከዕብነ በረድ፥ ከእንጨት) በተሠራው በጽላቱ ፊት ለቅዱስ ስሙ መስገድ ታላቅ የመንፈስ ጥበብ እንጂ ሞኝነት አይደለም። ምናልባት ስለታቦት፥ ስለጽላት ባለማወቅ ባጠቃቀሙ በኩል የሚሳሳቱ አባቶች እናቶች ካሉ ሽንጥን ገትሮ ማስተማር ተገቢ ነው።

ከዚህ በላይ ስለ ታቦት ከቤተ መቅደስ መውጣትና አለመውጣት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ከመሆኑም በተጨማሪ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሆኑ መታወቅ አለበት።

ብዙዎች በሐዲስ ኪዳን ታቦትን ለመቃወም በኤር.3፥16። የተጻፈውን ጠቅሰው «ከእንግዲህ የእግዚአብሔር ታቦት ብላችሁ የማትጠሩበት ጊዜ ይመጣል» ተብሏልና ታቦት አያስፈልግም በማለት ያስተምራሉ። ምንም እንኳን ይህ ቃል የተነገረበትን ምክንያትና ትንቢቱም መፈጸሙን በቁጥር 1–እትማችን የገለጽን ቢሆንም አንድ ነገር መጨመሩ አስፈላጊ ይመስለናል።

እንደተባለው ታቦት ብሎ መጥራት ካላስፈለገ በኤርምያስ 31፥34። ደግሞ «እያንዳንዱ ሰው ባልንጀራውን፥ እያንዳንዱም ወንድሙን እግዚአብሔርን ዕወቅ ብሎ አያስተምርም!» ተብሎ የተጻፈ ስለአለ እንግዲህ ሰው ሁሉ በየዘመኑ እግዚአብሔርን እንዲያውቅ ማስተማር አያስፈልግም ማለት ነዋ! ደግሞም ጌታችን በማቴ.28፥19። «ሂዱና አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ» ብሎ መናገሩ ስህተት መሆኑ ነዋ! በአጠቃላይ እንዲህ ነው ብሎ ከመናገር አስቀድሞ በመጽሐፍ የተጻፈው ነገር ለምንና እንዴት ባለሁኔታና ጊዜ መጻፉን ማጥናትና መልእክቱን (ምሥጢሩን) መመርመር ይገባል እንላለን።

በመጨረሻ ግን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የማርያም፥ የገብርኤል የጊዮርጊስ፥ ወዘተ. ታቦት እየተባለ የተሰየመበት ምክንያቱና የዚህ ስያሜ የትመጣው ምንድን ነው የሚሉ ጠያቂዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ እርግጥ ነው።

እንዲህ ተብሎ መሠየሙ በኢሳ.56፥4–6። በተገለጸው መሠረት የእግዚአብሔርን ሰንበቱን ለሚጠብቁ ደስ የሚያሰኘውንም ለሚመርጡ ቃል ኪዳኑንም ለሚይዙ ጃንደረቦች (ስለእግዚአብሔር መንግሥት ራሳቸውን ጃንደረባ ያደረጉ ቅዱሳን) ማቴ.19፥12 በእግዚአብሔር ቤትና በቅጥሩ የዘለዓለም መታሰቢያ እንደሚደረግላቸው የተገለጠ በመሆኑና ይህን አብነት በማድረግ የጌታ ሥጋውና ደሙ የሚከብርበት ሆኖ ለቅዱሳኑም መታሰቢያ ለማድረግ ነው። የቅዱሳን መታሰቢያ ለዘለዓለም ነው። መዝ.111፥7። እንዲሁም የጻድቅ መታሰቢያ ለበረከት ነውና ምሳ.10፥7። በዚህ ምክንያት እንጂ በታቦታቱ የሚከብረው መድኃኒተ ዓለም ክርስቶስ መሆኑ ግልጽ ሊሆን ያስፈልጋል። ከዚህ በተጨማሪ በቁጥር ሁለት እትማችን ስለ ጸበል በተጻፈበት ዓምድ ይህ የቅዱሳን መታሰቢያ በሰፊው የተገለጠ በመሆኑ ያንን ማንበብ ይጠቀማል።

እግዚአብሔር አስተዋይ ልቡና ይስጠን። ❖



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

# ትምህርተ ሃይማኖት

ይህ ዓምድ ስለ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ትምህርተ ሃይማኖት (ዶግማና ቀኖና) የምንማርበት ይሆናል።

## ሰው የመሆን ምሥጢር

ከብርሃኑ ጎበና

በምሥጢረ ሥላሴ አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ብለን ከአመንባቸው ከሦስቱ አካላት ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት የተወለደው ወልድ በተለየ አካሉ በቃልነቱ ከዊን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋን ነሥቶ ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ኾነ ብለን እናምናለን። «ወውእቱ ቃል ሥጋ ኮነ» «ያም ቃል ሥጋ ኾነ» እንዳለ ዮሐ.1፥14።

አንዳንዶች ግን ከእመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ የተወለደውን ጌታ እግዚአብሔር አይደለም በማለት በነቢይነት፥ በፍጡርነት እንዲሁም በአማላጅነት ደረጃ ሲያስቀምጡት ይታያሉ። ዳሩ ግን ለፍጥረታት ፈጣሪ፤ ሁሉን ቻይ ለሆነ ንጉሠ ሰማይ ወምድር፤ ለጌታችንና ለአምላካችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይግባውና እርሱስ ሁሉን ማድረግ የሚችል ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም የሚኖር ፈጣሪ እግዚአብሔር ነው። ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጥ የተብራራ እውነታ ነው። ምናልባት ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ እንደተናገረው «የሰማነውን ነገር ማን አምኗል? የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገልጧል?» እንዳለው ሆኖ መጽሐፍ ቅዱስ ስለጌታ የመሰከረውን «ጆሮ ዳባ ልበስ» ብለው ካላለፉት በስተቀር «የተናቀ ከሰውም የተጠላ የሕማም ሰው ደዌንም የሚያውቅ ነው ሰውም ፊቱን እንደሚሰውርበት የተናቀ ነው። እኛም አላከበርነውም። ...እርሱ ግን ስለመተላለፋችን ቆሰለ፤ ስለበደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሳጽ በእርሱ ላይ ነበረ።» ኢሳ. 53፥1–6። ተብሎ የተነገረው የቤዛነት ሥራው በቂ ነበር።

ስለአዳምና ስለልጆቹ ቤዛ ሊሆን መድኀኔዓለም ክርስቶስ ራሱን ዝቅ አድርጎ ወደምድር ወረደ። ይህንንም ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ በታላቅ አድናቆት ሲገልጽ «ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ያደረገልንን አስቡ፤ እግዚአብሔርነት የሌለው ኾኖ እግዚአብሔር የሆነ አይደለም የሌለውንስ አርአያ ገብርን ነሣ እንጂ (ራሱን ዝቅ አድርጐ ሰው ኾነ እንጂ) የሰውነት ሥራን ሠራ፤ አዘነ፥ አለቀሰ፥ ተራበ፥ ተጠማ፥ እስከሞት ድረስ ደረሰ፥ እሺ በጄ አለ። ፊልጵ. 2፥6–8። በማለት በትህትና ራሱን አዋርዶ ሰው ስለመሆኑ አድንቆ እኛም የጌታን ሰው መሆንና መከራ መቀበል፤ ስለ እኛ ብሎ ያደረገው እንጂ እርሱ በባሕርዩ ደካማ ሆኖ አለመሆኑን እንድንገነዘብ አሳስቦናል።

ንባቤ መለኮት ተብሎ የሚጠራው ዮሐንስ አካል ከህልውና ተገልጾለት ንጽሐ ሥጋ፥ ንጽሐ ነፍስ፥ ንጽሐ ልቡና ተሰጥቶት «በመጀመሪያ ቃል ነበረ... ቃልም እግዚአብሔር ነበር... ቃልም ሥጋ ሆነ።» ዮሐ.1፥1–14። በማለት ሰው የሆነው አምላክ ወልደ አምላክ እግዚአብሔር መሆኑን ይነግረናል።

ቅዱስ ጳውሎስ ይህን የእግዚአብሔርን ሰው መሆን ታላቅ ምሥጢር ለደቀመዝሙሩ ለጢሞቴዎስ ሲጽፍለት (የኪንግ ጀምስ የእንግሊዝኛውን ትርጉም ይመልከቱ) "And without controversy great is the mystery of godliness; God was mainfest in the flesh,..." በሥጋ የተገለጠ የእግዚአብሔርነት ምሥጢር በእርግጥ ታላቅ ነው። 1ጢሞ.3፥16። ምናልባት ይህን አገላለጽ በአሁኑ የዐማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ እትሞች በዚሁ መልኩ ላናገኘው እንችል ይሆናል። ቅዱስ ጳውሎስ እንግዲህ የእግዚአብሔርን በሥጋ መገለጥ ያለምንም ክርክር መቀበል እንዳለብን ያሳስበናል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፈሪሳውያንን ስለራሱ ማንነት ሲጠይቃቸው «ስለ ክርስቶስ ምን ይመስላችኋል? የማንስ ልጅ ነው?» ብሎ ነበር። እነርሱም «የዳዊት ልጅ ነው» አሉት። ጌታም መልሶ «እንግዲያስ ዳዊት እንዴት በመንፈስ ጌታ ብሎ ይጠራዋል?» በማለት የባሕርይ ጌትነቱን የዳዊት ፈጣሪ፥ የዳዊት ጌታ መሆኑን ገልጦላቸዋል። ማቴ.22፥41። ለፊልጶስም «ጌታ ሆይ አብን አሳየንና ይበቃናል» ባለው ጊዜ ጌታ ለፊልጶስ ሲመልስለት «ይህን ያህል ዘመን ከአንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አየ» በማለት የባሕርይ አንድነታቸውን አብ ሁሉን ቻይ እንደሆነ እርሱም (ወልድ) ሁሉን ቻይ መሆኑን ገልጾለታል። ዮሐ.14፥8–9። እንዲሁም በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 10፥30 «እኔና አብ አንድ ነን» በማለት በመለኮት በሥልጣን አንድ መሆናቸውን ገልጿል። በቀዳማዊ ዮሐ.5፥21። «እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘለዓለም ሕይወት ነው» ብሎ ዮሐንስ የባሕርይ አምላክነቱን መስክሮለታል። «በረከትና ክብር ምስጋናም ኃይልም ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለበጉም ይሁን ሲል ሰማሁ አራቱም እንስሶች አሜን አሉ፤ ሊቃናቱም ወድቀው ሰገዱ» ራእይ. 5፥13–14። እንግዲህ በጉ የተባለው ስለሁላችን ኃጢአት በቀራንዮ አደባባይ ሥጋውን የቆረሰው ደሙን ያፈሰሰው የድንግል ማርያም ልጅ የአብ የባሕርይ ልጅ መድኀኔ ዓለም ክርስቶስ አይደለምን? የባሕርይ አምላክ ካልሆነስ ኪሩቤልና ሱራፌል እንዴት ይሰግዱለታል? እንዴትስ ይገዙለታል?

«እግዚአብሔር በደሙ የዋጃትን ቤተክርስቲያን...» ሐዋር.20፥28። በማለት እያንዳንዳችንን ከሰይጣን ባርነት ነፃ ያወጣንና ቤተ ክርስቲያንን በደሙ የዋጃትን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እግዚአብሔር ብሎ ቅዱስ ሉቃስ ጠርቶታል።

ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት ነቢያትም እንደሚከተለው ጽፈዋል።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ኢሳ.48፥12–17። «...እኔ ፊተኛው ነኝ እኔም ኋለኛው ነኝ እጄም ምድርን መሠርታለች ቀኜም ሰማያትን ዘርግታለች በጠራኋቸው ጊዜ በአንድነት ይቆማሉ።»

ፊተኛ ኋለኛ መሆን የሚቻለው እግዚአብሔር አይደለምን? ፍጡር ቀዳማዊና ዳኀራዊ መሆን አይችልም፤ እግዚአብሔር ግን መጀመሪያ የሌለው መጀመሪያ ሲሆን እንዲሁም ደግሞ መጨረሻው ይህ ነው የማይባል ዘለዓለማዊ አምላክ ስለሆነ እኔ ፊተኛው ነኝ፤ እኔ ኋለኛው ነኝ ሊል ይገባዋል።

«ወደ እኔ ቅረቡ ይህንም ስሙ እኔ ከጥንት ጀምሬ በስውር አልተናገርሁም ከሆነበት ዘመን ጀምሮ እኔ በዚያ ነበርሁ፤ አሁንም ጌታ እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል።» ከሆነበት ዘመን ጀምሮ እኔ በዚያ ነበርሁ ማለቱ ያልነበረበት ጊዜና ዘመን አለመኖሩን ሲገልጽ ነው። እንግዲህ ያለና የነበረ ለወደፊትም የሚኖር እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስን አንብቤአለሁ የሚል ሁሉ የማይክደውና የማያስተባብለው እውነታ ሲሆን ከሦስቱ አካላት አንዱ አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ለመሆኑ «አሁንም ጌታ እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል» በማለቱ ይታወቃል። ይህንንም መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጥልናል። ሉቃ.4፥19። ዮሐ.10፥36። ዮሐ.16፥5። እነዚህና ሌሎች ጥቅሶችም ክርስቶስ ከባሕርይ አባቱ ከአብ፥ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ሂድ፥ ውረድ፥ ተወለድ፥ ተሰቀል፥ ሙት ተብሎ መላኩን የሚያስረዱ ናቸው።

<u>ሆሴ.13፥4።</u> «...እኔ ግን ከግብፅ ምድር ጀምሬ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ አታውቅም፤ ከእኔም በቀር ሌላ መድኀኒትም የለም። «ሆሴዕ ከእግዚአብሔር በስተቀር የባሕርይ አምላክ ሌላ እንደሌለ እንዲሁም እውነተኛ የሥጋና የነፍስ መድኀኒት እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ ገልጿል። ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ «የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኀኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን» ቲቶ.2፥12። በማለት የክርስቶስን አምላክነትና መድኀኒትነት ገልጾታል። እንግዲህ ክርስቶስ አምላክና መድኀኒት ከሆነ እግዚአብሔር መሆኑ ግልጽ ነው። ምክንያቱም ከእግዚአብሔር በቀረ መድኀኒት የሆነ የባሕርይ አምላክ የለም። እንዲሁም በሐዋርያት ሥራ 4፥12 «መዳንም በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና» በማለት የክርስቶስ አዳኝነት (መድኀኒትነት) ተገልጧል። በሉቃስ ወንጌል 2፥11 «ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኀኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋል» ተብሎ የበለጠ ተረጋግጧል።

<u>ዘካ.2፥8–12</u>። «...የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና:- ከክብሩ በኋላ ወደ በዘበዙአችሁ አሕዛብ ልኮኛል የሚነካችሁ የዓይኑን ብሌን የሚነካ ነውና። እነሆ እጄን በላያቸው አወዛውዛለሁ፥ ተገዝተው ለነበሩት ብዝበዛ ይሆናሉ። የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንደላከኝ ታውቃላችሁ።» በዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርን የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ልኮታል። የተላከው የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ለመሆኑ ምንም የሚያጠራጥር ነገር የለም። ስለዚህ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከንጽሕት ቅድስት ድንግል ማርያም በሥጋ የተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው ክብር ምስጋና ለእርሱ ይሁንና።

<u>ኢሳ. 9፥6</u>። «ሕፃን ተወልዶልናል ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል። ስሙም ድንቅ፥ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘለዓለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።» በበረት የተወለደው ሕፃን ኢየሱስ ክርስቶስ ለመሆኑ በማቴዎስ 2፥1፥ በሉቃስ 2፥7 የሰፈረውን መመልከት ብቻ በቂ ነው። ይህ ከቅድስት ድንግል የተወለደው ሕፃን የባሕርይ አምላክ መሆኑንና የዘለዓለም አባት መሆኑንም አስረድቷል። አምላካችንና አባታችንም አንድ ብቻ መሆኑን በሚል.2፥10። «ለሁላችን አንድ አባት ያለን አይደለምን? አንድ አምላክስ የፈጠረን አይደለምን?» በማለት ተጽፎ እናገኛለን።

<u>ዘጸአት.3፥14።</u> ሙሴ «...የአባቶቻችሁ አምላክ ወደ እናንተ ላከኝ ባልሁ ጊዜ ስሙስ ማነው? ባሉኝ ጊዜ ምን እላቸዋለሁ?» አለው እግዚአብሔርም ሙሴን «ያለና የሚኖር እኔ ነኝ» አለው። እግዚአብሔር ለሙሴ ያለና የሚኖር እኔ ነኝ ብሎታል። ከእርሱ በቀር ይህን ሊናገር የሚችል ፍጡር አይኖርም፥ የለምም። «ያለና የሚኖር» የሚለው ቃልም በእብራይስጡ «ያሕዌ ወይም ይሖዋ» ተብሎ ይጠራል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድሞ ለሙሴ «ያለና የሚኖር እኔ ነኝ» ብሎ የነገረው ታላቁ አምላክ እግዚአብሔር ለመሆኑ በዮሐንስ ራእይ.1፥8 «ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ አልፋና ዖሜጋ እኔ ነኝ ይላል። እንግዲህ ፍጡር ወይም አማላጅ ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላክ አልፋና ዖሜጋ እኔ ነኝ ሊል ይችላልን? የእንግሊዝኛው መጽሐፍ ቅዱስ (የኪንግ ጀምስ ትርጉም) "the Almighty" ብሎታል፤ «ሁሉን ቻይ» ለማለት። እንግዲህ ክርስቶስ ሁሉን ቻይ አምላክ መሆኑን በዚህ እናረጋግጣለን ማለት ነው።

<u>ኢሳ.40፥10</u>። «እነሆ ጌታ እግዚአብሔር እንደ ኃያል ይመጣል ክንዱም ስለእርሱ ይገዛል እነሆ ዋጋው ከእርሱ ጋር ደመወዙም በፊቱ ነው።» አስቀድሞ ኢሳይያስ በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ ሀብተ ትንቢት ተሰጥቶት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ዳግም ምጽአትና ፍርድ ሲናገር ክርስቶስን እግዚአብሔር ብሎ ጠርቶታል። ምክንያቱም ከድንግል ማርያም የተወለደው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሦስቱ አካላት አንዱ ነውና። እግዚአብሔርነትም ገንዘቡ ነው። መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በዮሐንስ ራእ.22፥12 «እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ። አልፋና ዖሜጋ ፊተኛውና ኋለኛው መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ» ብሎ ኢሳይያስ የተናገረው ለእርሱ መሆኑን አረጋግጦልናል። አልፋና ዖሜጋ፥ ፊተኛውና ኋለኛው፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስረዳን ከመሆኑም ሌላ በተጨማሪ ደግሞ የእሥራኤል ንጉሥ እግዚአብሔር፥ የሚቤዠም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። «እኔ ፊተኛ ነኝ። እኔም ኋለኛ ነኝ። ከእኔ ሌላም አምላክ የለም» ተብለናል ኢሳ.44፥6። ✣

ይቀጥላል።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# እሱ ነው እሱ!!

እሱ ነው እሱ የሕይወት ቃል
ቃሉ የማያልፍ የማይታበል
ጥንትም ያለ የነበረ
ዓለሙን በጥበቡ የመሠረተ
ምድርን በኃይሉ የፈጠረ
ዘመናትን የለካ የቀመረ
ነቢያትን ያናገረ
ኃያል ሱባኤ ያስቆጠረ
ከይስሐቅ ጋር የተሰዋ
እሥራኤልን ያከበረ
ከዮናስ ጋር በዓሣ ሆድ
ከዮሴፍ ጋር የታሰረ
እሱ ነው እሱ ለሙሴ
ሕጉን ትእዛዙን ያስተማረ።
በተረዳ ሦስትነቱ
የሚመሰገን በፍጥረቱ
በስም በግብሩ በአካላቱ
የሚመለክ በአንድነቱ
በሕልውናው በመለኮቱ
በአገዛዙ በጌትነቱ
እሱ ነው እሱ የጥንቱ የጥዋቱ
እንዘ አሐዱ ሠለስቱ።
በእፁብ ብቻ ይወሰናል
ቀዳማዊ ልደቱ
አይመረመርም ረቂቅ ነው
ዳግማዊ ሰውነቱ
ከወላዲተ–ቃል እናቱ
በድንግልና ተፀንሶ
በድንግልና መከሰቱ
ግሩም ድንቅ ነው ጥበቡ
ወሰን የለውም ቸርነቱ
ወልደ–አብ ወልደ–ማርያም
የሰማዩ የመሬቱ
እሱ ነው እሱ አልፋ ዖሜጋ
የሚታዘዙለት መላእክቱ።
የዓለም መድኃኒት ሥጋዌ
ረቂቅ ነው ምሥጢሩ
ቃል ከሥጋ መጣመሩ
ያለመለወጥ ሰው መሆኑ
ያለመቀላቀል ማደሩ
በፍቃዱ በግብሩ
አንድ ሆኖ መዋቀሩ
በተዋሕዶ መኖሩ
ሰው አምላክ ሆኖ መክበሩ።
እሱ እካን አይል ጥበበኛ
እጻድቅ አይል እውነተኛ
እነግሥ አይል ባለዙፋን
እከብር አይል የዓለም ጌታ
ዘላለማዊ ኃያል አምላክ
የማይወሰን በቦታ
እሱ ነው እሱ ሳንፈጠር የሚያውቀን
እንዲያው በጽድቁ የጐበኘን።
በፍቅር ተስቦ ተገዶ
ሰማያዊው መሬት ወርዶ
ሥጋ ለብሶ ተዋሕዶ
የከበረው ተዋርዶ
በአሮጌ ጨርቅ ተጠቅሎ
በጐለ እንስሳ ተጥሎ
ከፍጥረቱ ጋር ያደረ
እሱ ነው እሱ የኛ ተስፋ
ሞትን በልደት የሻረ።
የፈጠረውን ሥጋ ለብሶ
በሕግ ተከሶ ተወቅሶ
ተሰውቶ ደሙን አፍስሶ
እሱ ነው እሱ የታረቀን ተመላልሶ
እኛ በበደልን እሱ ከሶ።
እሱ ነው:- የበጐች መሪ በረኛ
ኖላዊ ትጉህ የማይተኛ
የደከመውን አጋዥ
የታመመውን ፈዋሺ
ምናለ ከእኛ ለሱ እሚሆን
እንዲያው ይክበር ይመስገን።

ከመ/ር ዘመነ አቡሐይ
ከጎንደር ጋይንት



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ልሳን

አባ ወ/ትንሣኤ አያልነህ

ካለፈው የቀጠለ

ባለፈው ቁጥር ሁለት እትማችን ስለልሳን መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተ ምረውን እውነት ተመልክተን በዘመ ናችን በልሳን እንናገራለን ስለሚሉ ሰዎች በዚህ እትማችን እንድናቀርብ በቀጠሮ መለያየታችን ይታወሳል።

በዛሬው ትምህርታችን ምእመናን ስለልሳን ሊያውቁ የሚገባቸውን ዐቢይ ነገር በመተንተን ይዘን ቀርበ ናል። በዘመናችን በልሳን እንናገራለን የሚሉና በዚህም እጅግ የሚመኩ አሉ። ነገር ግን ባለፈው እትማችን ከተመለከትነው አማናዊ ልሳን ጋራ ሲነፃፀር መጽሐፋዊ ያልሆነና ፍጹም ሐሰት ሆኖ እናገኘዋለን። ምክንያቱም በመንፈስ ቅዱስ ተሞላን ብለው የሚናገሩት አዲስ ልሳንም የሚሉት በዓለም ካሉት ቋንቋዎች አንዱን እንኳ የማይመስልና የቋንቋ ጠባይም ስለሌለው ነው።

ሐዋርያት እኮ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው በሌሎች ልሳኖች (ቋንቋ ዎች) ሲናገሩ በጉባዔ የተሰበሰቡት ሁሉ «በእያንዳንዳችን ቋንቋ ነው የሚ ናገሩት» ሲሉ መስክረውላቸዋል። ይህ የዘመናችን ልሳን ነኝ ተብዬ ቋንቋ የእኔ ነው ብሎ የሚመሰክርለት ባለመኖሩ ምን እንበለው። ማታለያ።

በእርግጥ አንዳንዶቹ የመንፈስ ቅዱስ ቋንቋ ነው ይላሉ። አንዳንዶች ደግሞ የመላእክት ቋንቋ ነው ይላሉ። መልካም እነሱ የሚሉትን አምኖ ለመቀበል በግድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ መኖር አለበት። ሐዋርያትና የመጀመሪያዎቹ በልሳን ተናጋሪ ክር ስቲያኖች ከሰው ልጆች ቋንቋ ውጭ በመንፈስ ቅዱስ ቋንቋ በመላእክትም ቋንቋ ተናገሩ የሚል አለ ወይ? ካለስ እስኪ መረጃው?

አንዳንዶች ደግሞ እንዲህ ይላሉ፥ በ1ኛ ቆሮ14፥10 «ለአን ዱም በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር፥ ለአንዱም በልሳኖች የተነገረውን መተ ርጐም ይሰጠዋል» ይላልና ምንም እንኳ እኛ ሰው በማይሰማው ቋንቋ ብንናገር የመተርጐም ጸጋ የተሰጠው ስለሚተረጉመው ችግር የለም ይላሉ።

መልካም «የትም ፍጭው ዱቄ ቱን አምጭው» እንዲሉ በፈለጉት ዓይነት የኮድ ቋንቋ ተንተባትበው ብዙኃኑ ወደሚሰሙት ቋንቋ ተርጉ መው ሰዎች ወደ ንሥሐ የሚመለሱ ከሆነ ባልተቃወምንም ነበር። ነገር ግን እኛን ያሳሰበን ነገር ቢኖር በልሳን ከመናገር በፊት በመንፈስ ቅዱስ መሞ ላት ሰበብ የሚከሰተው መንቀጥቀጥ፥ የሚታየው የአእምሮ መረበሽና መጮኽ ነው። የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ያስደስታል፥ ሰላምን ይሰጣል እንጂ አያስጨንቅም፥ አያንቀጠቅጥም፥ አእምሮንም አይለውጥምና ይኸም ዓይነት ድርጊት ወደ ክፉ መንፈስ እያዘነበለ በመሄዱ ጥንቃቄ ያስፈልገ ዋል እንላለን። መጽሐፍ ቅዱስ «መንፈስን ሁሉ አትመኑ ይላልና» (1ኛ ዮሐ.4፥1።)

እንደእውነቱ ከሆነ በ1ቆሮ.14፥ 10። ላይ ለአንዱ በልሳኖች መናገር ለአንዱ የመተርጐም ጸጋ ይሰጠዋል ሲል ለምሳሌ ያህል በአገራችን ብዙ ቋንቋዎች አሉ፤ ስለዚህ በጉባዔ ከተሰበሰቡት ለአንዱ እነዚህን ቋንቋ ዎች የመናገር ጸጋ ቢሰጠው የመተ ርጐም ጸጋ የተሰጠው ደግሞ እነዚህን ብዛት ያላቸውን ቋንቋዎች ብዙኃኑ ወደሚሰሙት ለምሳሌ ያህል ወደ ዐማርኛ ወይም ወደ ትግርኛ ወይም ወደ ኦሮምኛ እየተረጐመ የወንጌሉን ቃል ማሰማት ማለት ነው።

የልሳን ጸጋ በተለይ በብዛት መሥራት ያለበት በዚህ በመጨረሻው ዘመን ነው። ብለው የሚከራከሩት እንደመረጃ የሚያቀርቡት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እነሆ:-

«እግዚአብሔር ይላል፥ በመጨረ ሻው ቀን እንዲህ ይሆናል፥ ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ፥ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትን ቢት ይናገራሉ» ይላል። የሐዋ. 2፥27። ስለዚህ ዛሬ እኛ በልሳን የምንናገረው መንፈስ በጉባዔያችን እየፈሰሰ ነው። ኦርቶዶክሳውያንም በመንፈስ ተሞልተው በጉባዔያቸው በልሳን የማይናገሩት በጉባዔያቸው መንፈስ ስለማይፈስና ትክክለኛ እምነት ስለሌላቸው ነው ይላሉ።

እስኪ በቅድሚያ «በመጨረሻው ቀን» የሚለውን እንመልከት፤ አንባ ብያን ሆይ ይህን ቃል ከነቢዩ ከኢዩ ኤል ጠቅሶ የተናገረው ቅዱስ ጴጥሮስ ነው። የተናገረበትም ዕለት መንፈስ ቅዱስ በወረደበት ዕለት ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው በሌሎች ልሳኖች በተናገሩበት ሰዓት በበዓለ ሃምሳ ነው። የተናገረበትም ምክንያት ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ተሞል ተው በሐዋ.ሥራ 2፥ 5–15 እንደተ ገለጠው በዐረብኛ፥ በግሪክኛ፥ በእስያ፥ በሮማይስጥና በሊብያ... በመሳሰሉት ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ሲናገሩ የነዚህ ቋንቋዎች ባለቤቶች ከልዩ ልዩ አገሮች ተሰባስበው እግዚአ ብሔርን ለማመስገን እንደ ሥርዓታ ቸው በኢየሩሳሌም ተገኝተው ስለነ በርና በየገዛ ቋንቋቸው የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስን ማዳን (ወንጌልን) ስለሰበኩላቸው ተገርመው፥ ተደንቀ ውም እነዚህ ሐዋርያት ከዕብራይስጥ በቀር ሌላ ቋንቋ አይችሉም ነገር ግን በእያንዳንዳችን ቋንቋ የእግዚአ ብሔርን ታላቅ ሥራ እንዴት ሊናገሩ ቻሉ? አስደናቂ ነገር ነው በማለት ይህ ምልክት ሆኖላቸው በአንድ ቀን ሦስት ሺህ ሰዎች ሲጠመቁ በኢየሩሳሌም ያሉ አይሁድ ግን ከዕብራይስጥ በቀር ሌላ ቋንቋ ባለመቻላቸውና ሐዋርያት የሚናገሩትን ልዩ ልዩ ቋንቋ





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ባለመስማታቸው ሐዋርያትን ጉሽ የወይን ጠጅ ጠጥተው ሰክረው ነው የሚለፈልፉት አሉ። የሐዋ.2፥11–12። በዚህ ጊዜ ነው ቅዱስ ጴጥሮስ ተነሥቶ አሁን ከጧቱ ሦስት ሰዓት ነው የሚሰክሩበት ሰዓት አይደለም። ነገር ግን በነቢዩ በኢዩኤል ስለዛሬው ቀን ትንቢት ተነግሮ ነበር። ያም ትንቢት «በመ ጨረሻው ቀን ሥጋን በለበሰ ሁሉ ላይ መንፈሴን አፈሳለሁ፥ ወንዶች ልጆቻችሁና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ» የሚል ነውና አሁን ሐዋርያት ሰክረው ሳይሆን ይህ ትንቢት መፈጸሙን የሚያረጋግጥ ነው ሲል ተናግሯል።

አሁን እንግዲህ ቅዱስ ጴጥሮስ መንፈስ ቅዱስ የወረደበትን ዕለትና ሐዋርያት በልሳን የተናገሩበትን ዕለት የመጨረሻ ቀን ሲለው አሁን ያለን በትን የዓለምን የመጨረሻ ዘመን ነውን? አይደለም። ቅዱስ ጴጥሮስ የመጨረሻ ቀን ያለው የዓመተ ፍዳን፥ የዓመተ ኩነኔን፥ የዓመተ ኃጢአትንና የዓመተ ሞትን መጨረሻ ነው። የፍዳ ዘመን የኩነኔ ዘመን፥ የኃጢአትና የሞት ዘመን በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም አክትመዋልና ደግሞም በአዳም በደል ምክንያት ሞትና ኃጢአት የሰው ልጆችን እንደገዙ እንደማይቀሩና መድኅን ክርስቶስ አንድ ቀን በደሙ መፍሰስ እንደሚ ያስወግዳቸው ተስፋ ስለነበረና ይህም ተስፋ ብዙ ዘመናትን አስቆጥሮ ስለተፈጸመ፥ በክርስቶስ ደም ዲያብ ሎስና የእሱ የግብር ልጆች ሞትና ኃጢአት ድል የሆኑበትን፥ መንፈስ ቅዱስ ወርዶ በዓለም የብርሃን ሥራውን የጀመረበትን ሰሞን የመጨረሻ ቀን ብሎታል። ለዚህም መረጃ ይሆነን ዘንድ ቅዱስ ጳውሎስ በገላትያ መልእክቱ እንዲህ ይላል። «ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ልጁን ላከ» ይላል። ገላ.4፥4። በዚህ የእግዚአብሔር ቃል መሠረት አምላካ ችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ወደዚህ ዓለም የመጣበትና የተገለጠ በት ዘመን የዓለም የመጨረሻ ዘመን ነው ማለት አይደለም። የመዳን ተስፋ የተፈጸመበት፥ የገነት በር የተከፈተ በት፥ ሞትና ኃጢአት ድል የሆኑበት፥ ዲያብሎስ የእግዚአብሔርን ልጆች የመግዛቱ ዘመን ያከተመበት ማለት ነው እንጂ።

አሁን ስላለንበትና ስለዓለም እድሜ መጨረሻ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:-

«እርሱም በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ ደቀመዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ እርሱ ቀርበው፥ ንገረን ይህ መቼ ይሆናል? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድነው? አሉት። ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፥ ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ፥ ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና ብዙዎችንም ያስታሉ» ማቴ.24፥3–6።

«ብዙ ሐሰተኞች ነቢያትም ይነ ሣሉ፥ ብዙዎችንም ያስታሉ፥ ከአመ ጻም ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች» ማቴ.24፥11–12።

«በዚያን ጊዜ ማንም እነሆ ክርስቶስ ከዚህ አለ ወይም ከዚያ አለ ቢላችሁ አትመኑ፥ ሐሰተኞች ክርስ ቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፥ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ» ማቴ.24፥23–25። እስከመጨረሻው የሚጸና ግን እርሱ ይድናል» ማቴ.24፥13። ስለዓለም የመጨረሻ ዘመን ምልክቶች ማቴ.24 ከቁ.1 እስከመጨረሻው ብንመለከት ይጠቅመናል።

ክርስቲያኖች ሆይ! አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት በጠየቁት መሠረት ስለዓለም የመጨረሻ ዘመን የተናገራቸውን ስንመለከት ጸጋ መንፈስ ቅዱስ እየፈሰሰ በእውነተኛ ልሳን መናገር ሳይሆን ከመለያየትና ከፍቅር መቀዝቀዝ የተነሣ ሐሰተኛ መንፈስ ክርስቲያኖችን እንደሚያሳ ስት (በክርስቶስ ስም)፤ በዚህ በመጨ ረሻ ዘመን ይነሣሉ የተባሉትም እውነ ተኞች መምህራን ሳይሆኑ ሐሰተ ኞች፥ እውነተኞች ነቢያት ሳይሆኑ ውሸተኞች በስሙ የሚያደርጉት ምልክትና ተአምራትም ማሳሳቻ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ የሚያታልሉበት የክፉ መንፈስ ተንኮል እንደሆነ ነው የተነገረን። እነዚህ ሰዎች በጌታ ዳግም ምፅአትና በፍርድ ቀን ተስፋ የሚያስቆርጥ አስደንጋጭ የመለኮት ቃል እንደሚ ሰሙ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል:-

«በዚያ ቀን ብዙዎች ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢት አልተ ናገርንምን? በስምህ አጋንንትን አላወ ጣንምን? በስምህስ ብዙ ተአምራት አላደረግንምን? ይሉኛል። የዚያን ጊዜም ከቶ አላውቃችሁም እናንተ አመፀኞች ከእኔ ራቁ ብየ እመሰክርባቸዋለሁ» ይላል። ማቴ. 7፥22–23።

በናዝሬቱ ጌታ በኢየሱስ ስም በማለት ይህን ሁሉ ተአምራት ሲያደ ርጉ ቆይተው ለምን አመፀኞች ተባሉ የሚል ጠያቂ ይኖራል። አመፅ ማለት ትእዛዙን አለማክበር ነው። እነዚህ ሰዎች የመጀመሪያ ትእዛዙን አላከበ ሩምና ከትእዛዙም የመጀመሪያው እንዲህ የሚል ነው። «እኔ እንደወ ደድኳችሁ እርስ በእርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት» ዮሐ.15፥12። ይህ ትእዛዝ አልተከበ ረም እርስ በእርስ መዋደድ የለምና። እርስ በርስ መዋደድ ቢኖር ኖሮ እንደዚህ መለያየትና ቁጥር ሥፍር የሌለው ድርጅት አይፈጠርም ነበር። በአጠቃላይ በመጨረሻው ዘመን እውነተኞች መምህራን፥ እውነተኞች ነቢያት ይነሣሉ ተብሎ በወንጌሉ ቢነገረን ኖሮ፥ በዚህ ዘመን እውነተ ኞች ክርስቲያኖች እኛ ነን መንፈስ እየፈሰሰልን በልሳን እንናገራለን የሚሉትን ሁሉ በምስጋና በተቀበል ናቸው ነበር። ነገር ግን በየጊዜው የማሳሳቻ መንፈስ እየተሸከሙ የሚመ ጡትን ሁሉ የምንቀበልበት እጅ፥ የምናዝልበት ጀርባ የለንምና ስለእግ ዚአብሔር ብላችሁ ተሳስታችሁ አታሳስቱ እንላለን።



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

## ማጠቃለያ

መንፈስ ቅዱስ ለሐዋርያት የልሳንን (የቋንቋን) ጸጋ የሰጠበት ምክንያት ሐዋርያት በዓለም ተዘዋውረው ሲያስተምሩና ወንጌልን ሲያስፋፉ የቋንቋ ችግር እንዳይገጥማቸውና የወንጌሉ ትምህርት በፍጥነት እንዲስፋፋ ነው። እውነትም ወንጌሉ ፈጥኖ በዓለም እንዲስፋፋ የቋንቋ መገለጥ ታላቅ አስተዋጽኦ አድርጓል። የሐዋ.10፥44–47። የሐዋ.11–15። ቅዱስ ጳውሎስም በነበረበት ዘመን የነበረው ልሳን ሰው የሚናገረው፥ ሰው የሚሰማው የሚተረጐም ነው። የአሁኑ ዘመን ልሳን ግን ማንም የማይሰማው በዓለም ካሉት ሰዎች አንድ እንኳ ተነሥቶ የእኔ ቋንቋ ነው ብሎ የማይመሰክርለት ትርጉም የለሽ የውሸት ቋንቋ ነው። ስለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው።

በዚህ ዘመን በልሳን እንናገራለን የሚሉ ሁሉ እንደዋሸንትና ክራር የመሳሰሉት ነፍስ የሌላቸው መሣሪያዎች የመዝሙርን ምሥጢር የሚገልጡትን ያህል የማይገልጥና ትርጉም የለሽ በሆነ ከንቱ መለፍለፍ ተታልለው ከሚደክሙ እውነትን በመፈለግ ራሳቸውን እንዲያርሙና በዚህ ጉዳይ በእጅጉ እንዳያስቡበት በእግዚአብሔር ስም አደራ እንደላለን።

እንግዲህ የተሳሳትን ስህተታችንን አርመን ምግባራችን የተበላሸብን ከተበላሸው ምግባራችን በንስሐ ተመልሰን እረኛው አንድ መንጋውም አንድ የሚሆንበት ጊዜ አለ ይላልና። በአንዲት ጥምቀት፥ በአንድ እምነት፥ በአንዲት ቤተክርስቲያን ተመርተን፤ ስለ በደላችን የሞተውንና የተነሣውን፥ በክብር ያረገውንና አሁምን ከእኛ ጋር ያለውን አምላክ ፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስን በአንድ ልብ በአንድ ቃል በማመስገን የሚመጣውን ተስፋ ወራሾች ለመሆን ያብቃን አሜን። ✣

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

# እመ አምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ

ዘፍጥ.8፥6–12። መኃ.2፥14

በዲ.ተክለ ጻድቅ

ከፍ ብሎ የተጠቀሰው የመጽሐፍ ክፍል በጥፋት ውኃ ዘመን ደጉ የእግዚአብሔር ሰው ኖኅ ውኃው ከምድር ላይ መጉደሉንና በሰላም መኖር ይቻል እንደሆነ ለማወቅ በፈለገ ጊዜ በመርከቢቱ ውስጥ ከነበሩት አእዋፍ መካከል ቁራን ወደምድር እንደላከውና ቁራው ግን–ውኃው እስከደረቀ ድረስ በዚያው መቅረቱን ያስረዳናል። ከዚህ በኋላም ኖኅ ርግብን ከመርከቡ አውጥቶ በመስኮት እንደሰደዳትና ማረፊያ በማጣቷ ተመልሳ ብትመጣ ለሌላ ሰባት ቀናት ቆይቶ ዳግመኛ ቢሰዳት በሠርክ በአፏ የለመለመ የወይራ ቅጠል ይዛ መመለሷን ከዚህም የተነሣ ኖኅ በምድር የጥፋት ውኃ መቅለሉን ዐውቆ ሰላማዊ ኑሮውን እንደጀመረ በዚሁ ክፍል ተጽፎ እናገኛለን።

ኖኅና በመርከቢቱ ውስጥ የነበሩት ሰዎች የምእመናን ምሳሌ ናቸው፤ የጥፋት ውሃውም የኃጢአት ምሳሌ፤ ከመርከቢቱ በኖኅ ተልካ የለመለመ ዝንጣፊ ይዛ የተመለሰችው ርግብ የእመቤታችን ምሳሌ ሲሆኑ ያመጣችው ዝንጣፊ የሰላም ምሳሌ ነው። የመልእክቱ መልስ ነው። ቁራው የርኩስ መንፈስ (የሰይጣንና የማይረባ አምልኮ) ምሳሌ ነው።

ከታሪኩ እንደተመለከትነው ኖኅ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በውሃ ላይ በተንሳፈፈ ጊዜ ምድር ሰላም ስለመሆኗ ተጨነቀ:- ከዚህም የተነሣ ቁራን ላከው ነገር ግን ቁራ መልእክቱን በሚገባው ለኖኅ አላመጣለትም በሄደበት ቀረ እንጂ። በኋላ የተላከችው ርግብ ግን ውሃው መጉደሉን፥ በምድር ላይ ሰላም መሆኑንና ኖኅም ከመርከቢቱ ቢወጣ ሰላማዊ ኑሮውን በምድር መቀጠል የሚችል መሆኑን የሚያበስር ምልክት ይዛ ተመለሰች:- የሰላም መልእክተኛ ሆነች፤ ኖኅንም ከጭንቀቱ አሳረፈችው – ሰላምንም ሰበከችለት።

ምእመናን በእግዚአብሔር አምልኮ በሚኖሩበት ሕይወት ዙሪያ በሰይጣን ፈተና ተጨንቀው በኃጢአት ባሕር በወደቁ ጊዜ በነፍሳቸው ሰላም አጥተው ሕይወታቸው ተስፋ ትቆርጣለች። ያን ጊዜም ከበደላቸው ብዛት የተነሣ ወደእግዚአብሔር ቀርበው መለመን ተስኗቸው፤ የሰላምንና የእረፍትን ዜና ለመስማት አብዝተው በተመኙ ጊዜ በእርግጥ የሰላም ዜና የሚያሰማቸውን መልእክተኛ ወደእግዚአብሔር መላክ ያስፈልጋቸዋል። ርኅርኅተ ህሊና የምትሆን እመቤታችን ዘወትር ስለሰዎች ልጆች ሰላማዊ ሕይወት ከልጇ ከወዳጇ ፊት ቆማ የምታማልድ ናትና እርሷን መላክ፥ ለምኝልን ማለት ያስፈልጋቸዋል፤ አማናዊቱ ርግብ እርሷ ናትና።

አማናዊቱን ርግብ ድንግል ማርያምን አማላጅ አድርገው የሚኖሩ ምእመናን የምሥራችን፥ የሰላምን ዜና ሳይሰሙ ቀርተው ተጐድተው አያውቁም። በእርሷ ምልጃ ከወደቁበት ይነሣሉ፥ ከተዘፈቁበት የኃጢአት ባሕር ሊወጡና በመልካሚቱ ምድር (ሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም) በሰላም ለመኖር ተስፋቸው ፍፁም ነው። ከዚህ በተቃራኒ ደግሞ በማይረባና በማይጠቅም አምልኮ ተጠልፈው የተያዙ አምላክያን ጣዖት የሚልኩትንም ባለማወቃቸው በተዘበራረቀውና ተስፋ በሌለበት ሕይወት የሚያሰሙት ፊር የለቀቀ ልመና ከመንበረ ጸባዖት ሳይደረስና መልስም ሳያገኝ ይቀራል።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

እነዚህ ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርቡት የሚገባውን ልመናና የሚያድናቸው ማን በማን በኩል መሆኑን ያላወቁ የምልጃ ምሥጢር ያልገባቸው ራሳቸውንና የአላዋቂ ዕውቀታቸውን ብቻ በማምለክ እግዚአብሔር ያከበራቸውን የሚንቁ «እኛም ከቅዱሳን እኩል ነን» የሚሉ ከቅዱሳን በረከት ለመሳተፍ ያልታደሉ ናቸው።

እንግዲህ በሁላችንም ዘንድ እንደሚታወቀው በሰው ውድቀት አማካኝነት በሆነው ምልዓተ ኃጢአት የተነሣ የአዳም ዘር ሁሉ የሰላም ባለቤት ከሆነው አምላኩ ተለይቶ የዲያብሎስ ቁራኛና ተገዥ ሆኖ ለዘመናት በእግረ አጋንንት ሲጠቀጠቅ ኖሯል። በኋላ ግን ፈጣሪአችን እግዚአብሔር አስቀድሞ የገባውን ቃል በማሰብ ከቅድስት ድንግል ማርያም በነሣው ሥጋ ሰው ሆኖ ሰዎች ያጣነውን ሰላም አግኝተናል። የዚህ ሰላም ምክንያቱ ወላዲተ አምላክ ናት፤ ከራሱ ጋራ ያስታረቀን ሞትን በሞት ድል አድርጎ ሰላምን የሰጠን ከእርሷ በነሣው ሥጋ በተቀበለው መከራ ነውና። እርሷ የሰላም መገኛ–የሰላም የምሥራች ነጋሪ ሆነች። የሰው ሁሉ ዘር የዚህን የሰላምና የድኅነት የምሥራች ለመስማትና ለመዳን የታደለ ሆነ። ከዚህም የተነሣ መላእክት «በሰማያት ለእግዚአብሔር ምስጋና በምድርም ሰላም ሆነ እርሱ በሚፈቅደው» እያሉ የሰላምን ዝማሬ ዘመሩ። በዚህ ምክንያት ነው ቅድስት ድንግል ማሪያም በባሕር ላይ ትንሳፈፍ በነበረችው መርከብ ውስጥ ለነበረው ለኖኅና ለቤተሰቦቹ ሰላምን እንደአበሰረችው ርግብ ሁሉ የኃጢአት ባሕር በሆነ በዚህ ዓለም ላይ በምትንሳፈፍ ቤተክርስቲያን ውስጥ ላሉት ምእመናን የሰላም የምሥራች የተሰበከባት አማናዊት ርግብ ናት የምትባለው።

እርሷ–ወላዲተ አምላክ –ለሰው በሕይወቱ ሰላም እንዲሆንለት ዘወትር ከመጨነቅና ከልጇ ከወዳጇ ዘንድ ከማማለድ አርፋ የማታውቅ ርኅርኅት እናት ናትና ዘወትር አማላጅነቷን በመታመን ወደ እግዚአብሔር አማልጂን ብለው ለሚልኳት የሰላምን የምሥራች የምታበስር ሰላማዊት መሆኗን የቀመሰ ሁሉ ያውቀዋል።

ዛሬም ቢሆን ዓለም ወደ እግዚአብሔር ማንን መላክ እንደሚገባው ገና አላስተዋለም። ሰላም መገኛዋ የት እንደሆነ– ፍለጋዋም ወዴት እንደሚገኝ አላወቀም። እውነተኛውን ሰላም ሊስብክለት የሚችል – ይህንንም ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ሰላም ለማምጣት ኃይሉ የማን እንደሆነ አላወቀም፤ ቢያውቅም ከእግዚአብሔር እግር ሥር ራሱን በትህትና አዋርዶ የቅዱሳንን ምልጃ በተለይም የወላዲተ አምላክን ልምና ተስፋ ከማድረግ ይልቅ በገዛ ራሱ ፍልስፍናና የዚህ ዓለም በሆነ ከንቱ ዕውቀት መዳንን – ሕይወትን አገኛለሁ መስሎት በማንነቱ በመመካት ከሰላምና የሰላም ባለቤት ከሆነው አምላኩ ተለይቶ ይታያል። ይህ ትምክህትና ትዕቢት ግን ፍቅር አልባና ከእምነት የተለየ ሥጋዊ በመሆኑ ውጤት የለውም። የዓለም ወገን የሆነ ሁሉ በማይረባ አምልኮ የተሞላው ልቡናው ካልነጻ ከእግዚአብሔር የሚያስታርቀው መልእክተኛ ማን እንደሆነ ሊገለጥለት አይችልም። ስለዚህ ልብን አንጽቶ ሰውነትን ከክፉ ሃሳብና ሥራ ለይቶ ለእግዚአብሔር መሆን ያስፈልጋል። ሰው በልቡ ንጹሕ በሃሳቡ ቀና ያልሆነ እንደሆነ ከፈጣሪው ጋራ የሚገናኝበትን መንገድ ሊያውቅ አይችልም። እንዲህ ከሆነ ደግሞ የአዳም ዘር ሁሉ ልቡን ወደፈጣሪው መልሶ ትከሻውን በትህትና ለንስሐ አመቻችቶ ማቅረብና የሚላክለትና የሚያስታርቀው ማን፤ አማናዊ የሰላም የምሥራች የሚያሰማው ማን መሆኑን በአንክሮ መገንዘብና ማወቅም የገባዋል።

በዚህ ትምህርት መሠረት ኖኅ በላካት ርግብ የተመሰለችው አማናዊቱ ርግብ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በመሆኗ እርሷን ከፍጹም እምነት ጋር ወደፈጣሪአችን እንድታማልደን ብንጠይቅ በችግራችን ሁሉና በጭንቀታችን ጊዜ መፍትሔ ለጥያቄአችን ደግሞ ደገኛ መልስ እናገኛለን። በክርስትና ሕይወት ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅና የእግዚአብሔር ለመሆን የመጀመሪያው እርምጃ በሔዋን ስህተት የወደቀውና ሞት የተፈረደበት ሰው በድንግል ማርያም አማካኝነት ሕያው መሆኑን፤ በሔዋን ምክንያት የተዘጋው የገነት በር በድንግል ማርያም አማካኝነት መከፈቱን በፍጹም ልብ ማመን ነው። ይህን በመሰለ ልባዊ እምነት ለሚኖር ሰው እመቤታችንን አማልጂኝ ማለት ቅንጣት ታክል እንኳ የሚከብደው አይሆንም፥ በኃጢአቱ ብዛት ከእግዚአብሔር ፊት መቆም ለማይቻለው ሰባራ ልቡናው ምርኩዝ የምትሆነውና ከአምላኩ የምታስታርቀው ሰላማዊት እናቱ በመሆኗ ተስፋው በእርሷ አማላጅነት ይጸናል እንጂ። ከእርሷ በተነሣው ሥጋ ምክንያት በመንፀፈደይን ወድቆ በእግረ አጋንንት ሲጠቀጠቅ ለነበረው አዳም አዲስ የምሥራች እንደተሰበከለት የሚያውቅ በመሆኑም በአለበት ሥፍራ ሁሉ ሆኖ «ሰአሊ ለነ ቅድስት – ቅድስት ሆይ ለምኝልን» ይላታል። ሰላምን የሚሰጥ የሰላም ባለቤት ወደሆነው ልጇ ወደ መድኅኔዓለም ክርስቶስ ይልካታል ፊት በማያስመልስ አንገት በማያስቀልስ ልመናዋ እንድታማልደው። እርሷም ከልጇ ከወዳጇ አማልዳ ሰላምን ይዛለት ትመጣለች።

ብዙ የተቸገሩና የተጨነቁ በእርሷ አማላጅነት ከጭንቀታቸው አርፈዋል፥ ከፈጣሪአቸው ታርቀው ሰላም ሆኖላቸዋል፥ ለተስፋይቱ ምድር ለመንግሥተ ሰማይ በቅተዋል። ይህን አብነት አድርገን በወላዲተ አምላክ አማላጅነት ልንጠቀም የሚገባን እኛ ነን፤ የዘመኑ ሰዎች። በአማላጅነቷ ታምኖ ማን አልዳነም? እንግዲህ እንዳንሞኝ፤ በዘመናችን በቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት ማመንና መማጸን ሞኝነት ለሚመስላቸውና ይህንኑ አመለካከታቸውን የሚዘሩበት የሚፈልጉ ጊዜ የፈጠራቸው የሐሰት መምህራን እጅግ በዝተዋልና ምእመናን በሃይማኖት ልንጸና የአበውን ትምህርት ልናጸና ያስፈልገናል። ✥

ወላዲተ አምላክ በአማላጅነቷ አትለየን

አሜን



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

# ሰሙነ ሕማማት

ዲ.ሐብተወልድ

በዐቢይ ጾም ከሠርከ ሆሣዕና ጀምሮ እስከ ትንሣኤ ሌሊት ያሉት ዕለታት የሚገኙበት ሳምንት ሰሙነ ሕማማት ይባላል። ዕለታቱም የዓመተ ፍዳ፥ የዓመተ ኩነኔ መታሰቢያ ናቸው። ዓመተ ፍዳ፥ ዓመተ ኩነኔ የሚባለው የሰው ልጅ በሲኦል ባርነት፥ በዲያ ብሎስ ቁራኝነት ተይዞ የኖረበት የመከራ ዘመን ነው። ሰሙነ ሕማማትም የሕማማት ሳምንት ማለት ነው። ሰሙን የሚለው ቃል «ሰመነ» ስምንት አደረገ ከሚለው የግሥ ዘር የወጣ ነው። ሕማማት የሚለው ቃል ብዛትን የሚያ መለክት ሆኖ «ሐመ» ታመመ ከሚለው የግሥ ዘር የተገኘ ነው።

ሕማም ሲባል ሰው ሰውኛውን ለእኛ የሚሰማን ዓይነት ሕመም ማለትም የራስ ምታት፥ የሆድ ቁርጠት፥ የእጅ የእግር ቁርጥማት ሳይሆን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስ ቶስ የሰውን ዘር ሁሉ ከዲያብሎስ ቁራኝነት ለማላቀቅና ከሲኦል ባርነት ነፃ ለማውጣት ወዶ ፈቅዶ የተቀበላቸውን ጸዋትወ መከራ የሚያመለክት ነው።

በእነዚህ ዕለታት ውስጥ ማለትም በሰሙነ ሕማማት ብዙ አዝማደ መባልዕት አይበሉም። እጅግ አብዝቶ ስግደት ይሰገዳል፥ የጌታችንን የአምላካችንን የኢየሱስ ክርስቶስን መከራ ሞት የሚያስታውሱ ምንባባት ከቅዱሳት መጻሕፍት ሲነበቡ ይሰነብታሉ። ከወትሮው በተለየ ሁኔታ መከራ መስቀሉ ይዘከራል። ከእሁድ ሠርክ የተጀመረው የአይሁድ ምክራቸው የጸናላቸው ረቡዕ ነው። የሚቀጥለው ሐሙስም የጸሎት ሐሙስ ይባላል። ጌታ በፍጹም ትህትና የደቀመዛሙርቱን እግር ያጠበበት ከሐዋርያት ጋር ግብር ያገባበትና የክርስትና ሕይወት ማኅተም የሆነውን ምሥጢረ ቁርባን የመሠረተበት ዕለት ነው።

ይህች ዕለት ለደቀመዛሙርቱ ከእናንተ አንዱ ለሞት አሳልፎ ይሰጠኛል ያለባት፥ የሚወደው ደቀመዝሙር ዮሐንስም ወደ ጌታ ተጠግቶ አሳልፎ የሚሰጠው ማን መሆኑን በመጠየቅ ምልክት ያገኘ ባት፥ በጌቴ ሴማኒ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ ብሎ ደጋግሞ በመጸለይ በፈተና ጊዜ ጸሎት እንደሚገባ ያስተማረባት፥ ከፊቱም ልዩ የሆነና በምድር ላይ እንደ ደም የሚንጠባጠብ ወዝ የወረደባት ዕለት ናት። በመጨረሻም ይሁዳን የሰ ውን ልጅ በመሳም አሳልፈህ ትሰጣለ ህን ብሎ የተናገረባት፥ በቅዱስ ጴጥሮስ ሰይፍ የተቆረጠውን የማል ኮስ ጆሮ የፈወሰባት፥ ደቀመዝሙሩ ንም ሠይፍን የሚያነሱ በሠይፍ ይጠፋ ሉና ሠይፍህን ወደ አፎቱ መልስ ብሎ ያዘዘባት፥ እንደወንበዴ ሊይዙት የመጡትን በቃሉ ብቻ በምድር ላይ ያፍገመገመባት፥ በፈቃዱም ለአይ ሁድ አልፎ የተሰጠባት ዕለት ናት።

ለዚህ ሁሉ መታሰቢያ በዕለተ ሐሙስ ቄሱ ውሃውን በብርት አድርጎ በጌታ ምሳሌ አስቀድሞ የካህናትን በኋላም የምእመናንን እግር በቅደም ተከተል ያጥባል። ዛሬ ግን የወላጆቹን





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

እግር የሚያጥብ እንኳ ልጅ የለም። ይህ ብቻ ሳይሆን ለልጁ ይህን ታላቅ ትምህርተ ትሕትና የሚያስተምር ወላጅም በቁጥር ነው። ቅዱስ ጴጥሮስ እኔ እግርህን ካላጠብኩህ በቀር ከእኔ ጋር አንድነት የለህም በመባሉ ጌታ ሆይ እንዲህስ ከሆነ እግሬን ብቻ ሳይሆን መላ ሰውነቴን እጠበኝ ብሎ ለመታጠብ ቀረበ። ታጠበም። እኛም ከኃጢአት ቆሻሻ ለመንጻት ከበደል እድፍ በንስሐ ለመታጠብ በእምነት መቅረብ፥ በጸጸት እንባ መታጠብ ያስፈልገናል፤ ከጌታችን አንድነት እንዳንለይ።

ደቀ መዛሙርቱን እግራቸውን ካጠባቸው በኋላ አቅረባቸው ሥጋውን ደሙን ሰጣቸው። እንግዲህ ከንስሐ በኋላ እኛም ሥጋውን ደሙን መቀበል ይኖርብናል፥ የሕይወት ሰዎች መሆን ይገባናል። ደቀመዛሙርቱ ሁላችሁ ከዚህ ብሉ ጠጡ በተባሉ ጊዜ አንዳቸውም ሳይቀሩ በሉ ጠጡ። ዛሬም በክርስቶስ ክርስቲያን በወልድ ውሉድ የተባልን ሁላችን ለዚህ ታላቅ ምሥጢር ተጠርተናልና ሥጋውን ደሙን እንቀበል። ይህን የጌታን ጥሪ ብንፈጽም ከአምላካችን ጋር ዘለዓለማዊ አንድነት ይኖረናል።

በበነጋው ዓርብ ጌታችን የተሰቀለበት ዕለት በመሆኑ ለስቅለቱ መታሰቢያ አጎበር ተዘርግቶ ስቅለትን የሚመለከቱ ምንባባት ሲነበቡና ሲሰገድ ይዋላል። ሠርክ ሲሆን እያንዳንዱ ምእመን ወደ ቄሱ እየቀረበ በሰሙነ ሕማማት የሠራውን ኃጢአት ይናዘዛል፤ ቄሱም በወይራ ቅጠል እየጠበጠበ ቀን ከሰገደው ሌላ ስግደት ይሰጠዋል፤ በአሥራ ሁለት ሰዓትም ሠርሆተ ሕዝብ (የሕዝብ ስንብት) ይሆናል።

በቤተ ክርስቲያናችን እመቤታችን፥ ያዕቆብና ዮሐንስ የጌታን ትንሣኤ ሳናይ እህል ውሃ አንቀምስም ብለው እስከትንሣኤ መቆየታቸው ይነገራል። ዛሬም በሀገራችን ብዙ ሰዎች ይህን አብነት አድርገው ከሐሙስ ማታ እስከ ትንሣኤ ሌሊት የሚያከፍሉ አሉ። ይህ የማይቻላቸው ግን ዓርብ ማታ ትንሽ ቀማምሰው እስከ ትንሣኤ ይቆያሉ። ሁለት ቀን ማክፈል እንኳ ቢከብድ ቅዳሜን ማክፈል ተገቢ ነው። ቅዳሴው በመንፈቀ ሌሊት ስለሆነ በልቶ ማስቀደስ በልቶ መቁረብ እንዳይሆን።

በሰሙነ ሕማማት ክርስቶስን ይበልጥ በዓይናችን ፊት እንደተሰቀለ ሆኖ እናየዋለን ገላትያ 3፥1። የእግዚአብሔር ሰዎች በጆሮዎቻቸው የሰሙትን ሁሉ በእምነት በዓይነ ልቡናቸው ይመለከቱታል፥ ትልቁ ነገር ይህ ነው። በዓይን ለማየት መቻል። ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት «እግዚአብሔርን ሁል ጊዜ በፊቴ አየዋለሁ» ማለቱ ለዚህ ነው። መከራን በትዕግሥት ያሸነፈ ኢዮብ «መስማትንስ በጆሮ ሰምቼ ነበር፤ አሁን ግን ዓይኔ አየችህ ስለዚህ ራሴን እንቃለሁ፤ በአመድ ላይ ተቀምጬ እፀፀታለሁ። «ኢዮብ.42፥5። እንዳለው እኛም ከወትሮው በተለየ ሁኔታ መከራ መስቀሉን እያሰብን፥ ክርስቶስን በእምነት እያየን፥ የፈፀመልንን ቤዛነት የዋለልንን ውለታ ዘንግተን በደም መገዛታችንን አቃልለን፥ በኃጢአት ወድቀን እንደ ውሻ ወደ ተሸነፈልን ኃጢአት ቀድሞ ወደገዛን ጠላት በመመለሳችን፤ እንደ እርያ ታጥቦ ጭቃ በመሆናችን ራሳችንን እንንቃለን።

በጾም በጸሎት ሰውነታችንን በአምላካችን ፊት አዋርደን እንፀፀታለን። አመድ ነስንሰን ማቅ ለብሰን፥ 1. መከራ መስቀሉን

2. ቅዱሳን በከሃዲያን ፊት የተቀበሉትን መከራ

3. እንደ አዳም፥ ዳዊትና ቅዱስ ጴጥሮስ ኃጢአታችንን እያሰብን እናለቅሳለን።

በሰሙነ ሕማማት ጠቅለል ባለ መልኩ የምናስባቸው የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሕማማት አሥራ ሦስት ናቸው። እነርሱም አሥራ ሦስቱ ሕማማተ መስቀል ይባላሉ። ለክርስቲያኖች እነዚህን ሕማማተ መስቀል ማወቅና ዘወትር ማሰብ ተገቢ በመሆኑ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ሀ. ተኰርዖተ ርእስ፤ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን በዘንግ መመታቱንና መቀጥቀጡን የሚገልጥ ነው። «ተኰርዖት» የሚለው ቃል ኰርዐ—መታ ከሚለው የግእዝ ግሥ የተገኘ ነው። ርእስ ደግሞ ራስ ማለት ነው። አገረ ገዥው ጲላጦስ «እኔ ከዚህ ጻድቅ ሰው ደም ንጹሕ ነኝ» ብሎ እጁን ከታጠበ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ገርፎ ለካህናት አለቆችና ለሸማግሎች አሳልፎ ሰጥቶት ነበር። በአይሁድ ሕግ የተገረፈ አይሰቀልም፥ የሚሰቀል ደግሞ አይገረፍም። እርሱ ጲላጦስ ግን ከገረፈው በኋላ የበደል በደል እንዲሰቅሉት አሳልፎ ሰጣቸው ማቴ.27፥24። ማር.15፥15። ሉቃ.23፥25። ዮሐ.18፥39።


መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተላልፎ ከተሰጠ በኋላ የእሾህ አክሊል ጐንጉነው በራሱ ላይ ደፍተውበታል። ራሱንም በዘንግ መትተውታል። ማር.15፥19። የሰው ዘር ከአዳም ጀምሮ በጠላቱ በዲያብሎስ በተጐነጐነ የኃጢአት እሾህ ራሱ ተይዞ ነበርና ይህኑ ለማስወገድ ከሰማይ የወረደ ሰማያዊ የሆነ ዳግማዊ አዳም ክርስቶስ በጠላቶቹ በአይሁድ ተንኮል የተጐነጐነ አክሊለ ሦክ እንደ ዘውድ ደፋ። በሲኦል ወድቆ በዲያብሎስ ተረግጦ ራሱ የሚቀጠቀጠውን የሰው ልጅ ለማዳን መድኃኔዓለም ክርስቶስ ራሱን በመቃ ተቀጠቀጠ። ከራሱ ላይ በሚወርደውም ደም ፊቱ ተሸፈነ።

ለ. ተፀፍዖ መልታሕት፤ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ እጃቸው በደም





©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org



ጣቶቻቸው በበደል በረከሰ በአይሁድ እጅ በጥፊ መመታቱን የሚገልጥ ነው። ‹ተፀፍዖ› የሚለው ቃል ፀፍዐ በጥፊ መታ ከሚለው የግዕዝ ግሥ የወጣ ነው። መልታሕት ደግሞ ፊት ጉንጭ ማለት ነው።

ጌታችን ለሊቀ ካህናት ቀያፋ እውነትን በመናገሩ እንደ ስድብ ተቆጥሮበት መላልሰው ፊቱን በጥፊ መትተውታል። ፊቱንም በጨርቅ ሸፍነው «ክርስቶስ ሆይ በጥፊ የመታህ ማነው? ትንቢት ተናገርልን» እያሉ ዘብተውበታል። በጠላት ዲያብሎስ እጅ ወድቆ በነፍሱ ይቀለድበትና ይንገላታ የነበረውን የሰው ልጅ ለማዳን ብሎ በጠላቶቹ በአይሁድ እጅ ወድቆ ተጎሰመ፥ ተንገላታ፥ በጥፊም ተመታ። ማቴ.27፥27። ጲላጦስ አሳልፎ ከሰጠው በኋላም አክሊለ ሦክ በራሱ ላይ አኑረው ቀይ ልብስ አልብሰው «የአይሁድ ንጉሥ ሆይ ሰላም ለአንተ ይሁን» እያሉ እየተሳለቁበት በጥፊ መትተውታል። ዮሐ. 19፥2–4። አላወቁትም እንጂ እርሱ በመንግሥቱ ሽረት በባህርዩ ሞት የሌለበት የዘለዓለም አምላክ ነው።

ሐ. ወሪቀ ምራቅ፤ ርኩሳን አይሁድ በብርሃናዊው የክርስቶስ ፊት ላይ በሚያስጸይፍ ሁኔታ ምራቃቸውን እንደተፉበት የሚገልጥ ነው። «ወሪቅ» የሚለው ቃል ወረቀ ካለው ግእዛዊ ግሥ የተገኘ ነው። ትርጉሙም እንትፍ አለ (ተፋ) ማለት ነው። በነቢዩ በኢሳይያስ ምዕራፍ 50፥6። «ፊቴንም ከውርደትና ከትፋት አልመለስኩም» ተብሎ እንደተነገረ እየዘበቱበት ምራቃቸውን ተፉበት። ማቴ.27፥29–30። ማር.15፥19። በኃጢአት የቆሸሸውን የሰው ሕይወት ለማጥራት ተተፋበት። በሥራው ከገነት ተተፍቶ፥ ተንቆ፥ ተዋርዶ የነበረውን የሰው ልጅ ለማዳን ኃጢአትን ይቅር የሚል ሲሆን እርሱ ጌታችን ያለኃጢአቱ ተተፋበት፥ ተናቀ፥ ተዋረደ። እንኳን በአምላክ ፊት በሰው እንኳን ፊት መትፋት እጅግ ያስነውራል። እርሱ ግን የኃጢአታችንን ነውር ከእኛ ሊያጠፋ ነውር የሆነውን ምራቅ ተቀበለ።


መ. ሰትየ ሐሞት፤ የጌታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመልዕልተ መስቀል ሳለ ተጠማሁ ባለ ጊዜ መራራ ሐሞት መጠጣቱን የሚገልጥ ነው። «ሰተየ» ማለት ጠጣ ማለት ነው። ሐሞት የሚለውም አሞት ተብሎ በቁሙ ይተረጐማል። በመዝ. 68፥21። «ለመብሌ ሐሞት ሰጡኝ ለጥማቴም ሆምጣጤ አጠጡኝ» ብሎ ነቢዩ ዳዊትን ትንቢት ያናገረ የነቢያት አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ የመጽሐፉ ቃል ይፈጸም ዘንድ ተጠማሁ ባለ ጊዜ ሆምጣጤ ተሞልቶበት ተቀምጦ ከነበረው ዕቃ ሆምጣጤውን በሰፍነግ ሞልተው ወደአፉ አቀረቡለት። ውኃ አጠጡኝ ቢላቸው በሐሞት የተደባለቀ የወይን ጠጅ ሊጠጣ አቀረቡለት ቀምሶም ሊጠጣው አልወደደም። ማቴ.27፥34። ጌታችንም ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ ተፈጸመ አለ። ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ፤ ማቴ. 27፥48። ማር.15፥36። ሉቃ.23፥36። ዮሐ.19፥29።

ቢጠጡት ለዘለዓለም የማያስጠማ ውኃ የሚሰጥ አምላክ፥ የተጠማችውን ነፍስ የሚያረካ ጌታ፥ ለዘለዓለም የሚፈልቅ የሕይወት ውኃ ምንጭ የሚያድል ፈጣሪ በተጠማ ጊዜ የፈጠረውን ውኃ እንኳን የሚያጠጣው የሚያቀምሰውም አላገኘም። ኢሳ.55፥1። አርባ ዓመት ሙሉ በቃዴስ በረሃ ኳትነው ለነበሩ አባቶቻቸው ከሰማይ አውርዶ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

መብልን የመገባቸው፥ ከአለት አመን ጭቶ መጠጥን ያጠጣቸው ክርስቶስ



በተጠማ ጊዜ ቀዝቃዛ ውኃ ነፈጉት። ዘጸ.16፥1–20። 1ቆሮ.10፥3። የዝናማት፥ የባሕርና የውቅያኖስ ጌታ በውኃ ጥም ተቃጠለ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሲኦል በረሃ ወድቀው በሕይወት ውሃ ጥም የተቃጠሉትን ነፍሳት ለማርካት ሲል እርሱ ተጠማ። በኃጢአት ወድቀው፥ በበደል ረክሰው በነፍሳቸው ተጐሳቁለው መራራ መከራን የሚቀበሉትንና ምረረ ገሃነም አፉን ከፍቶ ሆዱን አስፍቶ የሚጠብቃቸውን ሁሉ ለማዳን መራራ ሐሞትን ቀመሰ፥ ሆምጣጣውንም ጠጣ። የመረረውን የሰው ልጆችን ሕይወት ለማጣፈጥ የመረረውን መጠጥ ተቀበለ።

ሠ. ተቀሥፎ ዘባን፤ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጀርባው እስኪላጥ ያለርኅራኄ የመገረፉን ነገር የሚገልጥ ነው። «ተቀሥፎ» የሚለው ቃል ቀሠፈ–ገረፈ ካለው የግእዝ ግሥ የተገኘ ነው። «ዘባን» ደግሞ ጫንቃ፥ ትከሻ ጀርባ ማለት ነው። ከላይ እንደተገለጠው የተገረፈ አይሰቀልም። የሚሰቀል ደግሞ አይገረፍም ነበር። ጲላጦስ ግን ኢየሱስ ክርስቶስን አስገረፈው። ከደሙ ንጹሕ ነኝ ብሎ ከታጠበ በኋላ ክርስቶስን ያለኃጢአቱ በመግረፍ ለአይሁድም አሳልፎ በመስጠት «ታጥቦ ጭቃ» እንዲሉ የታጠበ እጁን መልሶ አቆሸሸው። ማቴ.27፥26። ማር.15፥15። ዮሐ.19፥1። መንፀፈ ደይን ወድቆ በእግረ አጋንንት ተጠቅጥቆ በእሳት አለንጋ የሚገረፈውን የሰው ልጅ ለማዳን ሲል ጀርባውን ለግርፋት ሰጠ። ሥጋው አልቆ አጥንቱ እስኪቆጠር ተገረፈ። አይሁድ አገረገዥያቸው ጲላጦስ ላቀረበላቸው ምርጫ ነፍሳትን ከሲኦል የሚያወጣውን ክርስቶስን ሳይሆን ራሱን እንኳ ከምድራዊ ወህኒ ማውጣት ያልቻለውን ወንበዴው በርባንን መረጡ ይፈታላቸው ዘንድ። መገረፍ ይገባው የነበረ በርባን ተለቀቀ። በኢሳ. 50፥6 «ጀርባዬን ለገራፊዎች ጉንጬንም ለጠጉር ነጪዎች ሰጠሁ» ተብሎ እንደነተነገረ ጌታም ጀርባውን ለገራፊዎች አሳልፎ ሰጠ፥ ጽህሙንም ተነጨ ይህ ሁሉ በዚያን ዘመን የሰው ልጅ ከሚያድነው አምላክ ይልቅ የሚገርፈውን፥ የሚዘርፈውን ወንበዴ መርጦ ስለተገኘ ነው።

ረ. ተዐርቆተ ልብስ፤ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ልብሱን መራቆቱን የሚገልጥ ነው። «ተዐርቆተ» ታረዘ፥ ተራቆተ ማለት ነው። ፀሐይና ከዋክብትን ብርሃን አልብሶ የፈጠረ አምላክ ተራቆተ። ጸጋውን ለዕሩቃን የሚያለብስ አምላክ ተገፈፈ። ተገፍፎ ዕራቁቱን ቆመ። ጨለማን ለብሶ ጨለማን ተንተርሶ ይኖር የነበረውን ሰው መልሶ ብርሃን ያለብሰው ዘንድ የብርሃናት ጌታ የጸጋ ሁሉ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ተገፈፈ፥ ተራቆተ።

ጲላጦስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን አሳልፎ በሰጣቸው ሰዓት ወታደሮች ልብሱን ገፍፈውታል። ማቴ.27፥27። የሲኦል ወታደሮች የሆኑ አጋንንት የሰውን ልጅ ጸጋ ገፍፈውት ነበርና ከፍ ብለን እንደጠቀስነው የሰው ልጅ ለቀረበለት ምርጫ የሰጠው ምላሽ ዘራፊው፥ ገራፊው ወንበዴ በርባን እንዲፈታለት ነበር። «አቀረብኩ ለከ እሳተ ወማየ ደይ እዴከ ኀበ ዘፈቀድከ! እነሆ እሳትና ውኃን አቅርቤልሃለሁ እጅህን



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ወደፈቀድከው ስደድ» ሲባል የሰው ልጅ እጁን ወደ እሳት ሰደደ።

ሰ. ርግዘተ ገቦ፤ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ከሰጠ በኋላ ጎኑን በስለታም ጦር መወጋቱን የሚገልጥ ነው። «ርግዘት» የሚለው ቃል ረገዘ–ወጋ ከተሰኘ የግእዝ ግሥ የወጣ ነው። ገቦ ማለት ደግሞ ጎን ማለት ነው። ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ አጠገብ (በግራና በቀኙ) ሁለት ወንበዴዎች ተሰቅለው ነበር። ሥጋቸው በሰንበት በመስቀል ላይ እንዳይኖር ጭናቸው ተሰብሮ እንዲወርዱ አይሁድ ጲላጦስን በለመኑት መሠረት ጭፍሮቹ የሁለቱን ወንበዴዎች ጭን ጭናቸውን ከሰበሩ በኋላ ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ ሲመጡ ፈጽሞ እንደሞተ አይተው ጭኑን አልሰበሩም። ነገር ግን ከጭፍሮቹ አንዱ ጎኑን በጦር ስለወጋው ወዲያው ከጎኑ ደምና ውኃ ፈሰሰ። ዮሐ.19፥33።

አምላካችን ኢየሱስ ክረስቶስ ሞትን ድል ያደረገው ዘንድ ሞተ የሰው ልጅ በዘለዓለማዊ ሞት ተይዞ ነበርና። ትልቁ ሞት በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር መለየት ነው። በጌታችን ሞት ሞት ድል ተነሣ። የሞት መውጊያ በሆነ ኃጢአት የሞተውን ሰው ለማዳን ጎኑን በጦር ተወጋ። በሰው ልቡና ተተክሎ የነበረውን ኃጢአት ከነሥሩ ነቅሎ ስለጣለው ሞት ሆይ መውጊያህ የት አለ? ተባለ። የሞት መውጊያው ኃጢአት ነበርና። 1ቆሮ.15፥54–55። ኢሳ.25፥8። ሆሴ.13፥14።

ከተወጋው የጌታችን ጎን ደምና ውኃ መፍሰሱም የእግዚአብሔርን ልጅነትና የዘለዓለምን ሕይወት አጥቶ የነበረው ሰው ልጅነቱና ሕይወቱ እንደተመለሰለት የሚያረጋግጥ ነው። ምክንያቱም ከጎኑ በፈሰሰው ውኃ ተጠምቆ ልጅነትን ደሙንም ጠጥቶ የዘለዓለም ሕይወትን ያገኛልና ነው። ዮሐ.3፥5። ዮሐ.6፥54።

ሸ. ተአሥሮተ ድኅሪት፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት እጆቹን ወደኋላ የፊጥኝ መታሠሩን የሚገልጥ ነው። «ተአሥሮት» የሚለው ቃል አሠረ (ሲነበብ ይላላል) ከሚለው የግእዝ ግሥ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም አሠረ (ሲነበብ ይጠብቃል) ማለት ነው። ድኅሪት የሚለው ቃል ደግሞ ተድኅረ–ወደኋላ አለ ከሚለው ግሥ የወጣ ነው። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጊዜው በደረሰ ሰዓት ራሱን ለአይሁድ አሳልፎ በሰጠባት በዚያች ዕለትና ሰዓት ሻለቃውና ጭፍሮቹ የአይሁድም ሎሌዎች እጁን የኋሊት አሥረው መሬት ለመሬት ጎትተውታል። አፍገምግመውታል። ዮሐ.18፥12።



በኃጢአት ሰንሰለት የኋሊት ታሥሮ ጠላት ዲያብሎስ የሚያፍገመግመውን የሰው ልጅ ለማዳን ሲል መድኃኔዓለም ክርስቶስ በጠላቶቹ በአይሁድ እጅ የኋሊት ታሠረ፥ ሰውንም ከኃጢአት እሥራት ይፈታ ዘንድ።

ቀ.አምሥቱ ቅንዋተ መስቀል፤ መድኃኒታችን በመስቀል ላይ የተቸነከረባቸውን ጠንካራ የብረት ችንካሮች (ምስማሮች) የሚገልጥ ነው። «ቅንዋት» የሚለው ቃል ቀነወ–ቸነከረ ከሚለው የግእዝ ግሥ የተገኘ ነው። መስቀል ማለት ደግሞ ዝም ብሎ የቆመ ግንድ ሳይሆን አሁን በየሥፍራው እንደምናየው ምልክት የተመሳቀለ እንጨት ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተቸነከረባቸው አምስቱ ችንካሮች ሳዶር፥ አላዶር፥



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ዳናት፥ አዴራ፥ ሮዳስ ይባላሉ። እንዚህም የአምሥቱ አዕማደ ምሥጢራት ምሳሌዎች መሆናቸውን አበው ያስተምራሉ።

ሐዋርያው ቶማስ ከትንሣኤ በኋላ ወንድሞቹ ሐዋርያት ስለትንሣኤው በነገሩት ጊዜ «የችንካሩን ምልክት በዓይኖቼ ካላየሁ ጣቴንም በችንካሩ ምልክት ካላስገባሁ በእጄም የተወጋውን ጎኑን ካልዳሰስኩ አላምንም ማለቱ በብረት ቀኖት በመቸንከሩ ነበር። ዮሐ.20፥25። መድኃኒታችን በኃጢአት ቀኖት ተይዞ የነበረውን ሰው ለማዳን በብረት ቀኖት ተቸነከረ።

እንግዲህ አሥራ ሦስቱ ሕማማተ መስቀል የሚባሉት እነዚህ ናቸው። ድህ ያይደለ ጌታ፥ ፍጡር ያይደለ የፈጠረውን ሥጋ ገንዘብ ያደረገ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጅ ብሎ ተናቀ። የሕማም ሰው፤ ደዌንም የሚያውቅ ሆነ። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ፤ ሕማማችንንም ተሸከመ የሰውን ልጅ ለማዳን ማለትም እኛን ከደዌ ሥጋ ከደዌ ነፍስ ይፈውሰንና ከሕማመ ሥጋ ከሕማመ ነፍስ ሥቃይ ያሳርፈን ዘንድ ነው። ቁስለ ኃጢአታችንን ያደርቅልን ዘንድ ስለመተላለፋችን ቆሰለ። በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን። በደላችንን ይደመስስ ዘንድ ስለበደላችን ደቀቀ። ሊያረጋጋን ተጨነቀ። ሊያሣርፈን ተሠቃየ። አፉንም አልከፈተም። የእግዚአብሔር የመሥዋዕቱ በግ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት በሸላቾቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ እንዲሁ አፉን አልከፈተም። መልካም እረኛ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መልካምን እንጂ ግፍን አላደረገም ነበር። ልብንና ኩላሊትን የሚመረምር አምላክ ወሰብእ ወልድ ዋህድ ኢየሱስ ክርስቶስ በጲላጦስ በተመረመረ ጊዜ በአፉም ተንኰል አልተገኘበትም።

# ሆሣዕና በአርያም

ከዲ.ክፍል ሥላሴ

ይህ («ሆሣዕና በአርያም» የሚለው) ቃል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአህያ ወርንጫ ላይ ተቀምጦ ከደብረዘይት ተራራ አካባቢ ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ በክብር ሲገባ የተነገረ ነው። ምንም እንኳ ከፈሪሳውያን አንዳንዶቹ «ሄሮድስ ሊገድልህ ይፈልጋልና ከዚህ ወጥተህ ወደ ሌላ ሥፍራ ሂድ» ቢሉትም ነቢይ ከኢየሩሳሌም ውጪ ሊጠፋ አይገባውምና ወደ ኢየሩሳሌም በቅርብ ቀናት ውስጥ መሄድ እንዳለበትና ያም ቢሆን ግን «በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው» እስከሚሉበት ቀን ድረስ እንደማያዩት አስታውቋቸው ነበር። ሉቃ.13፥31–35።

ከንባቡ እንደምናገኘው ጌታችን ወደ ኢየሩሳሌም ከመግባቱ በፊት በነቢዩ በዘካርያስ የተነገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ከደቀመዛሙርቱ ሁለቱን ልኮ ወደፊት ካለችው መንደር አህያ ከነውርንጫዋ ከታሰረችበት ፈትተው እንዲያመጡለት አደረገ።

እነርሱም ልብሳቸውን ጫኑባትና ጌታችን በላይዋ ተቀምጦ ወደ ከተማ ሲገባ ብዙ ሕዝብ ይከተለው ነበር። ከሚከተሉትም አብዛኞቹ ልብሳቸውን የቀሩትም የዛፍ ዝንጣፊ በመሬት ላይ በማንጠፍ ክብሩን፥ ገናንነቱን፥ የነቢያት ሁሉ የበላያቸው፥ አምላካቸው መሆኑን ይገልጡ ነበር። አብረውት የሚጓዙትም ክብሩን አይተው ደስ ስለተሰኙ «ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው፤ ሆሣዕና በአርያም» በማለት ድምፃቸውን በተለይም የአልዓዛርን ከሙታን መነሣት በመመልከታቸው ተደስተዋል። ዮሐ.12፥17 ና 18። ሉቃ. 19፥37።

በከተማውም የፋሲካን በዓል ለማክበር አስቀድመው ከተሰበሰቡት አይሁድ ብዙዎቹ ጌታን ሊቀበሉት የዘንባባ ዝንጣፊ የዘው ወጥተዋል። እርሱን ለመቀበል ብቻ አልነበረም ከሙታን ያስነሣውን አልዓዛርን ለማየት ጭምር ነበር እንጂ። እነርሱም በበኩላቸው አስቀድሞ ጌታችን እንደተናገረው «ሆሣዕና በጌታ ስም የሚመጣ የእሥራኤል ንጉሥ የተባረከ ነው።» በማለት ሕፃናት ሳይቀሩ እየጮኹ ማመስገናቸውን በወንጌሉ ተጽፎ እናገኛለን። ዮሐ.12፥12–15።

የኢየሩሳሌም ከተማ እስክትናወጥ ድረስ እየተዘመረለት በቀጥታ በከተማው ውስጥ ወደ አለችው ቤተመቅደስ ገባ። ከዚያም ሻጮቹን፥ ለዋጮቹን አስወጣ፤

የገንዘብ ለዋጮችንም ገበታ ገለበጠ። በአጠቃላይ ቤተመቅደሱን እነዚህን ከመሳሰሉት አላስፈላጊ ነገሮች ከአጸዳ በኋላ ቤቴ የጸሎት ቤት እንጂ የወንበዴዎች ዋሻ ልትሆን አይገባትም በማለት ለወደፊቱም አስጠንቀቃቸው።

ይህ ሁሉ ሲሆን በማየት የተበሳጩት የካህናት አለቆችና ጸፎች ሕፃናትንና ደቀመዛሙርቱን እንዳያመሰግኑት፥ እንዳይዘምሩለት እንዲከለክላቸው በቁጣ ጠይቀውት ነበር። እርሱ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በፈቃዱ ነፍሱን ስለእኛ ኃጢአት መሥዋዕት አደረገ። ፋሲካችን ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሥጋውን ቆረሰልን፤ ደሙን አፈሰሰልን። ኢሳ.53፥1–13። ዮሐ.10፥ 18፤19፥30። 1ቆሮ.5፥7። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም «ተንኰልም በአፉ አልተገኘበትም፤ ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም፤ መከራንም ሲቀበል አልዛተም፤ ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ። ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን ተሸከመ። በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ» ብሏል። 1ጴጥ.2፥22–25። ክርስቶስ የሞተልን ለጽድቅ ሞተን ለኃጢአት እንድንኖር አልነበረም፤ የኃጢአት ኑሮ እንዲያከትምልን እንጂ።

እንግዲህ የእኛ ሕያውነትስ ለጽድቅ ይሆን ወይስ ለኃጢአት? ዛሬውኑ ሕይወታችንን መለስ ብለን ልናጤነው፤ ዛሬውኑ ሥጋዊ ፍላጎታችንንና የዓይን አምሮታችንን ከደን ነፍሳችንን ለማዳን መከራ መስቀሉን ተሸክመን ሕማማቱን እያሰብን ፈጣሪአችን ክርስቶስን ልንከተለው ይገባን ነበር። ማቴ. 16፥24። እንደ ቅዱስ ጳውሎስ ትምክህታችን መስቀሉ ማለትም በመስቀሉ ላይ የተፈፀመው ቤዛነት መሆን ነበረበት።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጽኑ መከራ ማለትም በመከራ ሥጋ ላይ መከራ ነፍስ በሞተ ሥጋ ላይ ሞተ ነፍስ በርደተ መቃብር ላይ ርዳተ ገሃነም የተፈረደበትን ሰው ለማዳን ጽኑ መከራ ተቀበለ። የለበሰው ሥጋ መከራ የተፈረደበት ነበርና፥ በዕፀ ምክንያት ወደዓለም የገባውን ኃጢአት ለማስወገድ በዕፀ መስቀል ላይ ተሰቀለ። የበለሲቱ ደም ፈስሷልና ክርስቶስ ደሙን አፈሰሰ። አዳም እጁን ዘርግቶ የበለሲቱን ደም ለማፍሰስ በእግሮቹ ወደዚያ ተጓዘ። ክርስቶስ ግን በእግሮቹ ወደ ቀራንዮ ተጉዞ እጆቹን ለቀኖት ዘርግቶ የራሱን

ግን አስቀድሞ በዳዊት መዝሙር «ከሕፃናትና ከሚጠቡት አፍ ምስጋና ለራስህ አዘጋጀህ» ተብሎ የተነገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ መሆኑንና እነርሱንም ቢከለክሏቸው ድንጋዮች ጮኸው እንደሚያመሰግኑት ነግሯቸው ወደቢታንያ ወጣ። ሉቃ.19፥40።

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሰው መሆን ዋነኛ ዓላማው የሰውን ልጅ ከጠፋበት ፈልጎ ወደቀደመው ክብሩ–የገነት የክብር ባለቤትነቱ ሊመልሰው ቢሆንም የሰው ልጅ ግን እጁን ዘርግቶ አልተቀበለውም። የፈለገው ዓይነት ምድራዊ ሥልጣን ያለው ንጉሥ ወይም መሲህ አይደለምና። ጌታችን የዚህን ዓለም ደካማ ነገር በመምረጥ የዚህ ዓለም ጥበብ፥ ኃይልና ሥልጣን ሁሉ ከንቱ መሆኑን በማሳየት ሰማያዊ (ከሰማይ) የሆነውን እንዲፈልጉ አስተማረ። ለዚህም አንዱ ምስክር በአህያ ውርንጫ መቀመጡ ነው። አህያ በእኛ ዘንድ የተናቀች ናት። የተከበረ ሰው የማይቀመጥባት። ነገር ግን እርሱ ትንቢትንም ይፈጽም ዘንድ በአህያ ውርንጫ ላይ ተቀምጦ እየተዘመረለት ወደ ከተማዋ ገባ። አስቀድሞ ብዙ ማስፈራሪያዎች ከተለያዩ ሰዎች ቢደርሱትም የሚሰቀለው በኢየሩሳሌም ብቻ በመሆኑ ወደዚያው መጣ። አህያዋ ከነውርንጫዋ የአዳምና የሔዋን እንዲሁም የልጆቻቸው ምሳሌ ሲሆኑ ታስረው መገኘታቸውም የሰው ልጆች ሁሉ ከአምላካቸው ኮብልለው ጠፍተው በአጋንንት፥ በማእሰረ ኃጢአት፥ በማእሰረ ፍዳ፥ በኲነኔ ታስረው ስለነበረ ተፈትተው እንዲመጡለት በመፈለጉ ሐዋርያትን ሥልጣነ ክህነት ሰጥቶ ከኃጢአት ማሰሪያ ፈትታችሁ የሃይማኖትን ትምህርት አስተምራችሁ ደቀመዛሙርቴ አድርጓቸው በማለት አዝዟቸዋል። ማቴ.16፥19። ማቴ.28፥19። ማር.16፥15። ሰይጣንም ቢከራከራችሁ «ለጌታ ያስፈልጉታል» ብላችሁ ወደ ጽድቅ ጎዳና ምሯቸው፥ ወደ እኔም አምጧቸው በማለት እንደላካቸው እንገነዘባለን።

የነቢያት ጌታ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕዝቡን በለመደው ሥርዓት ለማስተማር ሥርዓተ ነቢያትን ተጠቅሟል። አስቀድሞ የነበሩት ነቢያት ዘመነ መዓት መምጣቱን ለማሳየት በፈረስ ተቀምጠው ዘገር ነጥቀው በከተማው ውስጥ ሲዘዋወሩ ይታዩ ነበር፤ ዘመነ ሣህል፥ ዘመነ ምሕረት መምጣቱን ለማሳየት ደግሞ በአህያ ላይ ተቀምጠው ይታዩ ነበር። መድኃኒታችንም ዘመነ ሰላም ዘመነ ፍሥሐ መምጣቱን ለማመልከትና በሰውና በእግዚአብሔር፥ በሰውና በመላእክት በሥጋና በነፍስ መካከል የነበረው ጸብ ማብቃቱን ዕርቀ ሰላም በእርሱ አማካኝነት መውረዱን ሲያስረዳ በአህያ ላይ ተቀምጦ ለሕዝቡ ታየ።

የክብር ባለቤት ነውና ክብሩን ለመግለጥ የሚከተሉት ሕዝብ በሚሄድበት መንገድ ላይ ሳይቀር ልብሳቸውን እንዲሁም የለምለም ዛፍ ዝንጣፊ አነጠፉለት። እንኳን እርሱ የተቀመጠባት አህያ ስንኳ የተከበረችናትና መሬቱን እንዳትረግጥ ነው ልብሳቸውን ከትከሻቸው እየገፈፉ የጐዘጐዙላት። ይህ ሁሉ የሚያሳየን በትክክል የሚከተሉት ሰዎች ምን ያህል እንደሚያከብሩትና እንዲያውም እርሱን ብቻ ሳይሆን እርሱ የመረጣቸውን ሁሉ በታላቅ ትህትና እንደሚያከብሯቸው ነው። ይህንኑ ሲያስረዳን ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ ምዕራፍ 8 ቁጥር 33 ላይ «እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል?» በማለት ጽፎልናል።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ደም አፈሰሰ በችንካርም ላይ ቆመ። አዳም የበለሲቱን ፍሬ ወደ አፉ አስገብቶ አጣጣመ። ክርስቶስ ግን መራራ አሞትን ቀመሰ ሆምጣጤውንም ጠጣ። አዳም የብርሃን ልብሱን ተገፎ ራቁቱን ቀረ በበለስ ቅጠል ተሸፈነ። ክርስቶስ ግን ልብሱን ተገፎ ዕራቁቱን ተሰቀለ። ፀሐይም በመጨለሟ በጨለማ መጋረጃነት ተሸፈነ። ይልቁንም አዳም የተጐዳው በነፍሱ ነውና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱን ከሶ ታረቀው ከራሱም ጋር አስታረቀው።

ዛሬ ግን ክርስቶስ አሥራ ሦስቱን ሕማማት መስቀል በትዕግሥት ተቀብሎ ኃጢአታችንን ካራገፈልን በኋላ በኃጢአት ሸክም ጎብጠን ተገኘን። «እናንተ ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ» በሚለው አምላካዊ ቃል ብንጠራም ጆሮ ዳባ ልበስ ብለናል። በመስቀሉ ደም ሰላም ሆኖልን ሳለ በጦርነት ውስጥ ተዘፍቀናል። ከታረቀን በኋላ ተጣላን። ከእርግማን ሲዋጀንም ዳግመኛ ከእርግማን በታች ወደቅን። የመስቀሉ ነገር፥ በመስቀል ላይ የተፈጸመው ቤዛነት፥ ሥጋ ወደሙን መቀበል፥ መስቀል መሳለም፥ በመስቀል ማማተብ፥ የመስቀል ምልክት መያዝም ሞኝነት ሆነብን። በዚህ በመጨረሻው ዘመን የመስቀል ጠላቶች ሆነን ተመላለስን ሆዳችንን (ሥጋችንን) አመለክን። ነውር መሥራትን እንደ ክብር ቆጠርነው። ለሰማያዊ ክብር ባለቤትነት ከሞተልን በኋላ አሳባችን ምድራዊ ሆኖ ተገኘ። ማቴ.11፥28። 1ቆሮ.1፥18። ቆላ.1፥18።

ዛሬም በእኛ እጅ ክርስቶስን የምናሳዝንበትና የምናስቀይምበት የኃጢአትና የበደል መቃ አለ። ወገኖቻችንን በግፍ ቀንበር የምናደቅቃቸው በግፍ በትር የምንቀጠቅጣቸው ከሆነ ይኸም ክርስቶስ ራሱን የተቀጠቀጠበት መቃ ነው። ምክንያቱም በታናናሾቻችን ላይ የምንፈጽመው ሁሉ በእሱ ላይ እንደተፈጸመ ይቆጠራልና! ሳውል ክርስቲያኖችን ባሳደደ ጊዜ ክርስቶስ በሰማያዮኖ «ለምን ታሳድደኛለህ?» ማለቱ ለዚህ ነው። የሐዋ.9፥1–30።

ወደደብረ ዘይት ቁልቁለት በቀረቡ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ደስ እያላቸው በታላቅ ድምፅ «በጌታ ስም የሚመጣ ንጉሥ የተባረከ ነው በሰማይ ሰላም በአርያምም ክብር» እያሉ እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር። እርሱ የክብር አምላክ ነውና። በኢየሩሳሌም ከተማም የፋሲካን በዓል ለማክበር ተሰብስበው የነበሩት አይሁድ ድል አድራጊነቱንና የሰላም አምላክ መሆኑን ለመመስከር የዘንባባ ዛፍ ዝንጣፊ ይዘው ሊቀበሉት ወጡ። ዘንባባ የድልና የሰላም ምልክት ነውና። ንጉሡ ኢዩ ሲነግሥ ልብሳቸውን አንጥፈው ዘንባባ ይዘው ሕዝቡ እንዳከበሩትና እንደተከተሉት እንዲሁም አብርሃም ይስሐቅና ያዕቆብም ዘንባባ ይዘው እግዚአብሔርን እንዳመሰገኑት ዓይነት ነው። በአንፃሩ አምላክነቱን የተጠራጠሩ ዕሩቅ ብእሲ (ሰው)፥ የዮሴፍ ልጅ የመሰላቸው የካህናት አለቆች፣ ጻፎችና ፈሪሳውያን እንዴት በእንዲህ ያለ ምስጋና ይመሰገናል በማለት ተቆጥተው ነበር። ዮሐ.6፥42። ማቴ.13፥54–56። ሉቃ.3፥23። እርሱ ግን ተጠራጣሪዎችንና ትዕቢተኞችን ለማሳፈር ከሕፃናት አፍ ምስጋናን አዘጋጀ። መዝ.8፥2። ማቴ. 21፥16።

በወቅቱ የነበሩት የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ግን ጥሪውን ሊሰሙት አልፈለጉም። ክብሩንም ሊያዩ፥ ምስጋናውን ሊሰሙ አልፈቀዱም። ምድራዊውን እንጂ ሰማያዊውን ክብር ለራሳቸው አልፈለጉምና ይልቁንም ጌታችን በሕፃናት አንደበት በመመስገኑ ተቆጡ።

የሰው ልጅ ዛሬም ምድራዊ ክብርና ሥልጣን ሲፈልግ ሰማያዊ ጌትነቱን እያጣ ነው። የዲያብሎስ ባሪያ በመሆን፥ የሥጋዊ ፍላጐቱ ባሪያ በመሆን በማእሰረ ኃጢአት ታግቷል። የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን የትህትና ትምህርት ዘንግቶ፥ አላስተውል ብሎ በትዕቢት አሁንም የራሱን ጎዳና እየፈጠረ ወደ ሐሰት አምላክ እየገሰገሰ ነው።

እግዚአብሔር ግን ሕዝቡ ይጠፉ ዘንድ አይፈልግምና ከየሄዱበት፥ ከጠፉበት ቦታ ሁሉ ተፈልገው እንዲመጡለት ይጣራል። ዛሬም የሐዋርያትን አሠረ ክህነት የተቀበሉትን፣ የያዙትን በኃጢአት የታሰረውን ሁሉ ፈተው እንዲያቀርቡለት አዟል። እንደዚያን ጊዜዎቹ ሐዋርያት ትዕዛዙን በትክክል ለመፈጸም ወደፊት የሚሮጥ ሐዋርያ ይኖር ይሆን? ይህን አለማድረግ የሚያሰቀጣ፥ የሚያስከስስ መሆኑን አስቀድሞ በሕዝቅኤል ምዕራፍ 33 ላይ ተገልጿልና እናስተውል። ፈትታችሁ አምጡልኝ ያለው እናቲቱን አህያ ብቻ ሳይሆን ከነውርንጫዋ ነው። ስለዚህ ወላጆች ብቻ ሳይሆኑ ልጆችም እንዲቀርቡ ጠርቶ፥ ጐትቶ ወደቤተክርስቲያን ማምጣት ያስፈልጋል። የኃጢአትን ሸክም መሸከም ሳይለምዱ የጌታን መስቀል መሸከምን፥ ቤተክርስቲያንን ማገልገልን እንዲለምዱ ማድረግ ተገቢ ተግባር ነው። ጌታ ይፈልጋቸዋልና።

ጌታ ይቀመጥባት ዘንድ ያስመጣት አህያ እንዲሁ መደዴ የተለቀቀች ሳትሆን ጌቶቿ አስረዋት የነበረች፥ በጌቶቿ ሥር በሥርዓት የተያዘች ነበረች። ዛሬም የሰው ልጅ ለጌታ የሚያስፈልግ ሆኖ ለመገኘት እንዲችል ሥርዓት አልባ መደዴ መሆን የለበትም። በእምነት፥ በሃይማኖት ሥርዓት ታጥሮ መገኘት ይኖርበታል። እንዲያ ሆነን ከተገኘን ጌታችን ሊቀመጥብን ይፈልጋልና እንደአህያዋ ትሁታን፥ የዋሃን ሆነን እንቅረብ። በዘመናችን የሰዎች ትልቁ ችግር በየዋህነትና በትህትና ትከሻን የእግዚአብሔርን ሕግ ለመሸከም አመቻችቶና ተዘጋጅቶ መገኘት አለመቻል ነው። አምላካችን ግን ድካማችንን ዐውቆ «እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ወደኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ» በማለት ይጠራናል። ከተጫነብን አስቸጋሪ ወልገድጋዳና ከባድ የኃጢአት ሸክም ሊያሳርፈንና በም ትኩ የርሱን ቀላልና ልዝብ ቀንበር እንድን ሸከም ይጋብዘናል። ማቴ.11፥28–30። ታዲያ ኃጢአተኞችን ወደ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ትናንት ክፉዎች አይሁድ በጥፊ እንደመቱት እኛም በዕደ ልቦናችን በክህደት ጥፊ እየመታነው ነው። እንደ አይሁድ እጆቻችንን ለበደል እየዘረጋን ነው። በጥፊ የመታህ ማነው? እወቅ እያሉ እንዳፌዙበት እኛም እግዚአብሔር እንደማያውቅ አድርገን በምንሠራው ሥራ እየቀለድንበት ነው። እግዚአብሔር ካለ ለምን እንዲህ አያደርግም እያልን እያፌዝንበት ነው። ከኃጢአት ለመመለስ በደልን ለማራቅ ሳንወስን በፊቱ መንበርከክ ፌዝ ነው።

ምን ያደርገኛል? ማንስ ምን ሆነ? በሚል ደካማ አስተሳሰብ በእግዚአብሔር ፊት የማይገባ ሥራ መሥራት እንደ አይሁድ በፊቱ ላይ መትፋት ነው። አይሁድ ቢንቁት አይደል በፊቱ ላይ የተፉት? እኛም ብንንቀው ነው በፊቱ ኃጢአት የምንሠራው! አክታ አስጸያፊ እንደሆነ ኃጢአትም አስጸያፊ ነው። እነዚያ ነውራቸውን እንደ መልካም እንዳዩት እኛም ነውር ኃጢአታችን መልካም ይመስለናል።

ተጠማሁ ባለ ጊዜ ለመብሉ ሐሞት ለመጠጡ ሆምጣጤ አቀረቡለት። ትናንትና ዛሬ ለዘላለም ያው የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዛሬም ጽድቅን ተርቦና ተጠምቶ ሳለ ምንድን ነው ያቀረብንለት? ሕይወታችን ጣፋጭ ነው? ወይስ መራራ? ዛሬ ያቀረብንለት መጠጥ የኃጢአትና የበደል መራራ ሆምጣጣ መጠጥን ነው። ይኸም የእግዚአብሔር ወዳጆች አለመሆናችንን ያሳያል። ምክንያቱም ማንም ቢሆን ለወዳጁ የሚያቀርበው መራራውን ሳይሆን ጣፋጩን ነውና! መራራውን አሞት ቀምሶ የተወ አምላክ እኛንም አይቶ መርምሮ መራሮች ሆነን ካገኘን ለምረረ ገሀነም ይተወናል።

የከፋት፥ የምቀኝነት፥ የግብዝነት የትዕቢት የአመንዝራነት አለንጋ በእጃችን ካለ ይኸም ክርስቶስ የተገረፈበት አለንጋ ነው። ክርስቶስን ካሰዘነው፥ ካናደድነው፥ ካስቆጣነው በከፉ ሥራችን በሐዘን በንዴት በቁጣ አለንጋ ገረፍነው ማለት ነው። ወገኖቻችንን የምንገርፍበትም የግፍ አለንጋ በእጃችን እስካለ ድረስ የዛሬዎቹ አይሁዳውያን እኛ ነን። እንደ ጲላጦስ ነጹሖች ነን እያልን እየተገዘትን ወገኖቻችንን በግፍ አለንጋ የምንገርፍ ዛሬም አለን። ምርጫችንስ ወንበዴው

ማይንቀው አምላክ ግብዣ መታደም ይኖርብናል።

ሆሣዕና ማለት መድኃኒት ማለት ነውና መድኃኒታችንን እንፈልገው። እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ደቀመዛሙርቱ በአንድነት «ሆሣዕና በአርያም» ብለው እንደዘመሩለት እኛም ክርስቶሳውያን ነን፥ ተከታዮቹ ነን የምንል ሁሉ በአንድነት ከፍ ባለ ድምጽ ማንነቱን ዐውቀን እናመስግነው። ከሰማይ ለወረደልን መድኃኒት፥ ሆሣዕና ለወልደ ዳዊት እንበል። በመቅደስ አካባቢ የነበሩት የኢየሩሳሌም ሕፃናት እንዳመሰገኑት፥ እንደ ዘመሩለት እኛም ክብሩን እንግለጥ። እኛ ብናመሰግነው ለራሳችን ክብር ነው እርሱ ግን ምስጋናው የራሱ ነውና። እኛ ዝም ብንል ድንጋዮች ያመሰግኑታል። እንግዲህ ከግዑዛን ድንጋዮች እንዳናንስ አምላክነቱን ዕንወቅ፥ ለምስጋና አፋችን ይከፈት ድምፃችንም ይጉላ።

ሐዋርያት አህያይቱንና ውርንጫዋን እንዲቀመጥባቸው ለማዘጋጀት ልብሳቸውን አንጥፈውለታል። የሚከተሉትም ሕዝብ ልብሳቸውን መሬት ላይ ጐዝጉዘው አህያዋ በላዩ እንድትሄድ አድርገዋል። ዛሬም በእያንዳንዳችን ልቡና ውስጥ ጌታችን ሊቀመጥ ይፈልጋል። በውጪ ቆሞም በሩን እያንኳኳ ነው። እራ.3፥20። ታዲያ ምን አንጥፈን ልንቀበለው ተዘጋጅተናል? ድምፁንስ ሰምተነው ይሆን? ልባችንስ እርሱ ገብቶ ይቀመጥበት ዘንድ ጸድቶ፥ ተጐዝጉዞ፥ አምሮ ይጠብቀዋል? እግዚአብሔር አምላክ የኛን ልብ በንስሐ ተጠርጐ ፍቅርና መልካም ሥነ ምግባር ተጐዝጉዞበት አምሮ እንዲጠብቀው ይፈልጋል። ይህ ሳይሆን ቀርቶ ልባችን በኃጢአት ሥራ፥ በክፉ ምኞት፥ በተንኮል፥ በምቀኝነት፥ በቅንዓት፥ በቂምና በመሳሰሉት ተሞልቶ፥ በውስጣችን እርሱ የማይወደውን ሥራ እንሸጥ እንለውጥ እንደሆነ ቤተመቅደሱን እያቆሸሽን መሆናችንን ዐውቀን አሁኑኑ እኛው ማጽዳት እንጀምር። አሊያ ግን ጌታ በሆሣዕና ዕለት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በመጣ ጊዜ የአይሁድን ቤተ መቅደስ ቆሽሾ እንዳገኘው፥ የገመድ ጅራፍም አበጅቶ ሁሉንም እንዳስወጣቸው እኛንም ዳግመኛ ከቅዱሳኑ ጋር በመጣ ጊዜ በመቅሰፍተ ጥብጣቤ ይቀጣናልና ከቤቱም ያስወጣናልና የጽዳቱ ዘመቻ ከአሁኑ በእኛው ይጀመር።

የእግዚአብሔር ቤት የጸሎት ቤት ነው። የክርስቲያኖች ልቡና፥ የክርስቲያኖች ሰውነት የእግዚአብሔር ማደሪያ ቤተመቅደስ ነው። 1ቆሮ. 3፥16–17። ስለዚህ እንጠንቀቅለት! በጽድቅ ሥራ እንዲያሸበርቅ እናድርገው።

መድኃኒት የሆነውን የጌታችንን ሥጋና ደም ለመቀበል ሰውነታችንን በንስሐ እናዘጋጅ። ከርሱ ጋር ለዘለዓለም መኖር እንድንችል፥ ከቅዱሳኑ ጋር በሰማያት ለማመስገን እንድንበቃ ዛሬ ነቀተን ከእንቅልፋችን ተነሥተን ሥንቃችንን የክርስቶስን ሥጋና ደም እንቀበል ገና ረጅም ጉዞ አለብንና። ኤልያስን ከእግዚአብሔር ተራራ ከኮሬብ ለመድረስ ያበረታው ከእግዚአብሔር የተሰጠው እንጀራ ነው። 1ነገ.19፥5–9። እኛም ከሰማያዊት ኢየሩሳሌም ለመድረስ የሚያበረታን ከሰማይ የወረደልንን እንጀራ እንመገበው። ዮሐ.6፥32–41። ለዚህ ታላቅ ክብር እንድንበቃ የአምላካችን ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን። የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት የቅዱሳን መላእክት ተራዳኢነት የቅዱሳኑ ሁሉ ምልጃና ጸሎት አይለየን። ✣

«ወለእግዚአብሔር ስብሐት»



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በርባን ነው? ወይስ ጻድቁ ክርስቶስ ነው? ጦረኛውን በርባንን ነው? ወይስ ሰላማዊውን ክርስቶስን ነው? የወገኖቹን ደም የሚያፈሰውን በርባንን ነው ወይስ ስለወገኖቹ ደሙን ያፈሰሰውን ክርስቶስን ነው? ዛሬም በዓለማችን ብዙ በርባኖች አሉ። የእኛም ምርጫ በርባኖችን ሆኗል። ረቂቁንም በርባን ዲያቢሎስን መርጠናል። ክርስቶስን አስወግደው እንዳሉ ከልባችን ክርስቶስን አስወግደነዋል። ከሕይወታችን ለይተነዋል።

ክርስቶስ የምተለትን ሰውነት ከጽድቅ አራቁተን ከተገኘን ክርስቶስን ገፈፍነው ማለት ነው። በውስጣችን የበላነው ሥጋው የጠጣነው ደሙ አለና፤ ዛሬ የክርስቶስን የፈራጅነትና የሁሉን ቻይነት ሥልጣን ገፍፈው አማላጅ የሚሉት አሉ። የፈጣሪነቱንም ክብር ገፍፈው ፍጡርም ብለውታል። እሱ ግን ፈራጅ እንጂ አማላጅ ፈጣሪ እንጂ ፍጡር አይደለም። በተዋሕዶ የከበረ የአብ ልጅ የማርያም ልጅ ነው። ከተዋሕዶ በኋላ ሁለትነት የለም። አንድ አካል አንድ ባህርይ ነው። ለክርስቶስ የሚገባውን ክብር አለመስጠትም ልብሱን እንደ መግፈፍ ይቆጠራል።

ከጭፍሮች አንዱ በስለታም ጦር ጎኑን እንደወጋው በክህደትና በጥርጥር ጦር እየወጋነው ነው። በኃጢአት የቆሸሸው በበደል የረከሰው ሕይወታችን ለክርስቶስ የጐን ውጋቱ ነው። ክፉ ከሚያደርጉ ጭፍሮች ተቀላቅለን የክፉ ምግባራቸው ተባባሪ ሆነን ተገኝተናል። ያ የጥፋት የክፋትና የጭካኔ ጦር ዛሬም በእጃችን አለ። «በጦር ከተወጋ በነገር የተወጋ» እንዲሉ በነገር ጦር ስንቱን አቁስ ለናል? የትዕቢት ጦር የመዘዝን የለንም? በእኛ ምክንያት በሐዘን ጦር ተወግተው የወደቁ ብዙዎች ናቸው። ከክርስቶስ ጐን ደምና ውኃ እንዳፈሰሰ ደም እንባ የሚያለቅሱ ክርስቶሳውያን ዛሬም አሉ ምክንያቶቹ ዞሮ ዞሮ እኛው ነን።

በክፉ ሥራችን የእግዚአብሔር ምሕረት ወደ መዓት ትዕግሥቱ ወደ ቁጣ እንዲለወጥ በማድረግ ለሰላም፥ ለፍቅር፥ ለምሕረት፥ ለረድኤት፥ ለበረከት፥ ለቸርነት የተዘረጋው ቅዱስ እጁ እንዲታጠፍ ካደረግን፤ እጁን የኋሊት ጠፍሮ እንደማሰር ነው። እሱ እጁን ዘርግቶ እንካችሁ ተቀበሉ ሲለን አንቀበልም ማለት እጁን የኋሊት ማሰር ነው። የዛሬው የክርስቶስ ሥቃይ ይህ ነው።

አስማተኝነቱ፥ ሴሰኝነቱ፥ ነፍሰ ገዳይነቱ፥ አምልኮተ ጣዖቱ፥ ሐሰተኝነቱ፥ ይህ የዘመናችን ችንካር ነው። ትዕቢቱ፥ ስስቱ ገንዘብ መውደዱ፥ ይህም ችንካር ነው። ክርስቶስ የተንገላታለት፥ ሥጋውን የቆረሰለት፥ ደሙን ያፈሰሰለት፥ ሕይወቱን የካሰለት ሕዝብ እንዲህ ሆኖ ሲያገኘው እጅጉን ያዝናል። እንደመስቀሉ ችንካር ያቆስለዋል።

በሐዋርያት ላይ መንፈስ ቅዱስ በወረደላቸው ዕለት የቅዱስ ጴጥሮስን ስብከት የሰሙት ሕዝብ እንግዲህ ምን እናድርግ? እንዳሉ እኛም አሁኑኑ ምን እናድርግ? ልንል ይገባናል። የምናደርገውም ነገር ቀላል ነው። ንስሐ መግባት፥ ከኃጢአት መመለስ፥ ከበደል መራቅ፥ ወደ ቀራንዮ ማቅናት፥ ወደ መስቀሉ መመልከት ነው። ጌታ የሚወደው ደቀ መዝሙር ዮሐንስ በመስቀሉ ፊት ቆሞ እንደ ተገኘ የእናት አማላጅ ቅድስት ድንግል ማርያምን እንዳገኘ፥ እኛም እንደተወደዱ ልጆች ከመስቀሉ ፊት አንጥፉ «እነኋት እናትህ» ተብላ በዮሐንስ በኩል የተሰጠችንን የአደራ እናት ይዘን እንገኝ።

ቅዱስ ዮሐንስ ጌታን ከእናቱ ጋር ያገኘው በቀራንዮ ነው። ስለዚህ እኛም ወደ ቀራንዮ እንጓዝ። ጌታን ከእናቱ ጋር እንድናገኝ፤ አባትም እናትም እንዲኖረን፥ የዛሬዋ ቀራንዮ ቤተ ክርስቲያን ናት። ዕለት ዕለት አማናዊው የክርስቶስ ሥጋ ይቆረስባታል። ደሙ ይፈስባታል። በክርስቶስ ደም የከበረው መስቀል በክብር አለ። የበደል ግድግዳ የፈረሰበት ጥል የተባለ ዲያቢሎስ የተገደለበት ነውና። ዛሬም ሰላም ያገኘንበትን መስቀል እናከብረዋለን እንሳለመዋለን። በመስቀል ምልክትም ጥንተ ጠላታችንን ዲያቢሎስን እንቀጠቅጥበታለን። ተቃጠልኩ አረርኩ እናሰኝበታለን። በሲኦል ሲያቃጥለን የነበረውን ጠላት ዛሬ ተራችንን በክርስቶስ መስቀል እናቃጥለዋለን።

ቅዱስ ዮሐንስ በቀራንዮ ያገኛትን ዘለዓለማዊ ድንግል ቅድስት ማርያምን ከተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እናገኛታለን። የአማላጅነቷ ተጠቃሚዎች እንሆናለን። ጌታ በመጨረሻው ሰዓት በመስቀል ላይ ሆኖ እንደ ኑዛዜ ቢሉ ወይም እንደ አደራ ለሚወደው ደቀ መዝሙሩ ለዮሐንስ በዘለዓለማዊ ቃሉ «እነኋት እናትህ» እንዳለው ዛሬም መሠረቷም ጉልላቷም ክርስቶስ የሆነ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እያንዳንዱን ክርስቲያን በዘለዓለማዊው የጌታ ቃል «እነኋት እናትህ» ትለዋለች። የሚያስፈልገው ነገር ቢኖር ዮሐንስን ሆኖ መስቀሉ ሥር መገኘት ነው። ዮሐንስ የጌታን ቃል አክብሮ እናቴ ብሎ ወደቤቱ እንዳስገባት እኛም እናቴ ብለን ቤት ወደሚባል ልባችን ማስገባት ይኸም የክርስቶስን የኑዛዜ ቃል መጠበቅ የአደራ ቃሉን ማክበር ነው። እሱ «የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል።» እንዳለ እውነት የምንወደው ከሆነ ቃሉን እንጠብቅ። ዮሐ.14፥23።

አይሁድ ክርስቶስን እንደጠሉት እኛም አንጥላው። እውነተኛ መብል የክርስቶስን ሥጋ እውነተኛ መጠጥ የክርስቶስን ደም መጥላት በየምክንያቱም ከእሱ መራቅ ክርስቶስን መጥላት ነው። መጨነቅ መጠበብ የእንስሳት ሥጋ እና የዓሣ ሥጋ ቀረብኝ ተብሎ ሳይሆን የቀራንዮው በግ የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ለምን ይቅርብኝ ተብሎ ነው። አይሁድ ክርስቶስን አልተቀበሉትም አራቁት (ሰቀሉት) እንጂ እኛም ሥጋውና ደሙን አልተቀበልንም አራቅነው እንጂ፤ ስለዚህ አሁኑኑ ወደ ሕይወት መድኃኒት እንቅረብ።

ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለ የተናገራቸው ቃላት ሰባት ናቸው። እነሱም ሰባቱ አጽርሐ መስቀል በመባል ይታወቃሉ። አጽርሐ የሚለው ቃል ጸርሐ ጮኸ ከሚለው የግሥ ዘር የወጣ ነው።

1. «አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው» ብሎ ስለጠላቶቹ ለመነ። ሉቃ.23፥34። እኛስ ዛሬ የምናደርገውን እናውቃለን? ራስ ለመኖር ለመጥገብ ለመደሰት ሌላውን መግደል ማስራብ ማሳዘን፥ ማስጨነቅ፥ ማዋረድ መግፋት አላዋቂነት ነው። ይህ አላዋቂ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ነት እስካልተወገደ ድረስ የምንፈልገውን ደስታና ሰላም አናገኝም። እነኳን ተበድለን በድለንስ ቢሆን ይቅርታን የምንጠይቅ ነን? በቀልን ትተን ክርስቶስ እንዳስተማረን ይቅር የምንባባል ከሆን ዘመናችን የሰላም ዘመን ይሆናል። አለበለዚያ ግን በቀል በቀልን እየወለደ ትርፉ ሰላም ማጣት ነው። እኛ ሰለጠላቶቻችን ቀርቶ ስለ ወገኖቻችን የማናስብ ጨካኞች ነን። እንደዚህ ዓይነቱ ድንጋይ ልብ ከአሁኑ መወገድ አለበት።

2. «ተጠማሁ» አለ። ዮሐ. 19፥29። ዛሬም ክርስቶስ ከሰዎች ዘንድ የጽድቅን ውሃና የንስሐን እንባ ተጠምቷል። ያቀረብንለት ሁሉ እንደ አሞቱ መራራ ሆነ። በኃጢአት የመረረ ሕይወት ክረስቶስን አያረካውም። ስለዚህ በቃሉ ጨውነት የጣፈጠ ሕይወት ይኑረን።

3. «እውነት እውነት እልሃለሁ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትኖራለህ» አለው በቀኝ ለተሰቀለው ወንበዴ። ሉቃ.23፥43። በግራው የተሰቀለው ወንበዴ በመከራ ተይዞ ሳለ እንኳን ባለቀ ሰዓት ንስሐ መግባት አልቻለም። በቀኝ የተሰቀለው ግን አቤቱ በመንግሥትህ አስበኝ ባለው ጊዜ አዳም ወደ ተባረረባት ገነት ዛሬውኑ ትገባለህ ከእኔም ጋር ትኖራለህ ተባለ። እኛስ ከየትኛው ወገን ነን። ከቀኝ ወይስ ከግራ? ዛሬ አብዛኞቻችን በግራ የተሰቀለውን ወንበዴ እንመስላለን። በንስሐ የተዘጋጀ ልብ የለንም። እስከ ዕለተ ሞታችን የተሰጠንን ጊዜ ሳንጠቀምበት በሞት ተይዘን በኬሻ ተጠቅልለን ወደ መቃብር እንወርዳለን። በነፍሳችንም በአጋንንት ተይዘን በጨለማ ተጠቅልለን ወደ ሲኦል እንወርዳለን። ስለዚህ በቀኝ እንደተሰቀለው ወንበዴ ንስሐ የሚገባ ልብ በመንግሥትህ አስበኝ የሚል አንደበት ይኑረን። ዛሬውኑ ወደ ምድራዊቷ ገነት ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንግባ በመስቀል ላይ የተቆረሰውን ሥጋውን እንብላ ደሙንም እንጠጣ ነፍሳችንም ሰላማዊቱን ገነት የታደለች ትሆናለች።

4. «አምላኬ አምላኬ ስለ ምን ተወኸኝ» አለ። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የፍጡሩን ሥጋ በመልበሱ አምላኬ አምላኬ አለ። አንድም ተላልፎ የተሰጠለት የአዳም ቃል ነው። ስለ አዳም ሆኖ ተናገረ። በሲኦል ያለ አዳም «ከሰማየ ሰማያት ወርጄ ከድንግል ማርያም ተወልጄ በመስቀል ላይ ሞቼ አድንሃለሁ» ያለከኝ እነሆ ተፈጸመ። ታዲያ አምላኬ ሆይ ለምን ተውከኝ ከሲኦል የምወጣው መቼ ነው። የማለቱ ነገር ነው። አንድም በመከራ ሰዓት አምላኬ አምላኬ ማለትን ለእኛ ሲያስተምረን ነው። ከዚህም ትምህርት ወስደን በመከራ ነፍስ በመከራ ሥጋ የተያዝን እኛ አምላኬ አምላኬ አትተወን አትጣለን አትለየን እንበል።

5. «እነሆ ልጅሽ እነኋት እናትህ» ዮሐ.19፥26። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመልዕልተ መስቀል ሳለ ከፍጥረታት ሁሉ አብልጦ የወደዳትን እናቱን ቅድስት ድንግል ማርያምን እና ከደቀመዛሙርቱ አብልጦ የሚወደውን ዮሐንስን ባያቸው ጊዜ ለእናቱ ዮሐንስን እያሳያት «እነሆ ልጅሽ» አላት። ደግሞ እናቱን እያሳየው «እነኋት እናትህ» አለው። በማቴ.20፥20። እንደተጠቀሰው ዮሐንስ ሥጋዊ እናቱ ልመና አታውቅምና ልመና የምታውቅ መንፈሳዊት ንጽሕት ቅድስት እናት ተሰጠው። ያቺ ሳታውቅ መከራንና ሞት የምትለምን ናትና አውቃ ሕይወትን የምትለምን እናት ተሰጠው። ዛሬም ቢሆን የቅድስት ድንግል ማርያም ልጅ የሚሆነው እንደ ዮሐንስ ጌታ የወደደው ብቻ ነው። እናትነቷ በዮሐንስ በኩል ተላለፈልን። እኛ እናትነቷን ባንሻ ይጐድልብናል እንጂ አይጐድልባትም። እሷ የዘለዓለማዊው አምላክ የኢየሱስ ክርስቶስ እናት መሆኗ ብቻ ይበቃታል።

6. «አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ» አለ ሉቃ.23፥46። ቅዱስ ጳውሎስ ነፍሳችሁን ለታመነ ፈጣሪ አደራ ስጡ እንዳለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነፍስን ለታመነ ፈጣሪ አደራ መስጠትን ሲያስተምረን ነው። ከዚያ በፊት ነፍስ ሁሉ ለዲያብሎስ ትሰጥ ነበርና ከእንግዲህ ቀረላችሁ ሲለን ነው። እኛ ግን ነፃ የወጣች ነፍሳችንን በኃጢአት ምክንያት እንደገና ወደ ባርነት እየመለስናት ነው። ለአርነታችን ሥጋዊ ምክንያት እየሰጠን በዲያቢሎስ እጅ እየወደቅን ነው። ስለዚህ የቀራንዮን አደባባይ እያሰብን ነፍሳችንን አሁኑኑ ለባለቤቱ ለእግዚአብሔር አሳልፈን መስጠት አለብን።

7. በመጨረሻም «ተፈጸመ» አለ ዮሐ. 19፥30። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የማስታረቁን ነገር በመስቀል ላይ በዚህ ዓይነት መልኩ ፈጸመ። አስታረቀ ስንልም ከባህርይ አባቱ ከአብ፥ ከራሱ፥ ከባህርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ነው። ከእንግዲህ ወዲህ ያስታረቀኛል ማለት ዳግመኛ ይሞታል ማለት ነውና እንዲህ አይባልም። ምክንያቱም የእሱ አስታራቂነት የተፈጸመው በሞት ነውና፤ ልክ የእሱ መከራ በሞት እንደአከተመ በሲኦል የነበሩ ነፍሳትም መከራው አከተመላቸው።

ከዚህ በኋላ ዮሴፍና ኒቆዲሞስ የተባሉ ደጋግ ሰዎች ጲላጦስን ለምነው ከመስቀል አውርደው ገንዘው በአዲስ መቃብር አኑረውታል። ዛሬም ክርስቶስ እንደነዚህ ያሉ ደጋግ ሰዎች ይፈልጋል። ክርስቶስን ከችንካር እንዳላቀቁት ወገኖቹን ከግፍ ከመከራ የሚያላቅቅ በግፍ የተገደሉትን በክብር የሚቀብር ሰው ማነው? ስለክርስትና ሃይማኖት የሞቱትን የሚያስብ የወደቁትን የሚያነሳ የተበተኑትን የሚሰበስብ የተሰደዱትን የሚቀበል ማነው? እንግዲህ እንደዚህ ዓይነት ሰው ከጠፋ እንደዚህ ዓይነት ሰው ሆኖ ለመገኘት ራስን በሃይማኖት ማንቃቃት ነው።

በአጭር ቃል መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መግነዝ ፍቱልኝ መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል በተቀበረ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ። በአካለ ሥጋ ወደ መቃብር በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል የወረደ አምላክ ነፍሳትን ሁሉ ማረከ። በሞት ያሉትን ወደ ሕይወት አሸጋገራቸው። ሕይወት ነውና ሕይወት ሆናቸው። በጨለማ የነበሩትን ወደ ብርሃን መራቸው። ብርሃን ነውና ብርሃን ሆናቸው። ጨለማን ገፎ ብርሃን



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

አለበሳቸው። ከሲኦል አውጥቶ ገነት አስገባቸው። ወደ መቃብሩ በማለዳ የሄዱ ሴቶች «ሕያውን ከሙታን መካከል ለምን ትፈልጋላችሁ? አስቀ ድሞ እንደተናገረ ተነሥቷል ከዚህ የለም» ተባሉ። ነጫጭ በለበሱ መላእክት ትንሣኤው ተሰበከላቸው። ዮሐ.20፥12። እነሱም ትንሣኤውን ተራቸውን ለወንድሞቻቸው ሰበኩ። እኛም ትንሣኤውን ለሕይወት እንሰበክ። እንደ መላእክት ስሙን ለመቀደስ ክብሩን ለመውረስ የተፈ ጠርን እኛ ልብሳችን ሕይወታችን ነጭ ይሁን። በኃጢአት አይደፍ። እንደ መግደላዊት ማርያም በፍቅሩ ጦር ተወግተን በፍቅሩ ሰንሰለት ታስረን እንፈልገው። እናገኘውማለን። እሷን ሂጂ ተናገሪ ያለ አምላክ እኛንም ሂዱ ተናገሩ እያለን ነው። ሄዶ የሚናገርለት ይፈልጋልና።

እንግዲህ የተወደዳችሁ የእግዚአ ብሔር ቤተሰቦች የድንግል ማርያም ወዳጆች እነሆ እኛ በጾም ራሳችንን በእግዚአብሔር ፊት አዋርደን በአዲስ ልብ በአዲስ መንፈስ ሕማማተ መስቀሉን እያሰብን ነው። ከብርሃነ ትንሣኤውም ለመድረስ እየተቻኮልን ነው። እንዲህ መሆኑም መልካም ነው። ነገር ግን በዓሉ የደስታ ሆኖልን የትንሣኤው ብርሃን የሚበራልን የብር ሃን ኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋና ደም ስንቀበል መሆኑን ለአንድ አፍታ አስበን እናውቃለን? እስከአሁን ሥጋ ወደሙን ያልተቀበልን ሰዎችስ ሰውነ ታችንን በጾም በጸሎት እያዋረድነው ነው? ጾሙ ሲፈታ የበሬ፥ የበግና የዶሮ ሥጋ ለመብላት ብቻ ነው? እን ዲህስ አይደረግ። ይልቁንስ በቀራንዮ አደባባይ የሞተልንን የመሥዋዕቱን በግ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋእንብላ ደሙንም እንጠጣ ፋሲካችን ክርስቶስ ነውና።

የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን ። ✣

አሜን

# ኪነጥበብ

## የድኅነት ምስክር

ዳንኤል ክብረት

ከግሪክ ተነሥቼ–ማነህ ብትሉኝ –እኔ ተርቢኖስ:-ምንድነህ ብባል–በመጀመሪያው ምእተዓመት እኖር የነበርኩ ግሪካዊ ታሪክ ጸሐፊ ነኝ። የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ክርስቶስ በእሥራኤል ሀገር ያደረገውን ነገር ሁሉ አቴና ከተማ እያለሁ ሰምቼ በጣም እደነቅ ነበረ።

ታዲያ በቅርቡ አንድ የእኔ ብጤ ጓደኛዬ የዚህን የክርስቶስን እውነተኛ መልክ በገሊላ መንደር በምትኖር አንዲት እሥራኤላዊት ሴት ሐውልት የተሠራለት መሆኑን ነገረኝ። ስለትምህርቱ ሰምቼ በእሩቁ ያመንኩ ብሆንም መልኩን የማየት ጉጉትም ነበረኝና በታናሽ እስያ በኩል አድርጌ ወደ ፍልስጥኤም ገሰገስኩ።

ከገሊላ ከተማ እንደደረስኩ በገበያው ሥፍራ፥ በየምግብ ቤቱ፥ በየመንገዱ ሁሉ ሐውልቱን ያሠራችው ሴትና የሐውልቱ ጉዳይ ታላቅ የመወያያ ርእስ ሆኖ ሲነገር ሰማሁ። በኋላም አንድ እሥራኤላዊ አካባቢውን ጠቆመኝና በወይን ወደተከበበ አንድ ሥፍራ ተጓዝኩ። ወደዚያ ቦታ ለመድረስ ጥቂት ርምጃዎች ሲቀሩኝ ብዙ የውጭና የሀገር ውስጥ ሰዎች ወደዚያ ግቢ ለመድረስ ሲተራመሱ ተመለከትኩ።

ወደ ግቢው ስዘልቅ አንዳንዶች ቀና እያሉ ሐውልቱን እያዩ ንድፉን ይሥላሉ፥ ሌሎች የመልኩን ሁኔታ በዝርዝር በብራናዎቻቸው ላይ ያስቀምጣሉ፥ ከሁለቱም የሌሉበት ደግሞ በመደነቅ ከብበው ይመለከታሉ። የእኔ ፍላጐት ግን ከሁሉም የተለየ ነበር። ለመሆኑ ይህች ሴት ምን ያህል ብትወደው ነው ሐውልቱን ያሰራ ችለት? የሚለው ጥያቄ በአእምሮዬ ስለመ ጣብኝ እርሷን የማግኘቱ ጉጉት ነው የበለጠ ያደረብኝ።

ብዙ የውጭ ሀገር ታሪክ ጸሐፊዎች ከብበው ሲጠይቋት ቆይተው ተሰነባብተው ሲለያዩ ጠጋ አልኩና ለመሆኑ ለየትኛው ውለታው ነው ይህን ሐውልት ያሠራሽው? ብዬ ጠየቅኋት። ቀና ብላ በትኩረት ካየችኝ በኋላ «እስከ አሁን ድረስ ይህን ጥያቄ ያቀረበልኝ ማንም የለም በሰፊው ልንገርህ» አለችና ወደቤቷ ይዛኝ ገባች። በቤቷ ውስጥ ሐውልቱ የተቀዳበት ሥዕል በትልቁ ተሥሎ በጸሎት ቤትዋ ይገኛል። ከዚያ ሥዕል ጐን ደግሞ ልጇን የታቀፈች ከፊትዋ ላይ ርኅራኄና ደግነት የሚነበብባት እናት ተሥላለች:- ለካ የዚያ የደጉ የክርስቶስ እናት ኖራለች ደግሞ እኮ ቁርጥ ልጇን።

«ማን ነበር ስምህ? » አለችኝ

«ተርቢኖስ»

«አዎ ተርቢኖስ እኔ አሁን ታሪኩን ልንገርህ ብል የክርስቶስ ደግነቱ፥ ፍቅሩና ምሕረቱ ልቤን እየቀሰቀሰ በዕንባ ጐርፍ ስለሚ ያጥበኝ ድምፄ ይቆራረጥብሃል። አይሰማህም። እናም አንድ ታሪክ ጸሐፊ እንደምንም ነግሬው የጻፈውን ልስጥህ» ብላ ወደ ውስጥ ገባች።

አሁንም እንኳ ዕንባ ያዘሉ ዓይኖቿ የተቋ ጠረ ደመና መስለዋል። እኔኮ የሚገርመኝ ይህ ክርስቶስ ለእኛ ለሰው ልጆች ያለው ፍቅር እንዴት ነው አጥንት ድረስ ዘልቆ የሚገባው? ምን አለበት በእኔም ልቡና እንዲሁ ዘልቆ ቢገባ። ባለፈው ያ ሩፊኖስ የዚያችን የመግደላ ዊቷን ማርያም ታሪክ ሲነግረኝ በዕንባ ተጥለቅልቄ ነበር። ዛሬ ደግሞ የዚህች ሴት ታሪክ የባሰ ነው ልበል? መቼም እኮ ወዳጆቹ የክርስቶስን ፍቅር እንደቀመሰው ሰው የሚያውቀው የለም።

«እንካ ተርቢኖስ» አለችና የተጠቀለለ ብራና ሰጠችኝ። አራት ጥቅሎች። ከላይ ጀመርኩና ረጋ ብዬ ማንበብ ቀጠልኩ:-



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

እንዲህ ይተርካል።

ገሊላ ተናውጣለች። ከተማዋ በምድያም ነጋዴዎች፥ በዓሣ አሥጋሪዎችና በመርከበኞች ተጥለቅልቃለች። የበለጠ ደግሞ ተፍ ተፍ የሚሉት የሮማ ባለሥልጣናት ናቸው ከተማዋን ያተራመሷት። ሉንቱሌ የተባለው የሮማ ታላቅ ባለሥልጣን ከቄሣር ተልኮ ስለሚመጣ ከተማዋ መጽዳት አለባት እያሉ ቆንጨራና አካፋ የያዙ ሰዎች እያሰማሩ ናቸው።

ከከተማዋ በስተምዕራብ የገሊላ እብዶችና ደሃ ነዋሪዎች የሚገኙበት በጎጆ ቤቶችና ሊፈራርሱ በደረሱ የግድግዳ ግንቦች የተጠባበቀ መንደር ይገኛል። በዚህ መንደር ውስጥ ከሀገር የተገለሉ፥ ከማኅበር የተወገዙ፥ አጋንንት ያደሩባቸውና በተለያዩ ደዌያት የተያዙ ይገኙበታል። የከተማው ነዋሪዎች ወደዚህ አካባቢ ዘወር አይሉም። አንድ ሰው በአጋጣሚ እንኳን ብቅ ካለ ወዲያውኑ ገላውን ይታጠባል። ያለበለዚያ በመጸየፍ ቀኑን ሙሉ ምራቁን ሲተፉ ነው የሚውለው።

በዚሁ እርስ በርሱ በተደጋገፈ የድሆችና የችግረኞች መንደር ላይ አስደንጋጭ ወረራ ነበር የተካሄደበት። እነዚያ ድውያን በየቤታቸው ተቀምጠው የስቃይ ሮሮ ሲያሰሙ፥ በየጥጉ መሽገው ሕመማቸውን ሲያስታምሙ፥ ጉልበታቸው አልቆ አካላቸው ደቅቆ፥ መነሳት፥ መላወስ አቅቷቸው ተጋድመው ሲያቃስቱ ቆንጨራና ጎመድ፥ ዱላና አካፋ ያነገቡ ሰዎች መንደሩን አተራመሱት። ዓይነሥውራን ዕውር ድንብራቸውን ይራወጣሉ፥ ትንሽ ጉልበት ያለው ዱላውን እየተመረኮዘ እግሬ አውጭኝ ይላል።

እነዚያ ወራሪዎች መንደሩን እሳት ለቀቁበት። አብዛኞቹ በዚያው በተቆራቆሰ ቤታ ቸው መንቀሳቀስ አቅቷቸው በእሳቱ ወላፈን ተውጠው ቀሩ። በዚህ ሰዓት ነው አንዲት ወጣት እያለቀሰችና ደምዋን እያዘራች ከእሳቱ ውስጥ በሩጫ የወጣችው።

«ያቻት! ይህች ርጉም» አለ አንዱ ቆንጨራውን አንግቦ

«ርኩስ! ውሻ የውሻ ዘር! ዘወር በይ አትጠጊን» አለ ሌላኛው

«እንዳትነካህ! እንዳትነካህ!» አለ ሌላው እየሸሸ።

አንድ ገመድ የያዘ ወጣት በያዘው ገመድ ሸምቀቆ ሠራና በሩቁ ወረወረው። ወደዚያች ወጣት። ገመዱ በወገቧ ሲገባ ወደራሱ ሲጎትታት ማነቆው አጠበቃትና ወደቀች። ከዚያ በኋላ ብዙ ጐረምሶች እየጐተቱ ወደአልታወቀ ቦታ ይዘዋት ሄዱ።

ትጮኻለች፥ ታቃስታለች። ሰውነቷ በጐተታው ተላላጠ። ጐረምሶቹ ብዙ ከጐተቷት በኋላ ወደ ምዕራባዊው የገሊላ በረሃ ወስደው እግሯን አስረው ወረወሯት። ልብስዋ ተቀዳዷል። ፊትዋ ተጋግጧል። ሰውነቷ ቆሳስሏል። በዚያው ላይ ደግሞ ደምዋ ያለማቋረጥ ይፈሳል። አሸዋውን እያለበሰ ቆይቶ ወደውስጥ ይሠርጋል። በአሸዋው ላይ ግን ቀዩ ቀለም ይቀራል የደምዋ።

አካልዋ አጥንቱ ብቻ ቀርቶ በሞሚ የደረቀ የግብፅ አስከሬን ይመስላል። ዓይኖቿ ወደ ውስጥ ጎድጉደው የክረምት ውኃ ቋጥሮባቸው የከረመ ጉድጓዶች መስለዋል። አገጭዋ ሾሎ ጉንጮቿ ወደውስጥ ሰምጠዋል። አንጀቷ ከጀርባ አጥንቷ ጋር ከመጣበቁ የተነሳ ሆድ ያላት አትመስልም። ጉስቁልናና መራቆት ተደራርበው ከሰውነት ተራ አውጥተዋታል።

ቆም ብላ ጥቂት እንደቆየች ከፀሐዩ ንዳድ የተነሣ ራስዋን አዞራትና ባፍጢሟ ተደፋች። እጆቿ ይንቀጠቀጣሉ። ነገረ ዓለሙ ሁሉ ዞሮባታል። ደብዘዝ ያለ ድንግዝግዝ ነገር ብቻ ይታያታል። በዚያ ተኝታ ለብዙ ጊዜ ቆየችና መንቀሳቀስ ጀመረች። ከዚያም ያለችበትን አካባቢ እንዳወቀች ማልቀስ ያዘች። ነገር ግን ጉሮሮዋ ስለደረቀ እሺ ብሎ ሊወጣላት አልቻለም። ዕንባዋም ቢሆን ነጥፏል። አልፎ አልፎ ብቻ የደም ዘለላዎች ይንኳለላሉ።

ወላጆቿ የተለዩዋት ከአሥራ ሁለት ዓመታት በፊት ነው። የታወቁ የወይን ገበሬዎች ነበሩ። እርሷ ፊተኛ ልጃቸው ናት። የተከበሩና የተፈሩ ነበሩ። እርሷን በወለዱ በአሥር ዓመትዋ ግን ያልታሰበ አስደንጋጭ ክስተት ደረሰ ከዚህች ሴት ማኅፀን ደም መፍሰስ ጀመረ። ከዕለት ዕለት ደግሞ የማያቋርጥ ነገር ሆነ። ከግብፅ እስከ ዮርዳኖስ፥ ከሶርያ እስከ ሊባኖስ ድረስ አለ በተባለ ሥር ማሽ ቅጠል በጣሽ አዋቂ መጣቂ ሁሉ እያዞሩ አሳዩዋት:- መድኃኒት የተባለውን ሁሉ ጋትዋት፥ አሠሩላት፥ ቀቡዋት:- ነገር ግን እየባሰ እንጂ እየተሻለ የሚሄድ ነገር ጠፋ።

ወደኋላ ደግሞ ሌላ ጉድ በሠፈሩ ተከሰተ። የእነርሱ ኃጢአት በልጃቸው ላይ መርገም ማምጣቱ በገሊላ ከተማ ጉምጉምታ ይሰማ ጀመር። የሚያውቋቸው እየሸሿቸው፥ የሚያከብሯቸው እየናቁአቸው ሄዱ። የአይሁድ ካህናትም በሩቁ መገርመም አመጡ። ድሮ በተለይ ወይን ሲደርስ ቤታቸው ገበያ ይመስል እንዳልነበር ሁሉ ዛሬ ግን ጭር አለ። ዘመድ ወዳጅ ሠፈርተኛ ማኅበርተኛ ሁሉ በሩቅ መሸሽ ጀመረ። በመጨረሻ የአካባቢው የምኩራብ አለቆች ልጃቸውን የነካ ከቤታቸው የደረሰ ርኩስ ይሁን ብለው አወገዙ። ይህን ጊዜ ጉምጉምታው ለየለትና በይፋ መታማት ጀመሩ።

እናትና አባትዋ በከበርንበት ሀገር ተዋርደን፥ በሰጠንበት ሀገር ለምነን አንኖርም ብለው በልጃቸው ላይ ቆርጠው ያላቸውን ሀብት በሌሊት ጠቅልለው ወደ ሶርያ ኮበለሉ። ይህች የፈረደባት ልጅ በአሥራ አምስት ዓመትዋ ላላሰበችውና ለማትወጣው ዕዳ ተዳረገች።

ዘመዶቿ ሀብት ንብረቷን ወርሰው ከቤት አባረሩዋት። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለአምስት ዓመታት በየጎዳናው እያደረች ዓሣ አስጋሪዎች የሚጥሉትን የተበላሸ የተጠበሰ ዓሣ እየተመገበች ያያት ሁሉ ምራቁን እየተፋባት በስቃይ ኖረች። ልብሷ በላይዋ ላይ አልቆ በብርድ ተቆራምዳ የሰው ልጅ መሆኗ ቀርቶ እንደ እንስሳ በዝናም እየተደበደበች ጎርፍ በላይዋ እየወረደባት በደሟ ተጨመላልቃ ኖረች። የሚጠየፉት እንጂ የሚቀርባት፥ የሚተፉባት እንጂ የሚያጽናናት አልነበረም።

ከአምስት ዓመታት በኋላ ግን በዚህ የገሊላ የቆረቆዘ የምስኪናን መንደር የምንዱባን ሠፈር አንድ እብድ ጥሎት በወጣው፤ ጣራው በሚያፈስ ቤት ውስጥ መኖር ጀምራለች። እብዶች እየደበደቡዋት፥ አጋንንት ያደሩባቸው እያስቸገሯት ያለፉትን ሁለት የመከራ ዓመታት አሳለፈች። ዛሬም ደግሞ በመከራ ላይ መከራ ሲበዛ አይሁድ በገመድ ጎትተው:- ቤትዋን አቃጥለው በዚህ እንኳን ሰው እንስሳ ዝር በማይልበት፥ የዕፅ ዘር በማይታይበት ንዳዳማ በረሃ ወረወሩዋት። «የወደቀ ዛፍ ምሣር ይበዛበታልና።»

ታቃስታለች። ደግሞ መልሳ ፀጥ ትላለች። ትንዘፈዘፋለች። ደግሞ ወደኋላ ብቻዋን ታነበንባለች። ያለ የሌለ ጉልበትዋን አጠራቅማ ከተኛችበት ተነሥታ ቁጭ አለች። ቅልጥ ያለ ዋዕይ እልም ያለ በረሃ።

ራስዋን በጉልበቶቿ መካከል ደፍታ የሰቆቃ ለቅሶ እያለቀሰች የደም ዕንባ ታዘራ ጀመር።

«ፈጣሪዬ ምነው ከሰው ዘ...ር... አሳ...ነስ...ክ...ኝ? በ...ው...ኑ... አንተ ...ም... ትጸየ...ፈኛለህ?» ሲቃው አቋረጣት። ከዚህ በላይ መናገር አልቻለችም። ልቧ ግን ይናገር ነበር። ከአምላኳ ጋር ይሟገት ነበር። ወደውጭ ሳይሆን ወደውስጥ ያነባ ነበር። ዕንባ ሳይሆን እዥ ያመነጭ ነበር። መፈጠርዋን



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ጠላች፥ ሰው መሆንዋን ተንገሸገሸችበት። ማንም የማይፈልጋት እንዲያውም የሚጸየፋት ርኩስና የተረገመች ውዳቂና ውላቂ አድርጋ ራስዋን ተቀበለችው። ሞቷን ተመኘችው። መቃብርን ናፈቀችው። በዚህ ዓለም ተንቃና ተዋርዳ በገዛ ደምዋ ተጥለቅልቃ የገዛ ገላዋንም ተጸይፋ በመጥፎ ሽታ ታጅላ ከመኖር ይልቅ በመቃብር ውስጥ ከምስጥና ዘመሚት ጋር ማውጋቱን መረጠች። ያኔ ደግሞ ሁሉም ያቆማል። እዚያ አይሁድ የሉም ብላ አሰበች።

በረሃው ይነዳል። የፀሐዩ ቃጠሎ አሸዋውን ያጋየዋል። ፀሐይ ደግሞ ከአናት በላይ እየሆነች ነው – ቀትር ሊሆን:- መሬት የተጣደ ብረት ምጣድ ሆናለች። ያች ምስኪን ሴትም አብራ ትነዳለች።

የገሊላ ከተማ ባልተጠበቀ እንግዳ ተናወጠች፥ ባልታሰቡ ሰዎች ተጥለቀለቀች። አይሁድ ተረበሹ። ሰው በሰው ላይ ይተራመሳል። አንድ አስገራሚ ሰው ከበው ድውያን በአልጋና በወሳንሳ ሆነው ይመጣሉ። የቻሉ ደግሞ በዱላ ተመርኩዘው በሰው መሐል እየተጋፉ ወደዚህ ሰው ለመድረስ ጎንበስ ቀና ይላሉ።

የተአምሩ አበዛዝ! ዕውራን ያያሉ! ለምፃሞች ይነፃሉ! አንካሶች ይሄዳሉ! ምኑ ቅጡ። የገሊላ ነዋሪዎች በመገረምና በመደነቅ ተሞልተዋል። የአይሁድ ሹማምንት ደግሞ በንዴት ተቃጥለዋል። ይጠበቅ የነበረው የቄሣር ባለሥልጣን ነገሩን ሰምቶ ጉብኝቱን በርዟል።

የሕዝቡ ብዛት በጨመረ ቁጥር የከተማዋ አራቱም ማዕዘናት በጩኸት ተሞሉ። የተወረረች መሰለች።

ያች ምስኪን ተውተርትራ ተነሣችና በታሠረው እግሯ ቆመች። መልሳ ተቀመጠችና በጥርሷ መገዝገዝ ጀመረች። በመጨረሻ ገመዱን ወርውራ እየተንፏቀቀች ወደ ገሊላ ከተማ አመራች። ጉልበትዋ ተሟጦ አቅመ ቢስ በመሆኗ የዔሊ ጉዞ ነበር አካሄዷ ወደ ገሊላ።

ያ አስደናቂ ሰው ድውያንን እየፈወሰ በዳኑት ሰዎች ተከብቦ ሰው ወደናቀውና ወደጠላው አይሁድ ወደ ተጸየፉት መንደር መጓዝ ጀመረ። የገሊላን ሕዝብ ይበልጥ ያስደነቀው ደግሞ ይህ ነው።

«ምን ዓይነት ሰው ነው እባካችሁ! እንዲያው ሰው አይንቅምኮ» ይላል አንዱ:-

«ምን መናቅ! አገር የናቀውንና የጠላውን ሁሉ ነው ‹ልጄ› እያለ የሚሰበስበው»

«እንዴ! አላየህም ቅድም ያንን ለምፃም ሲዳስሰው:- ይገርማል እኔ ብሆን ንኪች አላደርገውም» ይባባላሉ።

ያ ሰው ከዚያ ወራዳ መንደር ሲደርስ ቆመና ባሻገር ወደ በረሃው ይመለከት ጀመር ሰዎቹም ከበውት ቆሙ።

ያች ምስኪን እየተጐተተች ወደጥንት መንደርዋ ስትመጣ አካባቢው በሰው ተጥለቅልቆ አየች። እነዚያ በረሃ ላይ የጣሏት የማለዳ ጅቦች መስለዋት ወባ እንደያዘው ሰው ባለችበት ትንዘፈዘፍ ጀመር። በዚህ ጊዜ አንድ መኰንን ወደእርሱ ቀርቦ ልጁን ከሞት እንዲያስነሳለት ለመነው። ክርስቶስም ወደዚያ መኰንን ቤት አቀና።

ያች ሴት በመንቀጥቀጥ ስታየው ከቆየች በኋላ ወደመንደርዋ ዘወር ስትል ቀድሞ በዚያ ቦታ አብሯት ይኖር የነበረው ዕውር ሆኖ የተወለደ ለማኝ ድኖ በደስታ ወደእርሷ ሲመጣ ተመለከተች።

«ያ ሰው አዳነኝ! ያ ደግ ክርስቶስ ፈወሰኝ» አላት በእጆቹ እያመለከተ። ዝም ብላ አዳመጠችው።

«ሂጂ! አትፍሪ! አንቺንም ይፈውስ ሻል» አላት በፈገግታ:-

«ይጸየፈኛል:- እኔ» ዕንባዋ ቀደማት

«ማንንም አይጸየፍም። ቁስላችንን ሲዳስስ፥ ለምፃችንን ሲነካ፥ ዕንባችንን ሲያብስ አንዳች አልተጸየፈም። ፀጉራችንን እየዳበሰ በፍቅር ሲያነጋግረን አንዳች የቁጣ መልክ አላየንበትም።

«የእኔና የአንተ ይለያያል»

«ምንም ይሁን ምን እኔ እንዳየሁት እንደእኛ ያለውን፥ ሰው የጠላውን፥ ሰው የናቀውን፥ በቁሙ የሞተውን ይወዳል።»

«ማን ያስቀርበኛል?»

«አይዞሽ በርትተሽ ወደእርሱ ቅረቢ ያኔ ይፈውስሻል።»

ቀና ብላ ስትመለከት ክርስቶስ ከእርሷ ፈቀቅ ብሎ ወደዚያ መኰንን ቤት ያመራል። ዘወር እያለ ግን ወደዚያ የምንዱባን መንደር ያያል። ወደ ሕዝቡ ተራመደች። ፈራችና ቆመች። «አሁንስ ቢያዩኝ ይገሉኛል።» አለችና አሰበች።

«አንቺ መናጢ ደግሞ ምን አመጣሽ» ዘወር ስትል አንድ ፈሪሳዊ አጠገብዋ ቆሟል። ምራቁን ተፍቶባት ሄደ። በዚህ ዓይነት በዚያ ሁሉ ሕዝብ መሐል ስታልፍ ነፍሷ እንደማትተርፍ ገመተች።

«በርትተሽ ወደእርሱ ቅረቢ ያኔ ይፈውስሻል» ያላት ትዝ አላትና እንደገና መራመድ ጀመረች።

ወደተሰበሰበው ሕዝብ ስትደርስ አንዱ ተንጠራራና በጥፊ አጮላት አዞሮአትም ወደቀች። ሌላው ረገጣት። በዚህ ጊዜ ክርስቶስ ወደፊት ስለተንቀሳቀሰ ጥለዋት አለፉ። ጥቂት ቆይታ ተነሣች። «አይዞሽ በርቺ» የሚል ውስጣዊ ብርታት ተሰማት በሌላው በኩል ዞረች:- ደምዋ ይንዠረዠራል። መንገዱ ሁሉ የደም መስመር ሠርቷል–እርሷ የሄደችበት።

በዚህኛው በኩል የተሰበሰቡት የገሊላ ነዋሪዎች ስለነበሩ ተጠይፈዋት መንገድ እየለቀቁ ሸሹዋት። እርሷም አጎንብሳ ስድብና ምራቁን ችላ በትዕግሥት ወደ ውስጥ ገሰገሰች:- ወደ ክርስቶስ።

በመጨረሻ ያንን አስደሳች ሰው አየችው፥ ፈራችና ቆመች:- ምን ትበል:-ነገር ዓለሙ ጠፋት:- «አዎ! ሌላ አልፈልግም ለእኔ ለኃጢአተኛዋ ለእኔ ለርኩስዋ ጨርቁን መንካት ብቻ ይበቃኛል።» ብላ አሰበች። እናም ወደፊት ቀርባ በደቀመዛሙርቱ መካከል ተንጠራርታ ነ...ካ...ች...ው! እንዴ! እንዴ! እንዴ! ደሜ ቆመ! ደረቀ:- ነጠፈ። አለች። እውነትም ቀጥ ብሏል። ደስታና ድንጋጤ አጥለቀለቃት። በዚህ ጊዜ

«ማነው ልብሴን የነካ» የሚለውን የክርስቶስን ድምፅ ሰማች። መንቀጥቀጥ ጀመረች። የተጸየፉት የተቆጣት መስሏት በፍርሃት ሰውነትዋ ራደ።

ደቀመዛሙርቱም

«ይህ ሁሉ ሰው እየተጋፋ ማነው የነካኝ ትላለህን?» አሉት።

«ኃይል ከእኔ እንደወጣ ዐውቃለሁ አንድ ሰው ዳሰሶኛል» አለ ክርስቶስም።

ቀስ ብላ ወደፊቱ ዘወር አለችና በግንባሩዋ ተደፍታ ሰገደች። ዝቅ ብሎ ደግፎ አነሳትና ፀጉርዋን እየዳበሰ ዕንባዋን እያበሰ «ልጄ አይዞሽ እምነትሽ አድኖሻል» አላት። በዚያ የነበረው ሕዝብ ጉርምርምታ አሰማ። እርሱ ግን በፍቅር ዓይኖቹ ሸኛት። ስትሄድ እንደአመጣጥዋ ሳይሆን በፈገግታ ደምቃ በደስታ ፈንድቃ ነበር። ያ ደም አሁን የለም።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

በመጣችበት መንገድ ስትሄድ የሠራችውን የደም መሥመር እያየች ያንን መድኃኒቷን በልቧ ሳለችው።

ጽሑፉን ጨርሼ ቀና ብዬ አየኋት ፡፡ ዕንባዋን ጠራርጋ ይኸውልህ ተርቢኖስ። ከዚያ በኋላ ለሮማ ፍርድ ቤት አቤት ብዬ በስንት መከራ የወይን እርሻው ተመለሰልኝ። እኔም ዘወትር አንድ ነገር ይቆረቁረኝ ጀመር። የዚያ የመድኃኒቴ የክርስቶስ ጉዳይ። በኋላ አንድ ታሪክ ሰማሁ:- አብጋር የተባለ የዑር ንጉሥ ባለሟል የጌታን ሥዕል መሣሉን። የወይን መጭመቂያ ወር ሲደርስ ወይኔን ሸጥኩና ያንን ሠዓሊ አስመጥቼ ይህን ሥዕል አሠራሁት። አምስት መቶ (500) ዲናር ከፍየበታለሁ። ከዚያም አንድ የቀርጻቅርጽ ባለሙያ ከግሪክ አስመጥቼ ይህን ሐውልት አሠራሁት።

ባስበው ባስበው ሌላ የፍቅር መግለጫ አጣሁ። ውለታውን እንዳልረሳ፥ እንዳስታው ሰው:- ለድኅነቴ ምስክር ሐውልቱን አሠራሁ:- የልቤን ፍቅር የምገልጥበት በማጣቴ እንጂ ይህች ትንሽ ነገር አትመጥነውም አለችኝ።

ታሪኳን ትቼ ወደልቡናዬ ተመለስኩ:- ለመሆኑ በክርስቶስ የዳነችው እርሷ ብቻ ናትን? እኛስ አልዳንምን? ግን ለድኅነታችን ምስክር ምን አለን? የሰው ልጅ ኃጢአቱ ለካ ከፋ መሥራቱ ብቻ አልነበረም። የጌታውን ውለታ መርሳቱም እንጂ:- ለካ ይህን ስለረሳን ነው በኃጢአት የተዋጥነው?

እርሷስ ለውለታው ያንን ያማረ ሐውልት መታሰቢያ አኖረች። እኛ ግን ጭራሽ ረስተ ነዋል። አዎ...አዎ...የክርስቶስ ውለታ በደም ሥር የሚሠርፅ እንጂ የሚረሳ አልነበረም።

ተሰናብቻት ስወጣ «ተርቢኖስ» አለ ችኝ። «አቤት» አልኩና ተጠጋኋት «አንድ ነገር ለዓለም ትነግርልኛለህ» አለችኝ ብዕሬን አሹዬ ጠበቅኋት:-

«የኃጢአት ትልቁ ከፋ መሥራት ሳይሆን የክርስቶስን ውለታ መርሳቱ ነው» ብለህ...

ብትልቁ ጽፌው በልቤ ነድፌው ከግቢው ወጣሁኝ። መዳናችሁን አትርሱ ብዬ ለዓለም ልናገር:-

ማቴ.9፥20–23። ማር. 5፥25–34

ተርቢኖስ ✣

# እናስተዋውቃችሁ

በዚህ ዓምድ ገዳማትን፥ አድባራትን፥ ታሪካዊና ተአምራዊ ቦታዎችን፥ የቤተክርስቲያን አባቶችንና ሌሎችንም እናስተዋውቃለን።

የብዙ አንባብያንን ትኩረት የሳበው የቦረዳው ድንቅ ዋሻ ቀደም ብለን እንደገለጽነው በሰሜን ኦሞ ሀገረ ስብከት የሚገኝ ነው። ለቁጥር ሦስት ሐመር መጽሔት የሚሆነውን ዘገባ ዘግቦ እንዲመጣ ሪፖርተራችንን ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ቦረዳ ልከነው ነበር። እርሱም የሚከተለውን ዘገቦ ተመልሷል።

መጽሔት ላይ የሰፈረውን ቃለመጠይቅ አንብቤ ስለተደነቅኩና ስለተመሰጥኩ ይህን ቅዱስ ቦታ ማየት አለብኝ ብዬ ነው። እዚህ ቦታ ስመጣ አሁን ሁለተኛዬ ነው ከዚህ በፊት የካቲት 21:1985 ዓ.ም. ከሦስት ጓደኞቼ ጋር መጥቼ ነበር፤ በዚያን ጊዜ ግን ቦታውን ከማየትና በቦታው አቀማመጥ ከመደሰት በስተቀር ሌላ ያየሁት ነገር አልነበረም። ለሁለተኛ ጊዜ

## የቦረዳው ድንቅ ዋሻ

ከአለፈው የቀጠለ

«ከአዲስ አበባ የተነሳሁት ቅዳሜ መጋቢት 11/1985 ዓ.ም. ነበር። በግምት 460 ኪ.ሜ. የሚሆነውን መንገድ ተጉዤ መጋቢት 12/1985 ዓ.ም. ቦረዳ ገባሁ። ዕለቱ ሚካኤል እንደመሆኑ መጠን የቦረዳ ሚካኤልን ለማክበር የሔደው ሰው ቁጥሩ በመጠኑ ነበር። እኔም ገና ቦረዳ ከመድረሴ በቅርቡ ከተለያየ ሥፍራ የመጡ አንዳንድ ሰዎችን በቦታው ስላዩት አስደናቂ ተአምር መጠየቅ ጀመርኩ። ቃለ መጠይቁን የጀመር ኩት ከደቡብ ሸዋ በሲኬ አዋራጃ ሾኔ ከሚባለው ከተማ ከመጡት ከመምሬ ላቀው ጋር ነበር። መምሬ ላቀው ቤተሰባቸውንና የአካባቢውን ሰዎች ይዘው ነው የመጡት። ድንኳን ዘርግ ተዋል። ከእኔ አንድ ቀን ቀድመዋል። መቅረጸ ድምፄን ወደ መምሬ ጠጋ በማድረግ ከመጡ ጊዜ አንስቶ በቦታው ያዩት ነገር እንዳለ ጠየቅ ኳቸው።

ሐመር — ስምዎት መምሬ ላቀው እንደሆን አስተዋውቀውኛል። መምሬ እዚህ ቦታ ሊመጡ የቻሉት በምን ምክንያት ነው?

መምሬ ላቀው — እዚህ አካባቢ ማለትም ቦረዳ ልመጣ የቻልኩት በእናንተው ቁጥር አንድ ሐመር

መጋቢት 11/ቀን ከቤተሰቦቼ ጋር ወደዚህ ሥፍራ ተመልሼ መጣሁ። የመጣሁ ዕለት ማታ እዚች ቦታ (በእጃቸው በፊት ለፊታችን ያለውን ሜዳ እየጠቆሙኝ) ሣር ገዝቼ አስነጥፌ ተኝቼ ነበር። ድንኳን ውስጥ የገባሁ እንደሆን የሚታየው ብርሃን እንዳያመልጠኝ ብዬ፤ እንዳንዶችም የእኔን አርአያ በመከተል ከእኔ ጋር ውጭ ለማደር የወሰኑ ነበሩ። ታዲያ ምን ሆን መሰለህ ገና ጨለምለም ከማለቱ አንዳንድ የብርሃን ብልጭታ ይታይ ጀመር። ከሌሊቱ በ9:30 ሰዓት በዋሻው ላይ ነበልባል የመሰለ ነገር ሲወጣ ታየኝ። ያ እሳታዊ አካል ወደ ላይ ሲወጣ ብርሃኑ ይኼን ያህል ነበር። ነገር ግን ወደ ታች እየወረደ ሲመጣ የብርሃኑ ድምቀት እየጨመረ መጣ ከዚያ ጥፍት አለ። በድጋሚ ከ10:00 ሰዓት በኋላ ደግሞ ጉልህ ሆኖ ታየ። የእሳቱ (የመብራቱ) ሁኔታ ልክ የቤት ቃጠሎ እሳት ወደላይ እንደሚወጣ ሁሉ ይኼ ያየነው እሳትም እንደእሳት ላንቃ ወደ ላይ ወጥቶ እንደገና ወደ ታች ይመለሳል። ይህን ያየሁት እኔ ብቻ ሳልሆን እነዚህ ዙሪያዬን ያሉት ሁሉ አይተዋል።

ቦረዳ የደረስኩት እሁድ በ8:30 ላይ ነበር አሥራ አንድ ሰዓት የዘወትር



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ጸሎት በዋሻው በራፍ ላይ ስለሚካሄድ እኔም ወደዚያው ሔድኩ። ጸሎቱን የሚመሩት መነኮሳት አልነበሩም። ሰው ቦታ ቦታውን ይዞ እነርሱን ይጠባበቃል። ከትንሽ ቆይታ በኋላ አንድ መነኩሴ አንድ ባሕታዊና ከእነርሱ ኋላ ኋላ ደግሞ የአገሬው ተወላጅ የሆኑ ገበሬ በሰሌን ወደታጠረው የዋሻው በራፍ ገቡ። ሁላችንም ከተቀመጥንበት ተነሣን። ጸሎት ተጀመረ። ከጸሎቱ በኋላ አንድ እንግዳ ነገር ከጥቂት ሰዓታት በፊት መፈጠሩን ጸሎቱን የመሩት መነኩሴ (መነኩሴው ከኤርትራ ከደብረ ቢዘን የመጡ ናቸው) ተናገሩና ክስተቱን መጀመሪያ ያየው ሰው ገበሬው መሆኑን ገልጸው ቦታውን ለእርሱ ለቀቁለት። የአካባቢው ተወላጅ የሆነው ገበሬ ፊቱ ራሱ እንግዳ ነገር እንደተመለከተ ይገልጻል፤ ደንግጢል። ከመናገሩ በፊት ወደ ዋሻው ዞሮ በግንባሩ ተደፍቶ በመስገድ «እግዚኦ እግዚኦ አለ» ወዲያው ተነሥቶ በጋሙኛ ያየውን አስገራሚ ነገር በዙሪያው ለተሰበሰቡት ሕዝብ ማሰማት ጀመረ። ባሕታዊው የክልሉ ተወላጅ ስለሆኑ ወደ አማርኛ መተርጐም ጀመሩ። ገበሬው አቶ አለማየሁ አለሆ ይባላሉ የቦረዳ አዲስ ቤ/ክን አሰሪ ኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ ናቸው።

«እኔ ዛሬ ያየሁት ተአምር ልዩ ነው። እነዚህ ሁለት የእግዚአብሔር አገልጋዮች ወደ እኔ ቤት መሔድ እንደሚፈልጉና ቤቴንም ጸበል መርጨት እንደሚሹ ገለጹልኝ። እኔ ግን አስቀድመው ስላልነገሩኝ እነርሱን የሚያክል ታላቅ የእግዚአብሔር እንግዳ በባዶ ቤት ይዤ መሔድ ስላልፈለግሁ በሌላ ጊዜ ተዘጋጅቼ እንጂ ዛሬ ድንገት ወደ እኔ ቤት አትሄዱም አልኩ። እነርሱ ግን መሔድ አለብን ብለው ርምጃ ጀመሩ እኔም የማይቀሩ መሆናቸውን ሳውቅ ፈጠን ብዬ ወደ ቤት በመሄድ ባለቤቱን ዛሬ ውርደት ውስጥ ገባን ለሰማይ ለምድሩ የከበዱ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ወደ እኔ ቤት መጠተዋል ምን ይሻለናል አልኩዋት። እርስዋም ምን አስቸገረህ ባለን እናስተናግዳቸዋለን ብላ ዳቦ ጋገረች፤ ቡና አፈላች።

የእነርሱን መምጣት የሰማ ጎረቤት ክርስቲያን ሁሉ ቤቴን ከአፍ እስከ ገደፉ ሞላው። ልቤ በደስታ ተሞላ እግዚአብሔር ቤቴን ዛሬ እንደባረከው ተረዳሁ የሰርክ ጸሎት ጊዜ ሲደርስ ወደ ዋሻው በመምጣት ላይ እያለን እነርሱ ፊት ፊቴ እኔ ኋላ ኋላቸው እየተከተልኩ ነበር። በግምት ዋሻው ጋ ለመድረስ መቶ ክንድ ያህል ሲቀር አንድ አስገራሚ ክስተት አየሁ። ከዚያ በፊት አይቼ የማላውቀው ታላቅ አስገራሚ ተአምር ነበር። ጽላቱ ያለበት ዋሻ ዳር እስከዳር ወርቅ የለበሰ መስሏል፤ እሳት በእሳት ሆኗል። እሳቱ እንደ ባንዲራ ይውለበለባል ከመደንገጤ የተነሳ ከእኔ እጅግ የከበሩትን የሃይማኖት አባቶች «አይታያችሁም ይህ ተአምር ኧረ ውደቁ እግዚኦ በሉ» ብዬ ጮኽኩባቸው። እነርሱም ቀና ብለው ሲመለከቱ ሁኔታው ተገልጾላቸው ወዲያው በግንባራቸው ተደፉ። ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ከተደፋንበት ስንነሳ የወትሮው የዋሻ የውጭ ገጽታ ብቻ ነበር። ወዲያው ከወደቅንበት ተነስተን ከአየነው እጹብ ድንቅ ተአምር የተነሳ እንባችንን እያፈሰስን ወደዚህ መጣን።

እኔ እስከ ዛሬ አንድ አመት ከአምስት ወር በዚህ ቦታ ያለምንም መሰልቸት ሳገለግል ምንም አይነት ተአምር አይቼ አላውቅም ነበር። ብዙዎች ገና በመጡ ማግስት ብዙ ነገር አየሁ ሲሉ ለእኔ ላይታየኝ የቻለው በኃጢአት ጭቃ የተጨማለቅሁ ሆኜ መሆን አለበት እል ነበር። ሌላው ቀርቶ የእኔ ትንሹ ልጅ፥ እኔና ትልቁ ወንድሙ ከእርሱ ጋር ሆነን በዚህ ዋሻ አጠገብ ስናልፍ የእኔ ልጅ አሉላ በዋሻው ላይ ብርሃን አይቶ «አባዬ ተመልከት እሳት እያለ ወደ ዋሻው ይጠቁመኝ ነበር።» እኔም እርሱ ያየውን ስላላየሁ የቱ ጋ? እለዋለሁ። እርሱም ፊት ለፊትህ ነዋ እያለ ይወተውተኝ ጀመር። እኔ ግን ላይ አልቻልኩም። ትልቁም ወንድሙ ሊያይ አልቻለም። እርሱ ግን እንዴት አይታያችሁም አውቃችሁ እኔን ውሸታም ለማሰኘት ነው እንጂ፤ ተመልከቱ እሳቱ እየተጎረደ ወደ ጸበሉ ይወድቃል። እናንተም ፊት ላይ ያበራል እንዴት አታዩትም እያለ ሲወተውተኝ። ልጄ አታንገላታኝ የእኔ ዓይንና ያንተ ዓይን ልዩ ሆነዋል።

የእኔ አይን ኃጢአት ከመሥራት የተነሣ ሁሉንም ነገር ማየት አይቻለውም። አንተ ግን ንጹህ ስለሆንክ ይህን ከእኛ የተሰወረውን ነገር ልታይ ቻልክ አንተ የተባረክህ ነህ» አልኩት። ከዚያን ቀን ጀምሮ ትንሹ ልጄን ማዘዝ እንኳን ፈራሁ። ወ/ገብርኤል ወደ ሌላ ቦታ በሚሄዱ ጊዜ ወደ ዋሻ ውስጥ ገብቶ ዕጣን የሚያጥን የእኔ ትንሹ ልጄ አሉላ ነው።

አንድ ቀን ወ/ገብርኤል ወደ ሌላ ቦታ በሔዱ ጊዜ የእኔ ልጅ አሉላ ዕጣን ሊያጥን ወደ ዋሻው ገባ። ሌላ ሰው ግን ዋሻው ውስጥ መግባት አይችልም። ዋሻው ውስጥ ገብቶ ቆየብኝ እኔም ግራ ገባኝ፤ ይኼ ልጅ ምን ሆነ ብዬ ሰጋሁ። ከዋሻው ውስጥ «ቃ–ቃ–ቃ–» የሚል የድንጋይ መፈንቀል አይነት ድምጽ ሰማሁ። ይበልጥ ደነገጥሁ አልገባ ነገር አለተፈቀደልኝም። ወዲያው አሉላ ከዋሻው ወጣ። ለምን እንደቆየ ጠየቅኩት እርሱም በዋሻው ውስጥ ያየውን አስገራሚ ነገር ነገረኝ። የዋናው ዋሻ መግቢያውን የዘጋው ደንጊያ ወደ ላይ ተነሣ ወዲያው ወርቅ በወርቅ የተጎናጸፈ በብርሃን የተከበበ ሰው ሲወጣ አየሁ። በላዩ ላይ ጽሑፍ አለ «ጾም ጸሎት» ይላል ሁለመናው «ጾም ጸሎት» የሚል ጽሑፍ ነው እርሱ ከዓይኔ ሲሰወር ወጣሁ ብሎ ነገረኝ። እኔም ተገረምኩ ተደነቅኹ። በዚህም የተነሣ የቦታውን ቅድስና ስለተረዳሁ ስራዬን ትቼ ጢት ማታ ከዚህ ቦታ የማልለይ ሆንኩ። ታዲያ ብዙ ሰዎች እራሴን ሙሉ ለሙሉ ለዚህ ለቤ/ክን ሥራ አሳልፌ ስለሰጠሁና ወ/ገብርኤል ስለሚወዱኝና ስለሚያስከትሉኝ አንተ ጽላቱን አይተሃል ወይ እያሉ ብዙ ሰዎች ይጠይቁኛል። የእኔ መልስ ግን «የእኔ እናትና አባት እግዚአብሔርን ያመኑት ጽላት አይተው ሳይሆን አባቶቻቸው መምህራን በነገሩአቸው ነው። ስለዚህ ዛሬም እኔ የእግዚአብሔርን መኖርና ኃያልነት ሌሎቹ ባዩት አምኜአለሁ፤ ተረድቻለሁ። ስለዚህ ባላይም ለእግዚአብሔር ቤት የተቻለኝን እሠራለሁ» የሚል ነበር።

እግዚአብሔር ትዕግሥትን ይወዳልና እኔንም በትዕግሥት ከፈተነኝ በኋላ ከእርሱ አለማፈንገጤን አይቶ ዛሬ ለማንም ያልታየ ተአምር ለእኔ ታየኝ። እኔ ዛሬ ትንሹ ልጄ



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

አሉላን ሆንኩ። የታላቁን አምላክ ሥራ አየሁ። እልል በሉ «ዕልልታው ቀለጠ። አቶ አለማየሁ በዋሻው በራፍ ላይ በግንባራቸው ተደፉ ዓይናቸው በእንባ ርሶ።

በማግስቱ አቶ አለማየሁን ጠርቼ ስለዚህ ቦታ የበፊት ሁኔታ የሚያውቁት ነገር እንዳለ ጥያቄ አቅርቤላቸው ነበር። እርሳቸውም ከሕፃንነት ጊዜያቸው ጀምሮ ይሰሙት የነበረውን በማስታወስ የሚከተለውን ተረኩልኝ።

«የዚህ ቦታ ጌታ ስማቸው አቶ ሽቶ ይባሉ ነበር። ታዲያ በዚህ አካባቢ አንዳንድ ጊዜ የቅዳሴና የከበሮ ድምፅ እንዲሁም የዕጣን ሽታ በሚሰማበትና በሚሸትበት ጊዜ የአካባቢው ሽማግሌዎች ነገሩ ግራ ስለሚያጋባቸው በአንድ ወቅት በሬ እስከማረድ ደርሰው ነበር! ሰይጣናዊ ኃይል የሚፈጽመው መስሎአቸው። ዳሩ ግን ይኸም ቢሆን የከበሮውም ሆነ የቅዳሴው ድምፅ የዕጣኑ ሽታ ሊያቆም አልቻለም። የአካባቢው ሽማግሌዎች የተደበቀ ልዩ ምሥጢር ሳይኖር አይቀርም በማለት አቶ ሽቶን እዚህ አንተ ጫካ ውስጥ ያለው ጉድ ምንድን ነው ወይስ በድብቅ የቀጠርካቸው ቄሶች አሉ እያሉ በማሾፍም የሚጠይቁአቸው ብዙዎች ነበሩ። እርሳቸው ግን እኔ የማውቀው ምንም ነገር የለም! ልክ እንደናንተው ከልጆቼ ጋር የሚሆነውን እናዳምጣለን። ዳሩ ግን ምክንያቱና ምሥጢሩ ሊገለጽልን አልቻለም በማለት ይመልሱ እንደነበርና እርሳቸውም ከሞቱ በኋላም ቢሆን ይኼ ነገር እንዳላቋረጠ የእኛ አባቶች ይናገራሉ።

ዛሬም ቢሆን ለዚህ ምሥክርነታቸውን የሚሰጡ ብዙ አረጋውያን ስላሉ ማረጋገጥ ትችላለህ ብለውኛል።

እኔም አንድ አዛውንት አናግሬ አቶ አለማየሁ የነገሩኝን ታሪክ ደግመው ነግረ ውኛል። ወላይታ ሶዶ የሚኖሩ ወ/ሮ አስካለ ሐብተ ወልድ ይህን በማስመልከት ቃለ መጠይቅ አድርጌላቸው ነበር። ወ/ሮ አስካለ ከዚህ በፊት ወደ ቦረዳ ሄደው በቦረዳ የሚታየውን ብርሃን በአይናቸው ያዩና የከበሮውን ድምጽም ያዳመጡ ናቸው። እንዲሁም በቦታው በፈለቀው ጠበል ከአስም በሽታ ተፈውሰዋል። እርሳቸው እንደሚሉት!

«የዛሬ 30 ዓመት ገደማ በጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን የንግሥ በዓል ላይ የድሮው አባ መላኩ በኋላም የኢትዮጵያ ፓትርያርክ የሆኑትና አሁን በሞት የተለዩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት የዚያን ጊዜ ገና ፓትርያርክ አልነበሩም። ለንግሥ ለተሰበሰበው ሕዝብ ሲናገሩ በዚህ በደቡብ በኩል በእጃቸው ወደ ቦረዳ እየጠቆሙ በዋሻ ውስጥ ያለ የቆየ ጽላት ይወጣል። በዚያን ጊዜ ግን እኔ አልኖርም ጊዜ የሰጠው ይህን ያያል» ብለውን ነበር። ይህን እኔው ራሴ በገዛ ጆሮዬ የሰማሁት ነው።

በቦረዳ የሚሰማውና ታየ የሚባለው እንዲሁም ተፈጸመ የሚባለው ነገር ሁሉ አስገራሚና ነገሩን በአንክሮ ላላጤነው ሰው አጠራጣሪ ይሆናል። እዚያ በቆየሁበት ወቅት ካነጋገርኳቸው ሰዎች አንዱ ዕድሜው በግምት በ26ና በ30 መካከል ያለ አንድ ወጣት ነው። የቀድሞ ስሙ መናይዛ ይባላል አሁን ግን ኃይለ ሚካኤል ተብሏል። ነዋሪነቱ በቦረዳ ከተማ ነው። ቀድሞ የሌላ እምነት ተከታይ ነበር። 24 ዓመት ሙሉ በዚያ እምነት እንደነበረ ይናገራል። ቀድሞ የሚያውቁትም ሰዎች እውነቱን መሆኑን አረጋግጠውልኛል። እንዴት ወደዚህ ቦታ ሊጠራና ሊሳብ እንደቻለ ለጠየቅኩት ጥያቄ ሰፊና አስደናቂ መልስ ሰጥቶኛል።

«እኔ መጀመሪያ እንደነገርኩህ የሌላ እምነት ተከታይ እንደመሆኔ በዚህ ዋሻ ውስጥ አለ ስለሚባለው ጽላት መጥፎ አመለካከት ነበር ያለኝ። እንዲያውም የሰይጣን ሥራ አድርጌ ነበር የማየውና የምናገረው። ታዲያ አንድ ቀን ምን ሆነ መሰለህ ለሥራ ጉዳይ ወደ ምዕራብ በመኪና ተጭኜ ስሔድ እዚህ አካባቢ ስደርስ የሆነ ትዕዛዝ መጣ «ውረድ» የሚል። ድምፁን የምሰማው እኔ ብቻ ነበርኩ። እኔም ለምንድን ነው የምወርደው ብዬ ስመልስ አብረውኝ የነበሩት ሰዎች ግራ ተጋብተው ነበር። ከማን ጋር እንደማወራም ጠየቁኝ። ነገሩን ነግሬአቸው ከመኪናው ወረድኩ። ከመቶ ሜትር ርቀት ላይ የታቦት ዓይነት ጃንጥላ የያዙ ከአጠገባቸው አበባ ያለ ሦስት ሰዎች «ና እኛን ተከተል ብለው አዘዙኝ። እኔም ምንም ምርጫ ስለሌለኝ ተከትያቸው ሄድኩ። አንድ ቋጥኝ አካባቢ እንደደረስን ማንነታቸውን ነገሩኝ። በግራና በቀኝ ያሉት ሚካኤልና ገብርኤል መሆናቸውን! በመሃከል ያለችው ቅድስት ድንግል ማርያም እንደሆነች ገለጡልኝ። ቀድሞ የነበርኩበት እምነት የእነርሱን ረዳትነትና አማላጅነት የማይታመንበት ነበር።

እኔም ይህንኑ የማስተምር ነበርኩ። ዛሬ ግን በገሃድ ተገልጸው መጡብኝ። ማንነታቸውን ከገለጹልኝ በኋላ የሰጡኝ ትእዛዝ የነበርኩበትን እምነት ትቼ የኦርቶዶክስን እምነት እንድከተል ነበር። ከዚያም ተሰወሩብኝ።

ከስድስት ወር በኋላ በራእይ ተመልሰው መጡብኝ። ከተኛሁበት እንድነሳና እነርሱን እንድከተል አዘዙኝ። እኔም እንዳዘዙኝ ተከትያቸው ወጣሁ። ወዴት እንደምንሔድም ጠየቅኩአቸው። እነርሱም እኛ ወደምናሳይህ ቦታ ነው! እኛ ያለንበትን ዋሻ ልናሳይህ ነው ብለው ነገሩኝ። በእኔ እምነት ወደዚያ እንድሔድ አይፈቀድልኝም አልኩአቸው። እነርሱም «እዚያ ሒደህ ሰይጣን መሆኑን አለመሆኑን ታረጋግጣለህ። ግን ተከትለኸን ና» ብለው ከምሽቱ ስድስት ሰዓት አካባቢ ነው እዚህ ቦታ ይዘውኝ መጡ የዚያን ጊዜ ሰው አልነበረም። ጽናሕ አሳዩኝ። ምንድን ነው አልኩአቸው። ዕጣን ማጠኛ መሆኑን ገለጹልኝ። በቦታው ብርሃን ነበር እኔም በልቤ ይህ የሰይጣን ሥራ ሳይሆን አይቀርም እል ነበር። እነርሱ ግን የሰይጣን ሳይሆን የእግዚአብሔር ሥራ መሆኑን ገለጹልኝ። ወደ ዋሻው እንድገባ አዘዙኝ እንዳዘዙኝ ወደዋናው ዋሻ የሚያስገባው የዋሻ በር ድረስ ገባሁ የዕጣን ሽታ ሸተተኝ ብርሃን ታየኝ ሦስቱም ይታዩኝ የነበረው በሠያፍ ነበር።

ይህን ለማን ነው የምነግረው አልኩአቸው። እነርሳቸውም ወደ ቦረዳ ከተማ ሂድ በነገው ዕለት አንድ ትልቅ ሰው ይሞታል በዚህ ምክንያት ብዙ ሰው ይሰበሰባል ስለዚህ በዚያ ሳትፈራ ሳታፍር ያየኸውን መሥክር አሉኝ።

እንደተባለው በቦረዳ ከተማ የታወቁ አንድ ሰው ሞቱ። በቦረዳ ሚካኤል ብዙ ሰው ተሰበሰበ። እኔም የታዘዝኩትን ለመናገር እየሄድኩ በመፍራት እመለስ ጀመር። እየሄድኩ ስመለስ በሦስተኛው ገንዘብ ሚኒስቴር የሚሠራ ታደሰ የሚባል ሰው ሁኔታዬ ስለገባው ምንድን ነው ችግርህ ብሎ ጠየቀኝ። ነገርኩት። ታዲያ ምን አስፈራህ ተናገር አለኝ። እኔም ቀድሞ የነበርኩበት እምነት ተከታዮች ይገድሉኛል አልኩት። ምንም አያደርጉህም ተናገር አለኝ። እኔም ቢገድሉኝም ይግደሉኝ ብዬ ከመጀመሪያው አንስቶ ያለውን ተናገርኩኝ። የተሰበሰበው ሰው ሁሉ ጉድ አለ! ብዙዎችም ወደ ኦርቶዶክስ እምነት ገቡ። የእኔን ሁኔታ አይተው ቀድሞ የነበርኩበት እምነት ተከታዮች ተከፋፈሉ።» በማለት ረዘም ያለ ታሪኩን አጫውቶኛል። ወጣቱ በአሁኑ ጊዜ በቦረዳ ዋሻ አካባቢ የተቻለውን አስተዋጽኦ እያበረከተ ነው።

በቦረዳ ዋሻ አካባቢ በዛ ያለ የጸበል ቦታ ይገኛል። በእነዚህ ጸበሎች እየተጠመቁ የዳኑ 430 ህሙማን ይገኛሉ። ከእነዚህም ውስጥ ግማሾቹ ከአስም ሌሎቹም ከሽባነትና ከዕውርነት እንዲሁም ከሌሎች በሽታዎች የተፈወሱ ናቸው። በቦረዳው ጠበል ከተፈ ወሱት መካከል አንዱ የሆኑትን አቶ አዳነ አሰፋን አነጋግሬ ነበር። የአራት ልጆች አባትና ቴፕና ሰዓት በማደስ የሚተዳደሩት አቶ አዳነ ከ1982 ዓ.ም. ጀምሮ ዓይናቸውን



©ማኅበረ ቅዱሳን

www.eotcmk.org

ይጋርዳቸዋል። ከዚህ የጨለማ ሕይወት የወጡበትን ቀን ሲያዘከሩ እንዲህ ብለዋል «አንድ አየለ የተባለ ወንድም ወደ ቦረዳ ይሄዳል እዚያም ሄዶ በነበረበት ጊዜ ጠበል ይዞ መጥቶ ስለነበር ይዞት ከመጣው ጠበል ዓይኔን እንዳባብሰው ሰጠኝ። እኔም ጠዋት ላይ ከእንቅልፌ ተነስቼ ጸሎት አድረጌ ዓይኔን ቀባሁት። ወዲያው ጸበሉ ዓይኔን እንደነካው የሆነ ነገር ከላዬ ተነሥቶ ሲሔድ ተሰማኝ። ወዲያውም ዓይኔ በራ ሁሉንም ነገር አጣርቼ ላይ ቻልኩ።

እኔም ከሦስት ዓመት የጨለማ ኑሮ ስለተላቀቅኩኝ ይህን ቅዱስ ቦታ ማየት አለብኝ ብዬ ስለቆረጥኩ ወደ ቦረዳ መጣሁ። በዚህም አንዳንድ አስደናቂ ነገሮችን ላይ ችያለሁ።

ቀጥሎ የምጠቅሳቸውን ሰዎች እይታ ለምሥክርነት ልጥቀስ «የተባለውን ብርሃን ባላይ ኖሮ በጥርጥር ማዕበል ሰጥሜ» ነበር የሚሉ በሽተኛ ልጃቸውን ሊያስጠምቁ የመጡ አንድ አባት ናቸው። በበኩሉ ሰው ሁሉ ብርሃን አየሁ ሲል ለእኔ ስላልታየኝ ከፍተኛ ሙግት ላይ ነበርኩ ከራሴ ሐሳብ ጋር ምናልባት እነዚህ ሰዎች የባትሪውን ብርሃን እያዩ ይሆን ወይስ ተወርዋሪ ኮከብ እያዩ በእርግጥ ከባድ ፈተና ላይ ነበርኩ። ሰኞ መጋቢት 13/1985 ዓ.ም አቶ ወ/ገብርኤል በነጋው ዕለት ተአምር ይታያል ብለው ስለተናገሩ ገና ከማለዳው ጀምሬ ነበር የዋሻውን አካባቢ ስሽከረከረው የነበረው። አንድ በአንድም አጠናሁት። ተአምር ነው ወይስ የሰዎች ብልሃት ብዬ የሌሊቱን ጸሎትም አብሬ ዋልኩ ይገርምሃል አንተ ተኝተሃል አሉ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ላይ የሻማውም ሆነ የፋኖሱ መብራት ጠፍቶ አካባቢው ሁሉ በጽልመት ጋቢ በተጀቦነ ጊዜ ከዋሻው ውስጥ ብርሃን ነበር። ጥርጣሬዬ ከፍ አለ። አንድ ሰው በውስጥ ሆኖ ፋኖስ ያበራ ነበር የመሰለኝ። የጠረጠርኳቸው ሁለቱን መነኮሳት ነበር። ቀስ ብዬ የእጅ ባትሪዬን አብርቼ ወደ ውስጥ በጥሩ ሁኔታ ልመለከትበት የምችልበትን ቦታ ይገኘ አየሁ። ያማኋቸው መነኮሳት ከዋሻው ውጭ ናቸው። በዋሻው ውስጥ ምንም ሰው የለም። ቀስ በቀስ የብርሃኑ ኃይል እየደመቀ መጣ ፈጽሞ ተአምራዊ መሆኑን ገሃድ አደረገው። አካባቢው ሁሉ በብርሃን ተጥለቀለቀ ጥርጣሬዬ ሁሉ እንደ ጉም በኖ እንደ ጢስ ተኖ ጠፋ። የተባለውን በዓይኔ ላይና ላረጋግጥ በቃሁ አምላኬን አመሰገንኩ።

የወ/ሮ ካሰች ላቀው እይታ ደግሞ አስደናቂ ነው «የአየሁት አስደናቂ ነገር አሁንም ቢሆን በእዝነ ልቦናዬ እንደተቀረጸ ነው። እውነቱን ለመናገር በቦታው የሚታዩትን ብርሃናት ያየሁት የመጣሁ ጊዜ ነው። ዳሩ ግን በ14/7/85 ዓ.ም. ያየሁት ተአምር ግን ለታሪክ ነው። አራት ሰዓት ገደማ ላይ ተርታ ጠብቀው በዛ ያሉ ብርሃናት ሲመጡ አየን። ብዙም አልቆዩም አንድ በአንድ ከዓይናችን ተሠወሩ። ይህን አንተም ማየትህን ነግረኸናል። ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ላይ በሐሳቤ መላእክቱ ቅዳሴ የሚገቡ ከሆን በዚህ ሰዓት መሆን አለበት ብዬ በማሰብ ዓይኔን በማሻሸት እንቅልፌን አባርሬ ፍጥጥ ብዬ ተቀመጥኩ። ዓይኔን ወደ ዋሻው ወረወርኩ ብርሃናዊው ትዕይንት ተጀመረ። ቦግ ቦግ እያለ ከዋሻው ውስጥ የወጣ መሰለን። ወደ እኛ እየቀረበና ወደ ታች ሲወርዱ አካባቢው በብርሃን ጎርፍ ተጥለቀለቀ።

በብርሃኑ ውስጥ ሁለት ሰዎች ታዩኝ። ረዣዥም ቀሚስ የለበሱ ይመስላሉ። በራሳቸው ላይ መሶበ ወርቅ የያዙ ይመስላሉ። ፊት ፊት የምትመራው ሴት መሆንዋ ታየኝ። የኋለኛው ወንድ ነው ዙሪያው ደስ በሚል ኅብረ:ብርሃን ተከቧል። ወደ እኛ ሲቀርቡ ብርክ ያዘኝ፤ መነሳት አልቻልኩም፤ በአፍጢሜ ተደፋሁ፤ በውስጥ ግን ልዩ የደስታ ስሜት ተሰማኝ። ያ ክስተት ከአምስት ደቂቃ በላይ አልቆየም ወዲያው ጠፋ።

ቦረዳ በሪፖርተሩ አመለካከት

በመሠረቱ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖታችን ተአምራትን የምታደርግና ገቢረ ተአምራት ወመንክራት የሚደረግባት ብትሆንም ተአምርን መሠረታዊ መመሪያዋ አታደርግም ምክንያቱም ሰይጣናዊ ተአምርም ለማሳሳት ሲባል ይደረጋልና።

ብዙ ሐሰተኞች ክርስቶሳውያን ወደ ዓለም መግባታቸውንና ብዙዎችን ለማሳት ምትሐታዊ ተአምራት እንደሚያደርጉም በቅዱስ ወንጌል ላይ የሰፈረ ነው። ስለሆነም ገቢረ ተአምራት ወመንክራት በሚደረግበት ጊዜ በአንክሮ ማጤንና በሃይማኖታዊ ሚዛን መመዘን ግንባር ቀደም ትኩረት የሚሰጠው ሆኖ ይገኛል። ያለበለዚያ «ይህ በእግዚአብሔር ካልሆነ በስተቀር አይደረግም በሚል የየዋህነት እምነት የሐሳዊ መሲሆች ሰለባ እንሆናለን። የሚያብለጨልጭ ሁሉ ወርቅ እንዳይደለ ሁሉ ተአምራትም ሁሉም ከእግዚአብሔር ብቻ የሚመጡና የሚደረጉ አይደሉም» ሰይጣን ራሱ የብርሃን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና 2ቆሮ.11፥14።

እንግዲህ የሚከሰቱትን ክስተቶች በጽሞናና በአንክሮ ማስተዋሉ የብልህ ክርስቲያን ሥራ ነው። የቦረዳውን ዋሻ ታሪክ ከሰማሁበት ጊዜ አንስቶ እስከ አሁን በአንክሮ ተከታትየዋለሁ።

አካባቢው የደረሰ ሰው ሁሉ ያለምንም ማመንታት እንደሚያረጋግጠው አንድ ገሃድ እውነት አለ። ይኸውም የቦታውን ቅድስና ነው። ያለምንም ማጋነን ቦታው የቅዱሳን መካን መሆኑን በዓይን ዓይቶ በልብ መዝኖ መናገር ይቻላል። የብዙኀኑን ትኩረት የሳበው ይህ ሥፍራ በመንፈስ ቅዱስ የተቃኙ ከቅዱሳን መካናት አንዱ መሆኑን ቦታው የደረሰ ሁሉ የሚያሰማው የምሥክርነት ቃል ነው። መንፈስን ይለውጣል። ከገሃዱ ዓለም ውጭ በሆኑ እንግዳ ክስተቶች የታጠረ አካባቢ ነው። ብርሃናዊ አካላት በየጊዜው ይጎበኙታል። ከብዙዎች ምሥክርነት እንደተረጋገጠው ቅዱሳን ቅዳሴ የሚያሰሙበት በሠውራን ኃይላት ማኅሌት የሚቆምበት ሥፍራ ነው።

ብርሃናውያን አካላት የሚታዩት አብዛኛውን ጊዜ ከሌሊቱ በዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ላይ ነው ይኸንንም ከብዙ ሰዎች ያረጋገጥኩት ነው። አንዳንድ ጊዜ በሌላው ሰዓትም ይታያሉ። ብርሃናውያን አካላቱ አገላለጣቸው ከሰው ሰው ይለያል። አንዱ የብርሃን ብልጭታ ብቻ ማየቱን ሲናገር ሌላው ደግሞ ከዚያ ለየት ያለ ክስተት እንዳየ ይናገራል።

በእርግጥ እንዲህ ዓይነቱን ተአምር ለማየትና ለመስማት ፈቃደ እግዚአብሔር ወሳኝነት ቢኖረውም አንዳንድ ሰዎች ግን ሌሊት የሚቃዡትን ሁሉ እንደ ብርቅ አድርገው የራሳቸውን አመለካከት በሕዝቡ ልቦና ላይ ሊያሰርጹ ሲጣጣሩ ተመልክቻለሁ። የማጥመቅ ሥልጣንና ፈቃዱ ሳይኖራቸው በራእይ አጥምቅ ተብያለሁ እያሉ በማያውቁት ሥራ ገብተው ሕዝበ ክርስቲያኑን ያሥከፉትም እንዳሉ ልመለከት ችያለሁ።


በአጠቃላይ ግን የቦረዳ ዋሻ በውስጡ የያዛቸው ጽላት ታሪካዊነት እንዳላቸውና አስደናቂ ቅዱስ መካን መሆኑን ጠበሉም ፈዋሽ መሆኑን ላረጋግጥ ችያለሁ። ይህን ታላቅ ቅዱስ ቦታ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሊንከባከበውና ሊጠብቀው የሚገባ ሲሆን የኦ/ተዋሕዶ እምነት ተከታዮች ደግሞ በዋሻው ውስጥ ያለው ጽላት ወጥቶ የሚገባበትን ቤ/ክን ማሠራት መንፈሳዊ ግዴታችን ነው። ✣

## ለአንባብያን

የበረከት ወንጌልና ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ ዓምዶቻችን ሰሙን ሕማማትን በሚመለከቱ ጽሑፎች በመተካታቸው በቁጥር አራት እትማችን የሚቀጥሉ መሆኑን በታላቅ ትህትና እንገልጻለን።



©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org




የሥላሴ ጽላት አለበት የሚባለው ዋሻ



«የእኔ ጌታ ለእኔ ለምስኪን ኃጢአተኛ ይህን ድንቅ ተአምር አሳየኝ--- »
አቶ ዓለማየሁ አላሆ



በቦረዳ ጠበል የተፈወሱት አቶ ምንዳዬ ወልደየስ



በሥራ ላይ ያለው አዲሱ የቦረዳ ቤተ ክርስቲያን

**አዲሱን የቦረዳ ቤተ ክርስቲያን ለመርዳት የምትሹ**
**በሚከተለው አድራሻ ትብብራችሁን አድርጉልን**
**ለቦረዳ ቤተ ክርስቲያን አስሪ ኮሚቴ**
**የባንክ ሒሳብ ቁጥር 10157**

**አርባ ምንጭ**

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org



## ማኅሌት

የጌታ ቃል በመላእክት፥
ዝማሬአቸው በሰማያት፥
በምድርም የካህናት።
መዓዛሽ ሳበኝ ከሩቅ፥
አልቻል አለኝ ከአንቺ መራቅ።
ከበሮ ሲመታ ሲጎሰም፥
ሁሉም በመቅደስ ሲከትም።
ጸናጽል ሲንሿሿ ማኅሌት ሲሰማ፥
ልብ ሐሴትን ሲሰማ።
ሕይወት ዘርቶ፥
መረስረስ ነው ማኅሌት ሰምቶ።
ዕጣን ሲጤስ ሃሌ ሲባል፥
በጣፈጠው የእግዚአብሔር ቃል።
ተቀምጦ በማኅሌት፥
አጣፍጠውት ሊቅ ቀሳውስት፥
ሸብሸባቸው የዲያቆናት፥
በተማሩት በመላዕክት።

የእግዚአብሔር ቃል ይጣፍጣል፥
በሚሰሙት ይወደዳል፥
ደንዳናን ልብ ያሸንፋል፥
ሰይጣናትን ድል ይነሳል፥
እንግዲህ ስለዚህ ቃል።
ማኅሌት መልእክት ንገሪ፥
እንግዲህ በስራሽ ተሰማሪ፥
ያልሰሙትን ዞረሽ ጥሪ።
የቅዱስ ያሬድ ቅርሳችን፥
የእኛነት መለያችን።
አቋቋሙ ዝማሜው፥
የመላእክት ዝማሬው፥
ጸናጽል ከበሯቸው፥
በእኛም አለ ቀዳሴአቸው፥
የምስጋና ትናጋቸው።

ከአባይነህ ካሴ

ዋጋ 3.00 ብር

አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

©ማኅበረ ቅዱሳን

ይህን መጽሔት ያለ ማኅበረ ቅዱሳን ፈቃድ በከፊልም ሆነ በሙሉ ማሳተም ፣እንዲሁም በማንኛውም መልኩ ለሽያጭ ማዋል በህግ የተከለከለ ነው፡፡